# ኪ ዳ ና ች ን

---

## ልዩ ዕትም፤ ነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፱ ዓመተ ምሕረት።

---

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥
ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳትና
የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ልጆች የኾነውንም ኹሉ፡ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡
በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም።

---

**የኪዳናዊ ሓኪም አክሊሉ፡ ወስመ-ጥምቀቱ፡ አክሊለ-ሰማዕት**
**እና**
**የኪዳናዊት ሓክሚት ቤዛዊት፣ ወስመ-ጥምቀታ፡ ዕሴተ-ገብርኤል**

## <u>ተክሊል፣ ከብካብ እና ሠርግ።</u>

## <u>የበዓሉ አጠቃላይ መርሓ ግብር እና ሥነ-ሥርዓት።</u>

**አዘጋጅ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ።**



# በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡

### የተፈጸመው፡

### የኪዳናዊ አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ፡ ወስመ-ጥምቀቱ፡ አክሊለ-ሰማዕት
### እና
### የኪዳናዊት ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ፣ ወስመ-ጥምቀታ፡ ዕሴተ-ገብርኤል

## ሥርዓተ-ተክሊል፤ በዓለ-ከብካብ እና የሠርግ ድግስ።

## የበዓሉ ሥነ ሥርዓት፡ አጠቃላይ መርሓ ግብር።

### ሥርዓተ-ተክሊሉ፤ በዓለ-ከብካቡ እና የሠርጉ ድግስ የሚካኼዱባቸው ሥፍራዎች፡-

**፩ኛ፡** ቤተ-ቅዱስ ኪዳን፤ ዐጸደ ሓመረ-ኖኅ መካነ-ምሕረት፤ ቂርቆስ ሰበካ፤ ዐዲስ አበባ መናገሻ ከተማ፤ ምድረ ኢትዮጵያ።

**፪ኛ፡** ደብረ ጽዮን፡ ቅድስት ማርያም ሰበካ ቤተ-ክርስቲያን፣ ደሴተ-ዙዋይ፤ አሩሲ ሀገረ-ስብከት፤ ኢትዮጵያ።

**፫ኛ፤** ሳሬም ቤተ-ነግድ፣ ሰሜን ማዘጋጃ ቤት መዳረሻ፣ በላይ ዘለቀ ጐዳና፣ ጉለሌ ክፍለ-ከተማ፤ አዲስ-አበባ፤ ኢትዮጵያ።

## የሥርዓተ ተክሊሉ፣ የበዓለ-ከብካቡ እና የሠርጉ ድግስ፣

## አጠቃላይ መርሐ ግብር።

### አንደኛ፣

የሥርዓተ ተክሊሉ ዕለት፦ ማግሰኞ፣ ነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፱ ዓ. ም. በዓለ-ፍልሰታ፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም።

ጊዜው፡- ከዋዜማው ሰኞ ማታ፡ ፪ ሰዓት ጀምሮ፣ እስከማግሥቱ፡ ማግሰኞ ንጋቱ ፲ ሰዓት ድረስ።

### ኹለተኛ፡

የበዓለ-ከብካቡ ዕለት፦ እሑድ፡ ዕለተ-ሰንበት ዝልፍት፣ ነሓሴ ፳፩ ቀን፥፳፻፱ ዓ. ም.

ጊዜው፡- ከዋዜማው ዕለተ-ሰንበት፣ ነሓሴ ፳ ቀን፥ ፳፻፱ ዓ. ም. ከጧቱ ፫ ሰዓት፣ እስከማግሥቱ፣ እሑድ፡ ዕለተ-ሰንበት ዝልፍት፣ ነሓሴ ፳፩ ቀን ፳፻፱ ዓ. ም. ከንጋቱ ፲፪ እስከ ምሽቱ ፲፪ ሰዓት ድረስ።

### ሦስተኛ፣

የሠርጉ ድግስ ዕለት፦ ዕለተ-ሰንበት፣ መስከረም ፲፫ ቀን፥ ፳፻፲ ዓ. ም.

ጊዜው፡- ከንጋቱ ፲፪ እስከማታው ፪ ሰዓት።

# ክፍል አንድ።

### አንደኛ፣

የሥርዓተ ተክሊሉ ዕለት፦ ማግሰኞ፣ ነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፳፻፱ ዓ. ም. በዓለ-ፍልሰታ፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም።

ጊዜው፡- ከዋዜማው ሰኞ ማታ፡ ፪ ሰዓት ጀምሮ፣ እስከማግሥቱ፡ ማግሰኞ ንጋቱ ፲ ሰዓት ድረስ።

የመርሐ-ግብሩ ዝርዝር፦

፩. ይህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ ሥርዓተ ጋብቻ በሚፈጸምበት፡ በዚሁ ዕለት፣ ጊዜና መካን [ቦታ]፡ የሙሽራውና የሙሽሪቷ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ቤተሰቦች እና ጥሪ የተደረገላቸው ኪዳናውያን ወንድሞቻቸውና ኪዳናውያት እኅቶቻቸው፡ ሥርዓቱ ከሚጀመርበት፡ ከምሽቱ ፪ ሰዓት በፊት፡ ቀደም ብለው፡ በተዘጋጀላቸው ቦታ ይገኛሉ።

-ስለሰዓት አከባበር፦ እንዲህ፡ በሥርዓት የተወሰነውን የሰዓት ጊዜን ማክበር፡የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን አንዱ ምልክት ነው።

-አለባበስ፦ በበዓለ ኢትዮጵያ እንደኾነው ኹሉ፣ ኢትዮጵያዊዉን ብሔራዊ የበዓል ባህል የተከተለና የትንሣኤ ብርሃን ልጆች መኾናችንን የሚያመላክተው፡ ጸዓዳው [ነጭ] ያገር ልብስ ቢኾን ይመረጣል።

-<u>ስለጫማ</u>፡- “ፍታሕ አሣእኒከ እምእገሪከ! እስመ መካን፡ እንተ አንተ ትቀውም ባቲ ምድር፡ ቅድስት ይእቲ። *ጫማዎችህን፡ ከእግሮችህ አውልቅ! ይህች አንተ፡ የቆምህባት ምድር፡ ቅድስት ናትና።"* የሚለውን መለኮታዊ ቃል፡ የበዓሉና የሥርዓቱ ታዳሚዎች ዅሉ፡ ዐውቀው የሚፈጽሙት ነው። (ዘፀአ. ፫፥ ፭።)

<u>-ቅዱስ ቍርባን ስለመቀበል</u>፡- በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን፡ ዅላችንም፡ የቅዱሱ ቍርባን ተሳታፊዎች በመኾናችን፥ ሥርዓተ-ቅዳሴው የሚፈጸመውም፡ በሌሊቱ ሰዓት በመኾኑ፡ ከዋዜማው እኩለ-ቀን በኋላ፡ ከመብልና መጠጥ ታቅበን መቆየት ያለብን መኾናችንን፡ በእየራሳችን እንዳንዘነጋው ያስፈልጋል።

፪. ሙሽራው፡ በሚዜዎቹ፣ ሙሽሪቷ፡ በደንገጥሮቿ ታጅበው፡ <u>ልክ፡ ከማታው፡ በ፩ ሰዓት ተኩል፡</u> እቅዱሱ ቤተ-ኪዳን ይደርሳሉ።

-እዚያ እንደደረሱ፡ ሙሽሮቹ፡ እያንዳንዳቸው፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ ፍጹም ሃይማኖታቸው ኾነው፡ ከቤተ መቅደሱ ፊትለፊት በመቆም፡ በመጀመሪያ ፩ [አንድ] ጊዜ፣ ቀጥለውም፡ ፫ [ሦስት] ጊዜያት፡ ለፈጣሪያቸው፡ ለእግዚአብሔር፡ የአምልኮ ስግደታቸውን ያደርጋሉ።

-በዚህ ስግደታቸው አማካይነት፡ ምስጋናቸውን፡ ለፈጣሪያቸው በማቅረብ እና ደስታቸውን በመግለጽ፡ የየግል ጸሎታቸውን አድርሰው እንዳበቁ፡ በየተሰናዱላቸው የክብር ወንበር ላይ ይቀመጣሉ።

-ሙሽሮቹ፡ ለፈጣሪያቸው፡ ለእግዚአብሔር ያደረጉት፡ ይህ የአምልኮ ስግደታቸው፡ አንዱ፡ ለአንድ አምላክነቱ ሲኾን፣ ሦስቱ ደግሞ፡ የሥላሴነት ቸርነቱ በኾነው፣ በሦስት ስም፥ በሦስት መልክና በሦስት ግብር ተገልጦ፡ በእግዚአብሔር አብእም'ነቱ [አባት-እናትነቱ]፣ በእግዚአብሔር ወልድነቱ [ልጅነቱ] እና በእግዚአብሔር መንፈስነቱ፡ ለፍጥረቱ፡ ለሚያበረክተው አገልግሎቱ የሚቀርብ ነው።

፫. **በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ሙሽራው እና ሙሽሪቷ፡ የእግዚአብሔር አብእም ልጆችና ካህናት ብቻ ሳይኾኑ፡ ንጉሥና ንግሥት መኾናቸው የሚታወጅበት ሥርዓትና ጸሎት፡ ከዚህ በታች ተያይዞ በሠፈረው መርሓ ግብር መሠረት፡ **"ኢትዮጵያ፡ አብጽሓት እደዊሃ ኀበ እግዝእተብሔርናሃ!** *ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔርነቷ አደረሰች!"* በሚለው መዝሙር፡ ልክ በተወሰነው፡ <u>ከማታው፡ በ፪ ሰዓት ተጀምሮ</u> ይካኼድና ይፈጸማል።

በቅዱሱ ቤተ-ኪዳን ውስጥ የሚካኼደው፡ ይኸው ጸሎትና ሥርዓት እንዳበቃ፡ አዲሶቹ ባለትዳሮች፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው፡ በቤተ መቅደሱ አንጻር በመስገድ፡ የዘለዓለም አባታቸውንና እናታቸውን፡ እግዚአብሔር አብእምን ተሳልመውና እግራቸውን ስመው፡ ተመርቀው ይሰናበታሉ።

፬፡ ሙሽራው እና ሙሽሪቷ፡ እንዲህ፡ በሰማያዊው ጸጋ ከብረውና በምድራዊው ውበት ደምቀው፥ **"ንሴብሖ ለእግዚአብሔር፡ ስቡሓ ዘተሰብሓ!** *በፍጥረቱ ዅሉ የተመሰገነ፣ ምስጉን እግዚአብሔርን፡ እኛም እናመሰግነዋለን!"* የሚለው የምስጋና ማሕሌታዊ ዜማ፡ በዕድምተኞቻቸው ኸብሸባ እየተዘመረ፡ በዚያው፡ በቤተ-ቅዱስ ኪዳኑ ውስጥ በተዘጋጀላቸው ዕልፍኝ ያርፋሉ።

ከጥቂት ዕረፍት በኋላ፡ ሚዜዎቹና ደንገጥሮቹ፡ ሙሽሮቹን ዐጅበዋቸው፡ የሙሽሮቹ ቤተሰቦች፡ ተክሊሉ በተፈጸመበት፡ በዚሁ ቤተ-ቅዱስ ኪዳን ወዳዘጋጁት የበዓለ-ፍልሰታ ፋሲካው ገበታ ግብዣ ያመራሉ።

በቃና ዘገሊላ የሠርግ በዓል ላይ የታደሙት፣ ያንንም በዓል የባረኩትና የቀደሱት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከዚህ በቀደመው ሥርዓተ-ተክሊልና ሥርዓተ-ቅዳሴ ላይ በመንፈስ-ቅዱስ ተገኝተው፡ ሥርዓታቱን እንደባረኩና እንደቀደሱ ኹሉ፡ አኹንም፡ እኒሁ፡ የፈጠሯቸውና የዘለዓለም ወላጆቻቸው የኾኑት እናት እና ልጅ፣ በዚህ የሠርግ በዓል ድግስ ላይ ተግኝተው፡ ይህን የምስጋና፣ የፋሲካ ገበታ እንደሚባርኩትና እንደሚቀድሱት፡ መሽሮቹና የሠርጋቸው ታዳሚዎች ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ኹሉ ያምናሉ።

፭. ሙሽሮቹ፡ እዚያ እንደደረሱ፡ በዚያ፡ ቀደም ብለው የተገኙት፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች የኾኑት፡ የሠርጉ ታዳሚዎች፡ ብድግ ብለውና ቆመው፡ **"መርዓዊ መጽአ፣ ወመርዓት መጽአት ተቀበሉ! መጽኡ በመንፈሰ ጽድቅ! እወ! ዘመጽኡ፣ ዘመጽኡ፡ በኪዳን ዘመብረቅ!** *እነሆ! ሙሽራው መጥቷልና፤ ሙሽሪቷም መጥታለችና፣ የመጡትም፡ በእውነት መንፈስ ነውና፣ ውጡና ተቀበሏቸው! አዎን! አመጣጣቸውም፡ በኪዳን መብረቅ ነው!"* በሚል ማሕሌታዊ የወረብ ዜማና ሽብሽባ ይቀበሏቸዋል።

-ይህ ማሕሌታዊ ወረብ፡ "**በኪዳን ዘመብረቅ!**" ማለትም፡ *"በኪዳን መብረቅ!"* በሚሉ ቃላት  የተደረሰው፡ "**እስመ ከመ መብረቅ፡ ዘይወጽእ እምጽባሕ፤ ወያስተርኢ እስከዐረብ፣ ከማሁ ምጽአቱ፡ ለወልደ-እጓለ-እመሕያው!** *ከምሥራቅ የወጣ መብረቅ፡ ወዲያው፡ እስከምዕራብ፡ በአንድ ጊዜ፡ እንደሚታይ፡ የማርያም ልጅ፡ የኢየሱስ መሲሕ ዳግም ምጽአቱም፡ እንዲሁ ነው!"* የሚለውን፡ መለኮታዊ ቃል ለማዘከርና በዚያ ላይ መመሥረቱን ለማሳየት ነው። (ማቴ. ፳፬፥ ፳፯፤ ፳፭፥ ፩-፲፫።)

፮. የሠርጉ ድግስ ማዕድ፡ በ"አቡነወእምነ-ዘበሰማያት፡ ተቀደሰ ስምከ!" በሚለው፡ የዜማ ጸሎት ተባርኮ፡ ግብዣው ይጀመርና፡ ለበዓሉ የሚስማማ የሙዚቃ ቃና እየተሰማ፣ እንዲሁም፡ "**ንግሥተ ሰማያት፥ ወምድር፡ ማርያም በቃላ! ተግህደ እግዝእናሃ፡ በቃና ዘገሊላ! የሰማይና የምድር ንግሥት ድንግል ማርያም፡ ቃሏ በኾነው ልጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፤ እግዝእተብሔር እም መኾኗ ተገለጠ!"** ደግሞም፡ **"በቃና ዘገሊላ! ከብካብ ኮነ! በቃና ዘገሊላ! ሠርግ ኾነ!"** በሚለው ማኅሌታዊ ወረብ ሲደምቅ፣ ተያይዞም፡ **"ሃሌ ሉያ ለአብወእም!"** የሚለውን የመሰለ፡ የቅዱሱ ኪዳን መዝሙር ቅኝት እየተደመጠበት ሲካኼድ ይቆያል።

-በማብቂያው ላይ፡ ስለሙሽሮቹ የሠርግ በዓል ደስታ መግለጫ፥ ይልቁንም፡ ይህን ኹሉ ላደረገው፣ ምግቡንና መጠጡንም አብዝቶ ለሰጠው፡ ለቸሩ ፈጣሪ እግዚአብሔር የሚቀርብ፡ የምስጋና ገጸ-በረከት አለ።

እሱም፡ የመልከ-ጻዴቅያዊው ኅብስትና ጽዋ [ጠበል-ጠዲቅ] ሥርዓት ኾኖ፡ "**ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ-ኢትዮጵያ! አንተ ሰጠቅህከ አፍላገ፣ ወአንቅዕተ! ለከ ውእቱ መዓልት፣ ወዘዚአከ፡ ይእቲ ሌሊት!** *ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ ንጉሥ የኾንኸው፣ በምድርም መካከል፡ መድኃኒትነትህን የገለጥህ አንተ እግዚአብሔርማ፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምግባቸውን ሰጠሃቸው! አንተ፡ ወንዞችንና ምንጮችን ከፋፈልህ! መዓልቱ፡ የአንተ ነው፤ ሌሊቱም፡ የአንተው ነው።"* በሚለው መዝሙር ይከፈትና፡ በስብሓቱ [የምስጋናው] ጸሎት ይጠናቀቃል። (መዝ. ፸፫፥ ፲፪-፲፮።)

፯. ከዚህ በማስከተል፡ በዚያ በተገኙት፡ በሙሽሮቹ ወላጆችና በቤተሰቦቻቸው አዛውንቶች፣ በኪዳናውያንና ኪዳናውያት የሠርጉ ታዳሚዎች፡ ምርቃት፥ በሙሽሮቹም ጉልበት መሳም፡ የማሰናበቻው ሥርዓት ይፈጸምና፡ ሚዜዎቹና ደንገጥሮቹ፡ ሙሽሮቹን፡ እስከ ጫጉላ ቤታቸው በማድረስ ይሸኟቸዋል።

በዚህ ሥርዓት፡ የሥርዓተ-ተክሊሉ እና የሥርዓተ-ቅዳሴው፣ የበዓለ-ፍልሰታ ፋሲካው ገበታ ግብዣም ፍጻሜ ኾኖ፣ በእግዚአብሔር አብእም፥ ወወልድ፣ ወመንፈስ-ቅዱስ አካል፣ ስምና ግብር ተጀምሮ፣ በእነርሱው ፍቅርና ሰላም፡ እስከዚህ ተካኺዶ፣ ለዚህ፡ ለፍጹሙ የምስጋናና የሓሤት ጣፋጭ ፍሬ በበቃው፣ በሠርጉ በዓል የረኩት የሙሽሮቹ ቤተሰቦች፣ ኪዳናውያቱና ኪዳናውያኑ የሠርጉ ታዳሚዎች፡ እርስ በርሳቸው በመሰነባበት፡ ኹሉም፡ በኪዳናዊው የቃና ዘገሊላ የሠርግ መንፈስ ተመልተው፡ ወደእየቤታቸው ይመለሳሉ።

# ክፍል ኹለት።

## በቤተ ክርስቲያን ተካኺዶ የሚፈጸመው ሥነ ሥርዓት፤

## *መግቢያ*

*ሥርዓቱንና ጸሎቱን የሚያካኺደው ካህን፡-*

*ከኹሉ አስቀድሞ፡ ሥርዓተ ተክሊሉ የሚፈጸምባቸውንና ለሙሽሮቹ የተዘጋጁትን የቃል ኪዳን ቀለበቶችና አልባሳት፥ የሚቀቡበትን ቅብዓ ቅዱስና የሚቀዳጁቸውን አክሊሎች፡ በቤተ መቅደሱ መንበር ፊት፡ በተዘጋጀው ጠረጴዛ ላይ ያኖራል፡፡*

*ሙሽራው እና ሙሽሪቷ፣ ዕድምተኞቻቸውም፡ ቦታ-ቦታቸውን መያዛቸውን ያረጋግጣል።*

*ስለመርሐ ግብሩ አጭር መግለጫን ይሰጣል።*

*ከዚህ በኋላ፡ ራሱንና አካባቢውን፡ በመስቀል አማትቦ፣ በዘንዜከሩንም አሥርቆ፥ የሥርዓተ ተክሊሉን አገልግሎት፡ እንዲህ በሚለው ሥርዓተ ጸሎት ይጀምራል፡-*

**በስመ እግዚአብሔር አብእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ! በምሥዋዐ-መድኃኒትናሃ፡ ለእግዝእትነ፥ ወለእምነ፣ ወለንግሥትነ ድንግል ማርያም፡ ወላዲተ አምላክ፥ በሰላመ- መስቀሉ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ!**

*አንድ አምላክ በኾነው፡ በእግዚአብሔር አብእም፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ስም፥*

*አምላክን በወለደች፡ በእግዝእተብሔራችንና እናታችን፣ ንግሥታችንም ድንግል ማርያም፡ በመድኃኒትነቷ ምሥዋዕነት [በማዳኗ መሠዊያነት]፣*

*በእግዚአብሔራችንና ፈጣሪያችን፣ ካህናችንና ንጉሣችንም ኢየሱስ መሲሕ፡ በመሰቀሉ ሰላም ቤዛነት፡ በተገኘው ኪዳነ ምሕረትነት አምነን፡*

**በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖቱ የጸና፡**
**የኪዳናዊ አክሊለ-ሰማዕትን [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽን]**
**እና**
**በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖቷ የጸናች፡**
**የኪዳናዊት ዕሴተ-ገብርኤልን [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷን]**

**የሥርዓተ ተክሊል ጸሎት እናደርሳለን።**

---

## የመክፈቻው ጸሎት፤

*"አአትብ ገጽየ" እያሉ፡ አራት ጊዜ በመስገድ ጸሎታቸውን ይጀምሩ:: ስግደቱ፡ ፩ዱ፡ ለእግዚአብሔር ለ፩ነቱ፥ ፫ቱ፡ ለ፫ነቱ ነው::*

**<u>በግእዝ፦</u>** "አአትብ ገጽየ፥ ወኵለንታየ፥ በትእምርተ መስቀል! በስመ እግዚአብሔር አብእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፥ በቅድስት ሥላሴ፡ እንዘ አአምን፥ ወእትመኀፀን፤ እክሕደከ ሰይጣን! በቅድመ ዛቲ፡ እምየ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ይእቲ፡ ስምዕየ፡ ማርያም ጽዮን፤ ለዓለም ዓለም::"

**<u>በኢትዮጵያኛ፦</u>** "ፊቴንና ኹለንተናዬን በመስቀል ምልክት እያማተብሁ፡ ልዩ በኾነች ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡ በእግዚአብሔር አብእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜና ተማጽኜ፡ እናቴና መጠጊያዬ፥ ምስክሬና የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ፊት፡ አንተን ሰይጣን ክጄሃለሁ! ለዘለዓለሙ::"

# ዋናው ጸሎት።

*ከዚህ ቀጥሎ፡ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ ቆመው፡ በሠራዒው ካህን መሪነትና በሕዝቡ ዕጀቢነት፡ እነዚህን፡ የኢትዮጵያን ልጆች የሃይማኖትና የቃል ኪዳን ጸሎቶች ከፍ ባለ ድምፅ በመድገምና በማሰማት ይጸልያሉ።*

| ግእዝ | ኢትዮጵያኛ |
|---|---|
| ጸሎተ ሃይማኖት፡ ዘኢትዮጵያ። | የኢትዮጵያ፡ የሃይማኖት ጸሎት። |
| ንሕነ፡ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡- | እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡- |
| ነአምን፡ በአሓዱ አምላክ፤ እግዚአብሔር ጸባዖት፤ አኀዜ ኵሉ፤ ገባሬ ሰማያት ወምድር፤ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ። | አንድ አምላክ በሚኾን፡ በአሸናፊው እግዚአብሔር እናምናለን።<br>እርሱም፡ ኹሉን የያዘው፣ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውንም የፈጠረው ነው። |
| ወነአምን፡ ከመ አሓዱ እግዚአብሔር ጸባዖት፡ ረሰየ ዋሕድናሁ ፍጹመ፡ በክዕበተ ህልውናሁ ዘእግዚአብሔር አብእም፣ ዘኮነ፡ በሥርዓተ ሰብሳብ መለኮታዊ። | አንድ አምላክ የኾነው፡ አሸናፊው እግዚአብሔር፡ ይህን አንድነቱን፡ እርሱ በሠራው፡ በመለኮታዊው የጋብቻ ሥርዓት፡ በእግዚአብሔር አብእም ኹለትነት፡ ፍጹም እንዳደረገው እናምናለን። |
| ወነአምን፡ በትሥልስተ አሓዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር ጸባዖት፣ ዘግህደ በተዋሕዶ ህላዌሃ፥ ወበአካላ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ እንተ ይእቲ፡ መንበረ እግዚአብሔር ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ፥ ወኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር። | የአንዱ አምላክ፡ የአሸናፊው እግዚአብሔር ሦስትነት፡ የእርሱው፡ የአሸናፊው እግዚአብሔር ቅድስት ሥላሴ ዙፋንና የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ የተዋሕዶ አኗኗርና አካል እንደተገለጠ እናምናለን። |
| ወነአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አሐዱ እግዚእ፥ ወልድ ዋሕድ፡ እምእግዚአብሔር አብእም፥ ዘህልው ምስሌሁ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም። | ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የእግዚአብሔር አብእም ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። |
| ውእቱ ኢየሱስ መሲሕ፥ ብርሃን፡ ዘእምብርሃን፥ አምላክ፡ ዘእምአምላክ፡ ዘበአማን፤ ዘተወልደ፡ ወአኮ ዘተገብረ፥ ዘዕሩይ ምስለ እግዚአብሔር አብእም፡ በመለኮቱ። | እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ፡ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከእግዚአብሔር አብእም ጋራ የሚተካከል ኢየሱስ መሲሕ ነው። |

ዘቦቱ፡ ኵሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ፡ አልቦ ዘኮነ፥ ወኢምንትኒ፥ ዘበሰማይኒ፥ ወዘበምድርኒ።

ዘበእንቲአነ ለሰብእ፥ ወበእንተ ሰላምነ፡ ወረደ እምሰማያት፤

ተሰብአ፤ ወተሠገወ፤ ወኮነ፡ ብእሴ ፍጹመ፡ በነሢአ ሥጋ፡ እምሥጋሃ፥ ወነፍስ፡ እምነፍሳ፤ ወመንፈስ፡ እምመንፈሳ፤ እምማርያም፡ እምቅድስት ድንግል፡ ዘተዋሓደት እግዝእተብሔር እም፡ ለመድኃኒትነ፡ በግብረ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ ዘበቅድም።

በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፡ ተሰቅለ፤ ወሓመ፥ ወሞተ፤ ወተቀብረ በእንቲአነ።

ወሞአ ለዲያብሎስ፡ አቡሆሙ፡ ለሓሰት፡ ዘተሰይመ "ኃጢአት"፥ ወለእከይ፥ ወለሞት፥ ወለሙስና መቃብር።

ወተንሥአ እሙታን፡ አመ ሣልስት ዕለት።

ዐርገ በስብሓት፡ ውስተ ሰማያት። ወነበረ፡ በየማነ እግዚአብሔር አብእም፥ በመንበሩ ዘበዕሪና።

ዳግመ መጽአ፡ በህላዌሁ ዘመንፈስ ቅዱስ፣ በከመ አሰፈዎሙ ለአርዳኢሁ፣ ወአስተቄጸለ ቀዳሚት ትንሣኤ ሕይወት ዘመንፈስ፡ ለደቂቀ-ኢትዮጵያ፡ ብፁዓን ወብፁዓት፥ ቅዱሳት ወቅዱሳን።

ወይመጽእ በትንሣኤ አካሉ ወበስብሓቲሁ፡ ለኵሉ ፍጥረት ዕልው፡ ዘኵሎን ዓለማት፤ ይኰንን፡ ሕያዋነ፥ ወሙታነ።

ወአልባቲ ማኅለቅት ለመንግሥቱ፡ ዘተሰምየት፡ "ኢትዮጵያ"።

በእርሱም፡ ኹሉ ኾነ። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን የኾነ የለም።

ስለእኛ ስለሰዎች፥ ስለሰላማችን፡ ከሰማይ ወረደ። እግዝእተብሔር-እም፡ ስለመዳናችን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ግብር ከተዋሓደቻት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋን፥ ከነፍሷም፡ ነፍስን፣ ከመንፈሷም፡ መንፈስን ነሥቶ፡ ፍጹም ሰውን ኾነ።

በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ።

"ኃጢአት" የተባለው፡ የሓሰት፣ የክፋትና የሞት፣ የመቃብር-መበስበስም አባት የኾነውን ዲያብሎስን፡ ድል አደረገው።

በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ።

በእግዚአብሔር አባቱና እናቱም ቀኝ፡ በእኩያ ዙፋኑ ተቀመጠ።

ለደቀ-መዛሙርቱ የሰጣቸውን የተስፋ ቃሉን በመፈጸም፣ በመንፈስ ቅዱስ ህልውናው ተመልሶ መጣ። የመጀመሪያዋን መንፈሳዊት የትንሣኤ ሕይወትም፡ ለብፁዓንና ለብፁዓት፣ ለቅዱሳትና ለቅዱሳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ አቀዳጀ።

በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድም፡ በትንሣኤ አካሉና በክብሩ ምስጋና፡ ለመላው ከሃዲ፡ የዓለማቱ ኹሉ ፍጥረት፡ ዳግመኛ ይመለሳል።

"ኢትዮጵያ" ለተባለችው መንግሥቱም፡ ፍጻሜ የላትም።

| | |
|---|---|
| ወነአምን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ። ውእቱ መንፈሰ ጽድቅ፤ ማኅየዊ ዘበአማን፤ ዘሠረፀ እምእግዚአብሔር አብእም፤ ወዘይነብር በመንበሩ ዘበዕሪና፣ በፀጋመ እግዚአብሔር አብእም፣ ዘንሰግድ ሎቱ፥ ወንሰብሖ፡ ምስለ እግዚአብሔር አብእም፥ ወእግዚአብሔር ወልድ። | በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። <br> እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጠው እና ከእግዚአብሔር አብእም የሠረፀው፤ በእግዚአብሔር አብእም በስተግራ ባለው፡ የእኩያ ዙፋኑ የተቀመጠው፣ ከእግዚአብሔር አብእም እና ከእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ጋር፡ የምንሰግድለት፣ የምናመሰግነውም፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። |
| ዘነበበ በነቢያት፤ ወዘወረደ ላዕለ ሐዋርያት፤ ወጸጋሁ፡ ዘመልአ ዓለመ፡ በምሥዋዐ መድኃኒትናሃ፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወበቤዛ ሰላመ-መስቀሉ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ። | በነቢያት ዐድሮ የተናገረው እና በሐዋርያት ላይ የወረደው፣ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ የማዳኗ ምሥዋዕነት እና በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የመስቀሉ ሰላም ቤዛነት፡ ዓለሙን፡ በጸጋው የሞላው፡ እርሱ ነው። |
| ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ይእቲ፡ ዘመሠረታ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እምጥንት፡ በኪዳነ ልቦና፡ ዘሰብአት ቀደምት፥ ወዘአጽንዓ፡ በቃለ ነቢያት፥ ወዘፈጸማ፡ በላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት። <br> በውስቴታ፡ ያቁርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ እምእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፤ ወባቲ ይትዌከፉ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡ ኪዳናውያን ወኪዳናውያት፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ዘዘዚአሁ። | እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ጥንት፡ በቀደሙት ሰዎች ኪዳነ ልቦና በመሠረታት፡ በአንዲት ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እናምናለን። እርሷም፡ በነቢያት ቃል ያጸናት እና በሐዋርያት ጉባኤ የፈጸማት፥ ካህናት፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣውን፡ የእርሱን፡ የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለመሥዋዕትነት የሚያቀርቡባት፥ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆችም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋዎች የሚቀበሉባት ናት። |
| ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት፡ ዘረከብናሃ፡ እምእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ ወበእሳት፡ ለስርየተ ኃጢኣት። | ኃጢአት በሚሰረይባት፥ ከእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት በተቀበልናት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን። |
| ወነአምን፡ በትንሣኤ ሙታን፤ ወሕይወተ፡ ዘለዓለም። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን። | በሙታን ትንሣኤ፥ በዘለዓለምም ሕይወት እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን። |

## ጸሎተ ኪዳነ ቃል፡ ዘኢትዮጵያ።

**ንሕነ፡ ደቂቀ ኢትዮጵያ፡-**

ነአምን በኢትዮጵያውናነ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፥ ህልው በዓቂበ ቃላት ኪዳናውያት፥ እለ ወሀቦን እግዚአብሔር፡ ለውሉድ ወአዋልድ፡ ዘሰብእ።

አምላክነ፡ ሣረረ ዝንቱ ሰብእና ኢትዮጵያዊ፥ ወኢትዮጵያዊት፡ በኪዳነ ልቦና፡ በዘኮነ እምሥርዓተ ሰብሳብ፡ ዘአዳም፥ ወሔዋን፡ በዘመነ ፍጥረት ቀዳማዊ፤ ወመትሎሁ፡ አዕረጎ ለዝ ሕያው ሕንጻ ዘሰብአት፡ በቀስተ ደመናሁ፡ ለኖኅ፥ ወበቍርባኑ፡ ዘመልከ-ጼዴቅ፥ ወበግዝረቱ፡ ዘአብርሃም፤ ወበዘመነ ሕግ ማእከላይ፡ ነደቆ ማኅፈዱ፡ በጽላተ ሙሴ፥ ወበመንበረ ዳዊት፡ ዘግህደ በፅምረተ አሥራወ- ዘርያሙ፡ ለንግሥት ማክዳ ኢትዮጵያዊት፥ ወለንጉሥ ሰሎሞን እስራኤላዊ፣ ከመ ያስተሰነአዎ ኵለንታሁ፡ በኪዳነ ኦሪት።

ወእምድኅረ አጽንዖቱሰ፡ በሥጋሁ ወደሙ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ፥ ወዘተወልደ እምእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ እንተ ሠረፀት፡ እምዛቲ ሥርው ምልእት፡ አስተቄጸሎ አክሊል ዘለዓለም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ ዘሕይወት፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ።

በእንተዝ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ገዝፈት፡ በሰብእናሁ ለኢትዮጵያዊ፥ ወበሰብእናሃ ለኢትዮጵያዊት፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ እንዘ በኀቤሁ፥ ወበኀቤሃ፡ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፡ በአሠረ ተዋሕዶ።

## የኢትዮጵያ፡ የቃል ኪዳን ጸሎት።

**እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡-**

እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች፣ ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም፣ የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን።

አምላካችን፡ ይህን የኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያዊት ሕያው ሰውነት፡ **በመጀመሪያው የፍጥረት ዘመን፡** በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ **በኪዳነ ልቦና መሠረተው፤**

ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቍርባን እና በአብርሃም ግርዛት፡ **ገንብቶ አሳደገው፤**

**በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡** በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፥ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእስራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሓድ፡ **በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤**

**በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡** ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የተወለደው፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእርሷ በነሣው ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው።

ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው እና ኢትዮጵያዊቷ ሰውነት ገዝፋ፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷን እና ቤተ ምልክናዋን፡ በምስጢረ-ተዋሕዶ፡ አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።

ነአምን፡ ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ "ክርስቲያን"፡ በስመ ዚአሁ፡ ዘተብህለ "ክርስቶስ"፡ ከመ ውእቱ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ካህንነ፥ ወንጉሥነ ዘለዓለም፡ በሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፡ ዘአስተርአየ በመዋዕል ቀዳማዊ፤ ወዘኮነ አርአያሁ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፤ በልደቱ ዘኮነ እምትሥልስተ ዘርዕ፡ ዘእምአንጋደ ሴም፥ ወካም፥ ወያፌት።

ነአምን፡ ንሕነ፡ እለ ተሠየምነ፡ "ደቂቀ ኢትዮጵያ"፡ በስመ ዚአሃ፡ ዘተብህለት፡ "ኢትዮጵያ"፡ ከመ ይእቲ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ዕፀ ሕይወት፥ ወእመ-ሕያዋን አማናዊት፥ ወታቦተ ጽዮን ዘለዓለማዊት፥ ወንግሥተ-ሰማያት ወምድር፡ በዘወሊዶታ ለእግዚአብሔር ጸባዖት።

ነአምን፡ በቀስተ ደመና፡ ዘተሠርገወ፡ በሠለስቱ ዓበይት ኅብረ ቀለማት፡ ዘውእቶን፡ ሓመልሚለ፥ ወወርቀ፥ ወቀይሓ፡ ዘተውህበ ለነ እምእግዚአብሔር ፈጣሪነ፡ እንተ በኀበ ኖኅ፡ በዘሕዝብናነ ዘኪዳን ቅዱስ፤ ከመ ውእቱ ይኩነነ፡ ትእምርተ ኪዳን ዘለዓለም።

ነአምን፡ በማኅተምነ ዘለዓለም፡ ዘረከብነ፡ እምእግዚአብሔር አምላክነ፡ በዘሕዝብናነ ዘኪዳን ቅዱስ፤ ወበዘውእቱ ዘተነግረ፡ በእንተ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፤ በቃለ ትንቢት፡ እንዘ ይብል፡ **"ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"**፤ ወበእንተ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ መፈጽም ለኪዳኑ ቅዱስ፡ በዝንቱ ቃል ዘመለኮት፡ እንዘ ይብል፡ **"ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!"**።

እርሱ፡ "ክርስቶስ" ተብሎ፡ እኛን፡ "ክርስቲያን" ያሰኘን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በቀደመው ዘመን፡ ለእርሱ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካም እና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን።

እርሷ፡ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ያሰኘችን፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ አሸናፊውን እግዚአብሔርን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕይወት ዛፍ፥ የሕያዋን እናትና፥ ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን።

በሦስቱ ታላላቅ ኅብረ-ቀለማት፡ በአረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ያሸበረቀው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነታችን፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከፈጣሪያችን እግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን።

ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የተነገረው፡ **"ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!"** የሚለው ትንቢታዊ ቃል እና የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የተነገረው፡ **"የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!"** የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነታችን፡ ከአምላካችን እግዚአብሔር ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን።

| | |
|---|---|
| ነአምን፡ ከመ ንሕነ፡ ወራስያነ መንግሥቱ፥ ወካህናቲሁ ለእግዚአብሔር፡ በእንተ ወልድናነ፡ በዘውእቱ ዘተከለልነ፡ በክብረ ልደት እምእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስ፣ ወበእሳት፡ እንበይነ ጸጋሁ፡ ዘኪዳኑ ቅዱስ። | በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት የመወለድን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ ልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች [ነጋሾች] እና ካህኖች [አገልጋዮች] እንደኾንን እናምናለን። |
| ነአምን፡ ከመ ብነ ይደልወነ፡ ንሄሉ በንስሓ፡ እንበለ ፅርዓት፡ ለስርየተ ኃጢአት፥ ወበተመጥዎተ ሥጋሁ፥ ወደሙ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ እምእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ለአጽንዖተ ዝንቱ ወልድናነ፥ ወለትውክልተ ውርስናነ ዘመንግሥቱ፥ ወለዝልፈተ ተልእኮትነ ንጹሕ። | ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን፡ ለማረጋገጥ እና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፣ኃጢአታችንን፡ ዘወትር በንስሓ እያጠራን፣ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣውንም ሥጋና ደም እየተቀበልን፡ መኖር እንዳለብን እናምናለን። |
| ነአምን፡ ከመ ውእቱ ሃይማኖትነ ዘኢትዮጵያውና፡ ገሃደ ይወጽእ፥ ወቅድስናሁ ይትአወቅ በምግባሪነ፡ ዘኢትዮጵያውና፡ ዘንፈጽም፡ በተዋሕዶተ ፍቅርነ፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ። | የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና ለእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ባለን የተዋሐደ ፍቅር ኾነን፡ በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን። |
| ነአምን፡ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ፡ ዘጸሓፈ ኢትዮጵያውናነ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ በልቦናነ፤ ወዘመሀረነ፤ ወዘረሰየነ፡ ንዕቀቦ በሀልዎትነ፡ በእንተ ቃለ ኪዳኑ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን። | የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን የጻፈው፣ ያስተማረንም፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን። |

*"ሰላም ለኪ!"ን፡ አንድ ጊዜ ሰግደው፡ ከ"ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም" ጋር ይጸልዩ!*

## <u>ሰላም ለኪ፦</u>

ሰላም ለኪ! እንዘ ንሰግድ ንብለኪ! ማርያም እምነ! ነአኵተኪ፥ እምአርዌ ነዓዊ፡ ተማሕፀነ፣ ወድኅንነ ብኪ፤ በእንተዝ ተወለድኪ እምሐና እምኪ፤ ወኢያቄም እምአቡኪ፤ በዓለ ፍልሰትኪ፥ ወከብካበ ደቂቅኪ ዘአክሊለ-ሰማዕት ወዘዕሴተ-ገብርኤል፡ ዮም፤ ድንግል ባረክኪ ምስለ ፍቁር ወልድኪ!

## <u>ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ።</u>

ተዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር፤ ወትትሐሠይ መንፈስየ፡ በአምላኪየ ወመድኃኒየ፤ እስመ ርእየ ሕማማ ለዓመቱ:: ናሁ እምይእዜሰ፥ ያስተበፅዑኒ፥ ኵሉ ትውልድ፤ እስመ ገብረ ሊተ፥ ኃይለ ዓቢያተ:: ወቅዱስ ስሙ:: ወሣህሉኒ፡ ለትውልደ ትውልድ፥ ለእለ ይፈርኅዎ:: ወገብረ ኃይለ በመዝራዕቱ፤ ወዘርዖሙ፡ ለእለ የዓብዩ ሕሊና ልቦሙ፤ ወነሠቶሙ ለኃያላን፡ እመናብርቲሆሙ:: አዕበዮሙ፡ ለትሑታን፤ ወአጽገቦሙ፡ እምበረከቱ ለርኁባን:: ወፈነወ ዕራቆሙ ለብዑላን:: ወተወክፎ ለእስራኤል ቍልዔሁ፤ ወተዘከረ ሣህሎ፡ ዘይቤሎሙ፤ ለአበዊነ፥ ለአብርሃም፤ ወለዘርዑ፤ እስከለዓለም::

## <u>ሰላም ለኪ፦</u>

እናታችን ማርያም ሆይ! "ሰላም ላንቺ ይኹን!" እያልን፡ እንሰግድልሻለን! እናወድስሻለንም! ተማፅነንብሽ፡ ከክፉው አውሬ፡ ከዲያብሎስ አዳንሽን! ከእናትሽ ከሓና፥ ከአባትሽ ከኢያቄምም የተወለድሽልን፡ ስለዚሁ ነውና! ድንግል ሆይ! እነሆ ዛሬ፡ ከልጅሽ፥ ከወዳጅሽ ጋር፡ በመካከላችን ተገኝተሽ፡ የፍልሰትሽን በዓላችንን፣ የልጆችሽን፥ የአክሊለ-ሰማዕትንና የዕሴተ-ገብርኤልንም የጋብቻ ሠርግ ባረክሽልን!

## <u>የአምላክ እናት፡ የእግዝእተብሔር ድንግል ማርያም ጸሎት።</u>

በአዲሱ ኪዳን፡ የምሥራች ቃል፡ "ማርያምም አለች" የሚለውን፡ ያንቺን ጸሎት፡ እናቀርብልሽ ዘንድ፡ እናታችን ድንግል ሆይ! ፈቀድሽልን! "ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን በታላቅ ክብር ታመሰግነዋለች፤ መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ እጅግ ደስ ይላታል፤ የእኔን የአገልጋዩን ፈተናና መከራ አይቷልና:: እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ፡ "ብፅዕት!" ይሉኛል፤ እርሱ፡ ለእኔና በእኔ፡ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓልና:: ስሙ፡ ቅዱስ ነው:: እርሱን በሚወድዱት ዘንድ፡ ምሕረቱ፡ ለልጅ ልጅ ይኖራል:: ታላላቅ ሥራዎቹን፡ በክንዱ ያደርጋል:: በዕውቀታቸው የታበዩትን፡ በታተናቸው! በኃይላቸው የተመኩትን፡ ከሥልጣናቸው አወረዳቸው! የተዋረዱትንም፡ ከፍ ከፍ አደረጋቸው! የተራቡትን፡ ከበረከቱ አጠገባቸው! በሀብታቸው የታመኑትን፡ ዕርቃናቸውን ሰደዳቸው! ብላቴናውን እስራኤልን ተቀበለ፤ ለቀደሙ የቅዱሱ ኪዳን ወንድሞቻችን እና እኅቶቻችን፥ ለአብርሃም እና ለሣራ፣ ለዘሩም፡ እስከዘለዓለም የገባውን፡ የቃል ኪዳን ምሕረቱን አስታወሰ::"

*ይህን ከጸለዩ በኋላ፡ ኢያይዘው፡ የዕለቱን "ውዳሴ ማርያም" በተራ እየተቀባበሉ በመድገም፡ በ"አቡነ ዘበሰማያት" እና በ"ኦ ማርያም እምነ!" ያጠቃልሉ።*

| | |
|---|---|
| **አቡነ ዘበሰማያት!**<br><br>አቡነ ዘበሰማያት! ተቀደሰ ስምከ። መጽአት መንግሥትከ። ኮነ ፈቃድከ፡ በከመ በሰማይ፥ ከማሁ፡ በምድር። ሲሳየነ ዘለለዕለትነ፡ ሀብከነ ዮም። ኅደግከ ለነ፡ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፤ ከመ ንሕነኒ፡ ንኅድግ፡ ለዘአበሰ ለነ። ኢታብአነ፡ እግዚኦ ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅንከነ፤ ወባልሓከነ፡ እምኵሉ እኩይ። እስመ ዚአከ፣ ይእቲ መንግሥት፤ ኃይል፤ ወስብሓት። ለዓለመ ዓለም። አሜን።<br><br>**እምነ ዘበሰማያት!**<br><br>ኦ ማርያም እምነ ዘበሰማያት! ሰላም ለኪ! በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ።<br>ድንግል በመንፈስኪ፣ ወበነፍስኪ፣ ወበሥጋኪ። እመ እግዚአብሔር ጸባዖት፡ ሰላም ለኪ! ቡርክት አንቲ እምአንስት፤ ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ። ተፈሥሒ፡ ፍሥሕት! ኦ ምልእተ ጸጋ! በእግዝእተብሔር እም'ናኪ ወበምሥዋዐ መድኃኒትናኪ፥ ወበቤዛ ሰላመ-መስቀሉ፡ ለፍቁር ወልድኪ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ገበርኪ ለነ፡ ምሕረተ ዘለዓለም። ወሰረይኪ ለነ፡ ኃጣውኢነ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን። | **የሰማያት አባታችን ሆይ!**<br><br>አባታችን ሆይ! በሰማያት የምትኖር! ስምህ ተቀደሰ። መንግሥትህ መጣች። በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ኾነ። የዕለት ምግባችንን፡ ለዛሬ ሰጠኸን። ኃጢአታችንንና በደላችንን ይቅር አልኸን፤ እኛም፡ የበደሉንን፡ ይቅር እንል ዘንድ። አቤቱ፡ ወደፈተና አላገባኸንም፤ ከክፉው ኹሉ፡ አዳንከን፥ ታደግኸን እንጂ። ይህች መንግሥት፥ ኃይልና ምስጋናም፡ የአንተ ናቸው። ለዘለዓለሙ። አሜን።<br><br>**የሰማያት እናታችን ሆይ!**<br><br>እናታችን ማርያም ሆይ! በሰማያት የምትኖሪ! በመልአኩ፡ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ "ሰላም!" እንልሻለን። በመንፈስሽ እና በነፍስሽ፣ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ሆይ! ሰላምታ፡ ለአንቺ ይገባል። ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ አንቺ፡ የተመሰገንሽ ነሽ። የማሕፀንሽም ፍሬ፡ የተመሰገነ ነው። የደስታ ምንጭ፥ ጸጋንም የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ! በእግዝእተብሔር እናትነትሽና በምሥዋዐ መድኃኒትነትሽ፣ በተወደደው ልጅሽ፡ በኢየሱስ መሢሕ የሰላመ-መስቀሉም ቤዛነት፡ የዘለዓለም ምሕረትን አደረግሽልን። ኃጢአታችንንም፡ አስተሰረይሽልን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን። |

# ክፍል ሦስት፤

## የጋብቻ ቃል ኪዳንን የመፈጸም ሥርዓት።

*እነዚህ ጸሎቶች ተደርገው እንዳበቁ፡ ኹለቱ ሙሽሮች፡ ሰው ኾኖ፡ ዓለሙን ላዳነውና ካህን ንጉሣቸው ለኾነው አምላካቸው ኢየሱስ መሲሕ ያላቸውን የአምልኮ ታማኝነት፥ እንዲሁም፡ ዘላለማዊት ንግሥትና ሕያውት ጽላተ ኪዳን ለኾነችው፡ ለቅድስት እናቱ፡ ለድንግል ማርያም ያላቸውን የፍቅር ፍጹምነት በማረጋገጥ ለማሳየት፡ ተንበርክከውና ከአንገታቸው ተጎንብሰው፡ ከኃጢኣት፡ በንስሓ ስለመፈታት፡ ይህን የኑዛዜ ጸሎት፡ በቅድሚያ፡ በእየራሳቸው ያደርሳሉ፡-*

እግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ካህን፡ ሊቀ ካህናት፥ ንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥት፥ ሰራዬ ኃጢኣት፥ ወደምሳሴ አበሳ፥ መፍቀሬ ንስሓ፥ ወሀቤ ጸጋ፡ ሥልጣነ ዘወሀብኮሙ ለሓዋርያት፥ ወለእለ የአምኑ ብከ፤ በዘአእመረ መንፈስ ቅዱስ፡ ከማሁ ሰረይከ ለነ ኃጢኣተነ ዘገበርነ፡ ንሕነ ደቂቀ ኢትዮጵያ፣ እምንእስነ እስከይእዜ፥ ውሉድ ወአዋልድ፡ ዘኪዳንከ ቅዱስ፡ ካህናተ እግዚአብሔር፣ ነጋሥያነ ወነጋሥያተ በበስምነ፡ ኲንነ ፍቱሓነ፥ ወንጹሓነ፣ ረሰይከነ ድልዋነ፡ ለንስሓከ፥ ወለቃል-ኪዳንከ፥ ለቅዱስ ሥጋከ፥ ወለክቡር ደምከ፥ ወለመንግሥትከ፤ "እግዚኦ መሓርከነ ኢየሱስ መሲሕ!" (፲፪ ጊዜያት!) "ኦ ማርያም መሓርኪ ለነ!" (፲፪ ጊዜያት!)

ይትባረክ ወይሴባሕ፡ ኄር እግዚአብሔር! እስመ ፈትሓነ እምኵሉ ኃጢኣት፡ ዘገበርነ በኀልዮ፥ በነቢብ፥ በገቢር፡ በምሥዋዐ-መድኃኒትናሃ ለእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፣ ወበቤዛ መስቀለ-ሰላሙ ለኢየሱስ መሲሕ፤ ለዓለም ዓለም፤ አሜን።

ፈጣሪያችን፥ አምላካችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፥ ካህን፡ ሊቀ ካህናት፥ ንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥት፥ ኃጢኣትን ያስተሰረይህ፥ በደልን የደመሰስህ፥ ንስሓን የምትወድ፥ ጸጋህን ያደልህ፥ ለሓዋርያት፣ ላመኑብህም ኹሉ፡ ይህን ሥልጣንህን የሰጠሃቸው፥ መንፈስ ቅዱስ ባወቀ፡ ከልጅነት እስከዛሬ፡ የሠራነውን ኃጢኣታችንን ኹሉ አስተሰረይህልን!

በቅዱሱ ኪዳን የእግዚአብሔር ልጆችና አገልጋዮች፣ ነጋሢዎችም የኾንን፡ እኛን፡ የኢትዮጵያን ወንዶችና ሴቶች ልጆች፡ በየስማችን፡ ከየኃጢኣታችን፡ የተፈታን፡ ንጹሓን እንድንኾን፣ ኹላችንንም፡ ለንስሓና ለቃል ኪዳንህ፥ ለሥጋ-ወደምህና ለመንግሥትህ፡ የበቃን ኾነን እንድንገኝ አደረግኸን። ስለዚህ፡ (፲፪ ጊዜያት)፡ "አቤቱ ኢየሱስ መሲሕ! ይቅር አልኸን!" እያልን፣ እንዲሁም፡ (፲፪ ጊዜያት)፡ "ድንግል ማርያም ሆይ! ይቅር አልሽን!" እንላለን።

በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም መድኃኒትነትና በኢየሱስ መሲሕ፡ የሰላም መስቀሉ ቤዛነት፡ በማሰብ፥ በመናገር፥ በማድረግም፡ ከሠራነው ኃጢኣት ኹሉ፡ ቸሩ እግዚአብሔር ስለፈታን፡ ክብርና ምስጋና ይገባዋል። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## የተክሊል ጋብቻ ቃል-ኪዳን

*ሠራዒው ካህን፡ ኹለቱም ሙሽሮች፡ ወደፊት ቀረብ ብለው፡ የቅዱሱ ኪዳን አምላክ፡ የልዑል እግዚአብሔርና የቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም መንበር ባለበት አግጣጫ እንዲቆሙ ይጋብዛቸዋል።*

*ወዲያው፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ እርስ በርሳቸው፡ ዘወር ብለው በመተያየትና በጎናቸው ባለው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን መጽሐፍ ቅዱስ በመመልከት፡ እነዚህን ተግባራት እያካኼዱ ይፈጽማሉ፡- በመጀመሪያ፡ሙሽራው፡ የሙሽራዪቱን እጆች፡ በእጆቹ ይዞና ዓይኖቿን አቅንቶ እያየ፥ ሠራዒው ካህን፥ ወይም፡ ከእርሱ ረዳቶች፡ አንዱ እያገዘው፡ ከዚህ የሚከተለውን ቃል ኪዳን ያሰማል፡-*

**“እኔ፡ አክሊለ-ሰማዕት [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ]፡ በፍጹም ልቦናዬ፡ አንቺን ዕሴተ-ገብርኤልን [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷን] ስለወደድሁሽ፡ ከዚህች ቀንና ከዚህች ሰዓት ጀምሮ፡ ሚስት ትኾኚኝ ዘንድ፥ ከእኔም ጋር፡ በሥጋ ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስና በመንፈስ ህልውና ጭምር፡ ትኖሪ ዘንድ፡ ተቀብዬሻለሁ፡፡**

**“ስለዚህ፡ ኹልጊዜም፡ በተቻለኝ ኹሉ፡ መልካም እና እውነት የኾነ ፍላጎትሽን እፈጽማለሁ፤ በበጎ ኾነ፡ ወይም፡ በክፉ ቀን፥ በብልጽግናም ኾነ፡ በችግር፥ በሕመም ኾነ፡ በጤንነት፥ በሕይወት ኾነ በሞት ምክንያት፡ በማናቸውም ዓይነት ኹኔታ፡ በአጠገብሽ እገኛለሁ እንጂ፡ ከአንቺ፡ ፈጽሞ አልለይም፤**

**በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት፡ እንደተቀደሰችው፡ እንደፈጣሪያችን መመሪያ፡ ከአንቺ ጋራ፡ ዛሬ ያደረግሁትን የጋብቻ ቃል ኪዳኔን፡ በታማኝነት፡ ለዘለዓለም አጸናለሁ፡፡”**

*ቀጥላም፡ ሙሽራዪቱ፡ የሙሽራውን እጆች፡ በእጆቿ ይዛና ዓይኖቹን አቅንታ እያየች፥ ሠራዒው ካህን፥ ወይም፡ ከእርሱ ረዳቶች፡ አንዱ እያገዛት፡ ከዚህ የሚከተለውን ቃል ታሰማለች፡-*

**“እኔ፡ ዕሴተ-ገብርኤል[ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]፡ አንተን፡ አክሊለ-ሰማዕትን [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽን]፡ በፍጹም ልቦናዬ ስለወደድሁህ፡ ከዚህች ቀንና ከዚህች ሰዓት ጀምሮ፡ ባል ትኾነኝ ዘንድ፥ ከእኔም ጋር፡ በሥጋ ብቻ ሳይኾን፡ በነፍስና በመንፈስ ህልውና ጭምር ትኖር ዘንድ፡ ተቀብዬሃለሁ፡፡**

**“ስለዚህ፡ ኹልጊዜም፡ በተቻለኝ ኹሉ፡ መልካም እና እውነት የኾነ ፍላጎትህን እፈጽማለሁ፤ በበጎ ኾነ፡ ወይም፡ በክፉ ቀን፥ በብልጽግናም ኾነ፡ በችግር፥ በሕመም ኾነ፡ በጤንነት፥ በሕይወት ኾነ በሞት ምክንያት፡ በማናቸውም ዓይነት ኹኔታ፡ በአጠገብህ እገኛለሁ እንጂ፡ ከአንተ፡ ፈጽሞ አልለይም፡፡**

**“በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓት፡ እንደተቀደሰችው፡ እንደፈጣሪያችን መመሪያ፡ ከአንተ ጋራ፡ ዛሬ ያደረግሁትን የጋብቻ ቃል ኪዳኔን፡ በታማኝነት፡ ለዘለዓለም አጸናለሁ፡፡”**

# የተክሊላዊው ጋብቻ ቃል ኪዳን፡ ማስተማመኛና ማረጋገጫ።

*አኹን ደግሞ፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ እያንዳንዳቸው፡ በየተራ፡ የቀኝ እጃቸውን፡ መስቀል ባረፈበት፥ ቅዱሳት ኪዳናትንም አካትቶ በያዘው፡ በቅዱሱ መጽሓፍ ላይ እያኖሩ፡ ቀደም አድርገው ለተለዋወጡት፡ የእርስ በርስ ተክሊላዊ የጋብቻ ቃል ኪዳን፡ ታማኞች ኾነው የሚኖሩ ለመኾናቸው የሚያሳውቁበትን ማስተማምኛና ማረጋገጫ፡ እንዲህ በሚል የስምምነት ቃላቸው ያጸኑታል፦*

“እኔ፡ ስመ ክርስትናዬ፡ አክሊለ-ሰማዕት የኾነ፡ ኪዳናዊ አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ፣ ስመ ክርስትናዋ፡ ዕሴተ-ገብርኤል የኾነውን፡ ኪዳናዊት ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷን፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ በአዳምና ሔዋን በመሠረተውና በቀደሰው፡ በቅዱሱ ኪዳን የጋብቻ ቃል ኪዳን፡ ሚስቴ፡ ትኾን ዘንድ ተቀብያታለሁ፡፡

“በዚህ ቃል ኪዳኔ፡ ለእርሷ፡ በባልነቴ፥ ደግሞም፡ እግዚአብሔር፡ በቸርነቱ፡ ከእርሷ፡ ለሚሰጠኝ ልጆች፡ በወላጅነቴ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖቴ፡ ከእኔ የሚጠይቀውን፡ ማናቸውንም አደራና ኀላፊነት፥ ተግባርና ግዳጅ እፈጽማለሁ፡፡

“በፈጣሪያችንና በሰላማችን፥ በካህን፡ ሊቀ ካህናታችንና በንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥታችን፡ በኢየሱስ መሲሕ እና በሃይማኖታችንና በመድኃኒታችን፥ በእናታችንና በንግሥታችን፥ በአገራችንም፡ በድንግል ማርያም ዙፋን ፊት፡ ይህን፡ የጋብቻ ቃል ኪዳን የሰጠሁት፡ በፍጹም ዕውቀትና እምነት፥ ፍላጎትና ፈቃደኛነት፥ እውነተኛነትና ቊርጠኛነት መኾኑን አረጋግጣለሁ፡፡”

*ቀጥሎ፡ የሙሽራዋ የስምምነት ቃል፦*

“እኔ፡ ስመ ክርስትናዬ፡ ዕሴተ-ገብርኤል የኾነ፡ ኪዳናዊት ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ፡ ስመ ክርስትናው፡ አክሊለ-ሰማዕት የኾነውን፡ ኪዳናዊ አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽን፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ በአዳምና ሔዋን በመሠረተውና በቀደሰው፡ በቅዱሱ ኪዳን የጋብቻ ቃል ኪዳን፡ ባሌ፡ ይኾን ዘንድ ተቀብዬዋለሁ፡፡

“የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖቴ፡ በዚህ ቃል ኪዳኔ፡ ለእርሱ፡ በሚስትነቴ፥ ደግሞም፡ እግዚአብሔር፡ በቸርነቱ፡ በእርሱ፡ ለሚሰጠኝ ልጆች፡ በወላጅነቴ፡ ከእኔ የሚጠይቀውን፡ ማናቸውንም አደራና ኀላፊነት፥ ተግባርና ግዳጅ እፈጽማለሁ፡፡

“በፈጣሪያችንና በሰላማችን፥ በካህን፡ ሊቀ ካህናታችንና በንጉሥ፡ ንጉሠ ነገሥታችን፡ በኢየሱስ መሲሕ፥ እንዲሁም፡ በሃይማኖታችንና በመድኃኒታችን፥ በእናታችንና በንግሥታችን፥ በአገራችንም፡ በድንግል ማርያም ዙፋን ፊት፡ ይህን፡ የጋብቻ ቃል ኪዳን የሰጠሁት፡ በፍጹም ዕውቀትና እምነት፥ ፍላጎትና ፈቃደኛነት፥ እውነተኛነትና ቊርጠኛነት መኾኑን አረጋግጣለሁ፡፡”

*ሙሽሮቹ፡ እነዚህን፡ ከላይ የተገለጹትን ቃል ኪዳናት የመገባባት ሥርዓቶችን ከፈጸሙ በኋላ ይቀመጣሉ።*

# <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የሥርዓተ ተክሊሉ ጸሎትና ቡራኬ።</u>

### <u>አንደኛ</u>

*ከዚህ በኋላ፡ ሙሽሮቹና ዕድምተኞቻቸው ተቀምጠው፡ የተክሊሉ መርሓ ግብር ይጀመርና፡ ካህኑ፡ የቀለበቱን ሥርዓት ያካኼዳል።*

**ኹለት አካላት፡ ዐብረው እንደነዶ ሲታሠሩ፡ ገመዱ፡ ክብ ኾኖ ተጠምጥሞ፡ አንድ እንደሚያደርጋቸው ኹሉ፡ እኒህ፡ በኹለት ጾታዎች ተለይተው የተፈጠሩ ወንድና ሴት፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ቃል ኪዳናቸው አረጋግጠው ባጸኑት፡ በዚህ፡ በቅዱሱ ኪዳን ጋብቻቸው ተሣሥረው፡ አንድ አካል ስለሚኾኑ፡ <u>ቀለበቱ፡</u> የዚያ አንድነታቸው ምልክት ነው። ከዚህ አንድነት በሚገኙት፡ መሰል ፍሬዎቻቸው የሚቋቋመው ቤተሰብ፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት፡ ገሃድ የኾነ አዎንታዊ ማስተማመኛ ኾኖ፡ አባሎቹ፡ ዘለዓለማዊዉን ሕይወት የሚኖሩበት ይኾናል።**

*ካህኑ፡ በቅድሚያ፡ በቀለበቶቹ ላይ የሚደረገውን፡ እንዲህ የሚለውን ጸሎት ያደርሳል፡፡*

| | |
|---|---|
| **ነአኵተከ ኦ እግዚአብሔር አምላክ! አኀዜ ኵሉ፤ ዘሀሎከ እምቅድመ ኵሉ ዓለማት፤ ዘአጽናዕከ ሰማያተ ወምድረ በቃልከ፣ ወመሠረተ ምድር፥ ወኵሎ ግብረ፡ ዘውስቴቶሙ።** | **እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! ኹሉን የያዝህ፥ ከዓለማት በፊት የነበርህ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የምድርን መሠረትና በውስጣቸው የሚገኙትንም ፍጥረታት ኹሉ፡ በቃልህ ያጸናህ፡ እናመሰግንሃለን።** |
| **ዘአስተጋባእከ ዝርዋነ፤ ወረሰይኮሙ ለክልኤሆሙ አሐደ፤ ይእዜኒ፡ ኦ እግዚእነ! ንትአምነከ፡ ከመ ትባርክ፡ ዘንተ፡ ኅልቀተ ዘኪዳን ጽኑዕ፡ ከመ ይኩኖሙ፡ ትእምርተ ማእሰረ ተዋሕዶ፡ ለእሉ ወልድከ ወለገብርከ አክሊለ-ሰማዕት [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ]፥ ወለወለትከ ወለዓመትከ ዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]፡ ዘኪዳን ቅዱስ፣ እስመ የኀሥሡ በረከተ፡ ዘእምኀቤከ።** | **የተበተኑትን የሰበሰብህ፤ ኹለቱንም ወገን፡ አንድ ያደረግህ፤ አኹንም፡ እግዚአብሔራችን ሆይ! ይህን፡ የጸና የቃል ኪዳን ቀለበት ትባርክ ዘንድ እንታመንብሃለን፤ እኒህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ልጆችህና አገልጋዮችህ፣ ነጋሚዎችህም፡ አክሊለ-ሰማዕት [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ] እና ዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]፡ ለአንድነታቸው ምልክት ይኾንላቸው ዘንድ፡ ከአንተ በረከትን ይሻሉና።** |
| **ወከመ ይኩኑ ድልዋነ፡ ለአርአያ ትእምርተ ቃልከ፡ በማእሰረ ዐረቦን፡ ከመ ይኩኑ ሎሙ፡ ፍቅር ዘኢይትፈለጥ በበይናቲሆሙ፥ በጻዕቅ ጽኑዕ፡ ላዕለ መሠረተ መንግሥትከ።** | **በቀዳሚው ማሠሪያ፡ ለቃልህ የአርአያነት ምልክት የተዘጋጁ እንዲኾኑ፡ በመካከላቸው፡ የማይለያይ ፍቅር ይኾንላቸው ዘንድ፤ ይኸውም፡ በመንግሥትህ መሠረት ላይ በጽኑ የጠበቀው ነው።** |

| | |
|---|---|
| ወከመ ያንሶስዉ፡ በማእሰረ ተዋሕዶ፡ ዘአጽንዕዎ በበይናቲሆሙ፤ እስመ አንተ ውእቱ፡ ማእሰረ ፍቅር፤ ወአዘዝከ በሕግ፡ ተባጽሆቶሙ፤ ወረሰይከ ተሰናዕዎ ማእከሌሆሙ።<br>ወከመ ይፈጽሙ፡ ትእዛዘ ወልድከ ዋሕድ፡ እግዚእነ፣ ወአምላክነ፣ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘሎቱ ይደሉ፡ ስብሓት ወክብር፥ ወሰጊድ ምስሌከ፥ ወምስለ መንፈስ ቅዱስ፤ ይእዜኒ፥ ወዘልፈኒ፥ ወለዓለም ዓለም፤ አሜን። | እያንዳንዳቸው፡ ተስማምተው ባጸኑት፡ በአንድነት ማሠሪያ ይኖሩ ዘንድ፤ አንተ፡ የፍቅር ማሠሪያ ነህና፤ ቃል ኪዳናቸውን፡ በሕግህ አዝዘሃልና፤ በመካከላቸውም፡ መግባባትን አድርገሃልና።<br>የአንድ ልጅህን፡ የእግዚአብሔራችንንና የአምላካችንን፥ የሰላማችንን፣ የካህናችንንና የንጉሣችንን፡ የኢየሱስ መሲሕን ትእዛዝ ይፈጽሙ ዘንድ፤ እርሱም፡ ጌትነት፥ ክብርና ስግደት የሚገባው ነው። ከአንተም፥ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ፤ ዛሬም፣ ዘወትርም፣ ለዘለዓለሙ፤ አሜን። |

*ቀጥሎ፡ ካህኑ፡ ቀለበቶቹን፡ እንዲህ እያለ በማማተብ፡ በመስቀል ይባርካል።*

*ሙሽሮቹና ሕዝቡ፡ ቆመው፡ በእያንዳንዱ ቡራኬ መጨረሻ፡ "አሜን!" ይላሉ።*

| | |
|---|---|
| በስመ እግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፤ ናበጽሕ ተክሊለ ቡሩክ እኁነ ድንግል ኪዳናዊ: በተዋሕዶ ሃይማኖት ኢትዮጵያዊት ዘቅዱስ ኪዳን አክሊለ-ሰማዕት **[አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ]**፣ ወቡርክት እኅትነ ድንግል ኪዳናዊት: በተዋሕዶ ሃይማኖት ዘቅዱስ ኪዳን **ዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]**።<br>ቡሩክ እግዚአብሔር አብእም፡ አኀዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ!<br>ወቡሩክ እግዚአብሔር ወልድ ዋሕድ፡ እግዚእነ ኢየሱስ መሲሕ፣ ዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል፡ ለሰላመ ዚአነ!<br>ወቡሩክ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ፥ መጽንዒ፥ ወመንጽሔ ለኵልነ! አሜን። | በእግዚአብሔራችንና በአምላካችን፥ በሰላማችንና በካህናችን፣ በንጉሣችን፡ በኢየሱስ መሲሕ ስም የተባረኩ፥ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊት ተዋሕዶ ሃይማኖትም፡ ኪዳናዊ ድንግል የሚኾን፡ የወንድማችን፡ **የአክሊለ-ሰማዕትን [የአክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽን]**፣ ኪዳናዊት ድንግል የኾነች፡ የእኅታችን፡ **የዕሴተ-ገብርኤልን [የቤዛዊት ስንሻው ንጋቷን]** ተክሊል እናደርሳለን።<br>ዓለሙን ኹሉ የያዘው፡ አምላካችን እግዚአብሔር አብእም ቡሩክ ነው!<br>ሰላማችን ይኾን ዘንድ፡ ከመድኃኒታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው፡ አንዱ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ መሲሕም ቡሩክ ነው!<br>ሕይወትን፥ ጽናትንና መንጻትን ለኹላችን የሚሰጥ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ቡሩክ ነው! አሜን። |

*ይህ የቡራኬ ጸሎትና ሥርዓት ሲያበቃ፡ ሠራዒው ካህን፡ የሙሽራዪቱን ቀለበት አንሥቶ፡ ለሙሽራው ይሰጠዋል፡፡*

*ሙሽራውም፡ በሙሽራዪቱ፡ በግራ እጇ፡ በአራተኛው ጣቷ ውስጥ ያስገባላታል፤ ቀለበቱንም፡ ከጣቷ ጋር አንድ አድርጎ ይዞ፡ እንዲህ ይላታል፦*

"በክርስትና የጥምቀት ስምሽ፡ 'ዕሴተ-ገብርኤል' የተባልሽው፡ እኅቴ፡ ኪዳናዊት ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ ሆይ! በክርስትና የጥምቀት ስሜ፡ አክሊለ-ሰማዕት የተባልሁ፡ እኔ፡ ኪዳናዊ አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ፡ አንቺን፡ የዘለዓለም ሚስት ልትኾኚኝ፡ አግብቼሻለሁ፡፡

አንቺና እኔ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን፡ ላደረግነው፡ ለዚህ፡ የቃል ኪዳን ጋብቻችን ምልክት እንዲኾነን፡ እነሆ፡ ይህን ቀለበት ሰጠሁሽ! እንግዴህ፡ ከዚህ ዕለት፥ ከዚህች ሰዓት ጀምሮ፡ ያገኘሁትን ኹሉ፡ ካንቺ ጋራ አንድ አደርጋለሁ፡፡

"ለዚህም ምስክሮቼ፡ ፈጣሪያችን እና አምላካችን፥ አባታችን እግዚአብሔር አብ፣ መድኃኒታችንና ሃይማኖታችን፣ እናታችን እግዝእተብሔር እም፥ ቅድስት ድንግል ማርያም፣ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡"

*ሙሽራዪቱም፡ ለእጮኛዋ ማረጋገጫ ቃል፡"አሜን!" የሚለውን ምላሽ ትሰጣለች፡፡*

*ካህኑ፡ አኹን ደግሞ፡ የሙሽራውን ቀለበት አንሥቶ፡ ለሙሽራዪቱ ይሰጣታል፡፡*

*ሙሽራዪቱም፡ በሙሽራው፡ በግራ እጁ፡ በአራተኛው ጣቱ ውስጥ ታስገባለታለች፤ ቀለበቱንም፡ ከጣቱ ጋር አንድ አድርጋ ይዛ፡ እንዲህ ትለዋለች፦*

"በክርስትና የጥምቀት ስምህ፡ 'አክሊለ-ሰማዕት' የተባልኸው፡ ወንድሜ፡ ኪዳናዊ አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ ሆይ! በክርስትና የጥምቀት ስሜ፡ ዕሴተ-ገብርኤል የተባልሁ፡ እኔ፡ ኪዳናዊት ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ፡ አንተን፡ የዘለዓለም ባል ልትኾነኝ፡ አግብቼሃለሁ፡፡

"አንተና እኔ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን፡ ላደረግነው፡ ለዚህ፡ የቃል ኪዳን ጋብቻችን ምልክት እንዲኾነን፡ እነሆ፡ ይህን ቀለበት ሰጠሁህ! እንግዴህ፡ ከዚህ ዕለት፥ ከዚህች ሰዓት ጀምሮ፡ ያገኘሁትን ኹሉ፡ ካንተ ጋራ አንድ አደርጋለሁ፡፡

"ለዚህም ምስክሮቼ፡ ፈጣሪያችን እና አምላካችን፥ አባታችን እግዚአብሔር አብ፣ መድኃኒታችንና ሃይማኖታችን፣ እናታችን እግዝእተብሔር እም፥ ቅድስት ድንግል ማርያም፣ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡"

*ሙሽራውም፡ ለእጮኛው ማረጋገጫ ቃል፡ እርሷ እንዳደረገችው፡ "አሜን!" የሚለውን ምላሽ ይሰጣል።*

*ካህኑ፡ የጋብቻው ቃል ኪዳን የጸና መኾኑን የሚያረጋግጥ ምልክት ስለኾነውና ሙሽሮቹ፡ በየቀለበታቸው መለዋወጥና መተሳሠር፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም፡ አንድ ስለመኾናቸው፡ የሚከተለውን ጸሎት፡ ወደእግዚአብሔር ያቀርባል። ሙሽሮቹና ሕዝቡ፡ "አሜን!" ይላሉ::*

| | |
|---|---|
| አ እግዚአብሔር! ዘለሓኮ ለአዳም ቀዳማዊ፡ በእደዊከ፤ ወገበርኮ ተባዕተ፥ ወአንስተ፤ ዘኮነት ብእሲተ ረዳኢተ፥ ወመጽንዒተ ሎቱ። ወእምደኃሪት ድንግል፡ ዘተወለድከ አንተ፡ በኵነትከ፡ ዳግማይ አዳም።<br>አንተ፣ ይእዜኒ፡ እግዚእነ፡ ኲንከ፡ ዐራቂ ለእሉ ክልኤቱ ወራዙት፡ መርዓዊ፥ አክሊለ-ሰማዕት [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ]፥ ወመርዓቱ፡ ዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]፡<br>ወአስተሳተፍኮሙ፡ በዐረቦነ ሱታፌ፤ ወሀብኮሙ ትእምርተ ተሳትፎቶሙ።<br>ወናሁ ኮኑ አሐደ፡ በማእሰረ ፍቅር፡ በሎሙ፡ "እሁብ ሰላምየ፡ ለክልኤክሙ፤ ወኅድግ ሰላምየ፡ ምስለ ክልኤክሙ!" እስመ አንተ ሰላመ ኵልነ።<br>ወንሕነኒ ንፌኑ፡ ስብሐተ፥ ወክብረ፥ እስከ አርያም፣ ምስለ ወልድከ ዋሕድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ፤ ይእዜኒ፣ ወዘልፈኒ፣ ወለዓለመ ዓለም። | በእጆችህ፡ ቀዳማዊዉን አዳም የፈጠርህ፣ ወንድና ሴት አድርገህ የሠራኸው፤ አንዳቸው፡ ለአንዳቸው፡ረዳትና ኃይል ይኾኑ ዘንድ፡ ባል እና ሚስት ያደረግሃቸው። ከኋለኛዪቱም ድንግል፡ ዳግማዊው አዳም ኾነህ የተወለድህ እግዚአብሔር ሆይ!<br>አኹንም፡ ፈጣሪያችን! ለእኒህ ኹለት ወጣቶች፡ ለሙሽራው፡ ለአክሊለ-ሰማዕት [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ] እና ለሙሽሪቷ፡ ለዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]፡ አዋሓጅ ኹንሃቸው!<br>በአንድነት ፈለማ አዋሓድሃቸው! አንድ የመኾናቸውንም ምልክት ሰጠሃቸው!<br>በፍቅር ማሠሪያ፡ አንድ ይኾኑ ዘንድ፡ "ሰላሜን፡ ለኹለታችሁም ሰጠኋችሁ፤ ሰላሜን፡ ከኹለታችሁ ጋር ተውሁላችሁ፤" አልሃቸው። አንተ፡ የኹላችን ሰላም ነህና።<br>እኛም፡ ወደላይ፡ ክብርና ምስጋናን፡ ከአንድ ልጅህና ሕይወትን ከሚሰጥ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ እናቀርብልሃለን። ዛሬም፤ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ። |

## <u>ኹለተኛ</u>

*ሙሽሮቹና ዕድምተኞቻቸው ተቀምጠው፡ ካህኑ፡ የአልባሳቱን ሥርዓት ያካኼዳል።*

**ኹለቱ ሙሽሮች፡ የእየራሳቸውን ካባ ከመልበሳቸው በፊት፡ በቅድሚያ፡ አንዱን ካባ ዐብረው ይለብሳሉ፤ እንዲህ መልበሳቸው፡ አንድነታቸውን ለማመልከት ሲኾን፡ አንድ ዓይነት የኾነውን ካባ፡ ለየብቻቸው መልበሳቸው ደግሞ፡ እኒህ፡ ወንድና ሴት፡ በዚህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ጋብቻ፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸውና ቃል ኪዳናቸው ተሣሥረው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አምላካዊዉን የክብር፥ የደስታና የደኅንነት ጸጋ ለመጎናጸፋቸው ምልክት ነው።**

*በቅድሚያ፡ ካህኑ፡ ኹለቱም ሙሽሮች እንደተቀመጡ፡ በጀርባቸው ላይ አንድ ካባ ደርቦ ያለብሳቸዋል። በኹለቱ የተክሊል ካባዎች ላይ የሚደረገውንም፡ እንዲህ የሚለውን ጸሎት ያደርሳል፡፡*

| | |
|---|---|
| አ እግዚአብሔር አምላክነ፡ ኢየሱስ መሲሕ! ዘአሠርጎከ ሰማየ በከዋክብት። ወለምድርኒ ዘአሠርጎካ በሥነ ጽጌያት። ወወሀብከ ለሰብእ ሀብተ ሰማያዌ፥ ወዕረፍተ ምድራዌ። | እግዚአብሔር አምላካችን፡ ኢየሱስ መሲሕ ሆይ! ሰማይን፡ በከዋክብት፥ ምድርንም፡ በአበቦች ውበት ያስጌጥህ። ለሰው፡ ሰማያዊ ሀብትንና ምድራዊ ዕረፍትን የሰጠህ። |
| ይእዜኒ ካዕበ፡ አንተ፡ አ ኄር ወመፍቀሬ ሰብእ! ንትአመን ከመ ባረክሃ፡ ለዛቲ ልብስ ቅርብት። ወኮነት ሎሙ፡ ለእሉ ፪ቱ ገብርከ፥ አክሊለ-ሰማዕት [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ]፥ ወዓመትከ ዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]፡ ለእለ ይለብስዋ በኂሩትከ፡ ልብሰ ፍቅር፥ ወክብር፥ ወመድኃኒት፤ ልብሰ ፍሥሓ፥ ወሓሤት። | አንተ፡ ሰውን የምትወድ ቸር ሆይ! ዛሬ ደግሞ፡ ይህችን፡ የቀረበች ልብስ፡ ስለባረክሃት እናመሰግንሃለን። ለሚለብሷት፡ ለእኒህ፡ ለ፪ቱ፡ የቃል ኪዳን ልጆችህና አገልጋዮችህ፣ ነጋሚዎችህም ለአክሊለ-ሰማዕት [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ] እና ለዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]፡ በቸርነትህ፡ የፍቅር፥ የክብርና የመዳን፥ የደስታና የሓሤት ልብስ ትኾንላቸው ዘንድ። |
| ዐቀብኮሙ፡ ከመ ይኩኑ ንጹሓነ በሥጋሆሙ፥ ወበነፍሶሙ፥ ወበመንፈሶሙ፤ ከመ ትኩን ሕይወቶሙ፡ ሕይወተ ሰላም፥ ወጥኢና፥ ወንጽሕ፡ በገቢረ ጽድቅ። | እውነትን በማድረግ፡ ሕይወታቸው፡ የንጽሕና፥ የሰላምና የጤና ትኾን ዘንድ: በነፍሳቸውና በሥጋቸው፥ በመንፈሳቸውም ንጹሓን እንዲኾኑ ጠበቅሃቸው። |
| ሀብኮሙ፡ በረከተ ሰማይ ወምድር። ወረሰይኮሙ ብዑላነ፡ በገቢረ ርትዕ። ወመላእከ አብያቲሆሙ፡ ኵሎ በረከተ። ወረሰይኮሙ በኵሉ ጊዜ፡ ድልዋነ፡ ለገቢረ ፈቃድከ፤ እስመ አንተ፡ መሓሪ፥ ወብዙኀ ምሕረት። | የሰማይና የምድርን በረከት ሰጠሃቸው። በቅንነት በመሥራት፡ ባለጸጎች አደረግሃቸው። ቤታቸውንም፡ በበረከት ኹሉ መላህ። በየጊዜው ኹሉ፡ ፈቃድህን ለመፈጸም፡ የበቁ አደረግሃቸው፤ አንተ፡ ርኅሩኅ ነህና፤ ቸርነትህም፡ የበዛ ነውና። |
| ለከ ስብሓት፡ ምስለ አብከ ኄር ሰማያዊ፤ ወእምከ ኄርት ሰማያዊት፣ ወመንፈስከ ቅዱስ ማሕየዊ፤ ዘዕሩይ፡ ምስሌከ። ይእዜኒ፤ ወዘልፈኒ፤ ወለዓለም ዓለም። | ቸር ከኾነ አባትህ፥ ቸሪት ከኾነች እናትህ፣ ከሚተካከልህና ሕይወትን ከሚሰጥ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ፡ ክብር ይገባሃል፤ ዛሬም፤ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ። |

*ሙሽሮቹና ሕዝቡ፡ "አሜን!" ይላሉ፡፡*

*ቀጥሎ፡ ካህኑ፡ አልባሳቱን፡ ከላይ በተነገረው የቡራኬ ቃል በማማተብ፡ በመስቀል ይባርካል፡፡*

*ሙሽሮቹና ሕዝቡ ቆመው፡ በእያንዳንዱ ቡራኬ መጨረሻ፡ "አሜን!" ይላሉ።*

*የቡራኬው ጸሎት ሲያልቅ፡ ካህኑ፡ ካባዎቹን ባርኮ፡ ሙሽሮቹን፡ እንደቆሙ ያለብሳቸዋል፡፡*

## ሦስተኛ

*የአልባሳቱ ሥርዓት እንዳበቃ፡ ሙሽሮቹና ዕድምተኞቻቸው ተቀምጠው፡ ካህኑ፡ የቅብዓ ቅዱሱን ሥርዓት ያካኼዳል።*

**ኹለቱ ሙሽሮች፡ ቅብዓ ቅዱስን የሚቀቡት፡ ክፉውን መንፈስ በመቃወም፡ በክርስትና ጥምቀታቸው ጊዜ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የመንግሥቱ አገልጋዮች ካህናትና ወራሾች ንጉሥ/ንግሥት የኾኑበትን ጸጋ፡ አኹን፡ እኒሁ፡ ወንድና ሴት፡ በዚህ፡ የቅዱሱ ኪዳን ጋብቻቸው፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ ቃል ኪዳናቸው ተሟሥረው፡ ከዚያ፡ ከታተመው፡የእግዚአብሔር ልጅነታቸውና ክህነታቸው ጋር፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ለንጉሣዊውና ለንግሥታዊው ክብር የመብቃታቸው ማረጋገጫ ምልክት ነው።**

*በቅድሚያ፡ ካህኑ፡ በቅብዓ ቅዱሱ (ዘይቱ) ላይ፡ ከዚህ በታች ያለውን ጸሎት ያደርሳል፡፡*

*ሙሽሮቹና ሕዝቡም፡ ካህኑ፡ "ኾነ!" ሲል፡ በየምዕራፉ፡ "አሜን!" ይበሉ።*

| | |
|---|---|
| ኦ እግዚእነ፥ ወአምላክነ፡ አኃዜ ኵሉ፥ አቡሁ፤ ወእሙ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፥ ወካህንነ፤ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘቀባዕከ ካህናተ፥ ወነገሥተ፥ ወነቢያተ፡ በቅብዐ ፍሬ ዘይት።<br>ኦ እግዚአብሔር፥ ወመፍቀሬ ሰብእ! ኀቤከ ነአኵተከ፥ ወንትአመን፤ ከመ ባረክሽ ለነ፡ ዘንተ ዘይተ። ወኮነ፡ ንዋየ ጽድቅ፥ ወርትዕ፡ ዘያከብሮሙ ለ፪ቱ ደቂቅከ፡ ገብርከ፥ ወዓመትከ፡ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ዘቅዱስ ኪዳን፡ እኁነ፡ አክሊለ-ሰማዕት [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ]፤ ወእኅትነ፡ ዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]።<br>ወኮነ፡ መሠረተ ጽድቅ፥ ወርትዕ።<br>ወኮነ፡ ቅብዐ ንጽሕ ዘኢይጠፍእ።<br>ወኮነ፡ ሥነ፡ ዘኢይጸመሂ፥ ወብርሃነ ዘሥጋ።<br>ወኮነ፡ ሠርጐ ፍሥሓ፥ ወሓሤት ዘበአማን።<br>ወኮነ፡ ዘይመውዕ፡ ኵሎ ኃይለ ጸላኢ፥ ወፀር።<br>ወኮነ፡ ዘይሔድስ ነፍሶሙ፥ ወሥጋሆሙ፥ ወመንፈሶሙ።<br>ወኮነ፡ ዘይሁብ ፍሬ ብዕል፥ ወምግባረ ሠናይ።<br>ወኮነ፡ ክብር ወስብሓት፡ ለቅዱስ ስምከ፤ ምስለ ወልድከ ዋሕድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ፥ ዘዕሩይ ምስሌከ፤ ለዓለመ ዓለም። አሜን። | ኹሉን የያዝህ፡ እግዚአብሔር ሆይ! የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፤ የካህናችንና የንጉሣችን፡ የኢየሱስ መሲሕ አባት-እናት! በወይራ ፍሬ ዘይት፡ ካህናትንና ነገሥታትን፥ ነቢያትንም የቀባህ!<br>ሰውን የምትወድ፡ ቸር እግዚአብሔር! ይህን ዘይት እንደምትባርክ እንታመንብሃለን። እኒህን፡ ፪ቱን ልጆችህንና አገልጋዮችህን፡ በኢትዮጵያ፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ኪዳናዊ ወንድማችን የኾነውን አክሊለ-ሰማዕትን [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽን]፤ እና ኪዳናዊት እኅታችን የኾነችውን ዕሴተ-ገብርኤልን [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷን] የሚያከብር ዘይት ኾነ!<br>የእውነትና የፍትሕ መሣሪያ ኾነ!<br>የማይጠፋ፥ ንጽሕና ያለው ቅባት ኾነ!<br>የማይጠወልግ መልክና የሥጋ ብርሃን ኾነ!<br>የእውነተኛ ደስታና ሓሤት ጌጥ ኾነ!<br>የጠላትንና የተቃዋሚን ኃይል ኹሉ ድል የሚነሣ ኾነ!<br>ነፍሳቸውንና ሥጋቸውን፥ መንፈሳቸውንም የሚያድስ ኾነ!<br>የብልጽግናና የበጎ አድራጎት ፍሬን የሚያበረክት ኾነ!<br>ከአንዱ ልጅህ፥ ከሚተካከልህና ሕይወትን ከሚሰጠው፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፡ ክብርና ምስጋና፡ ለቅዱስ ስምህ ኾነ! ለዘለዓለሙ፤ አሜን። |

*ካህኑ፡ ጸሎቱን እንደፈጸመ፡ ቅብዓ ቅዱሱን፡ ከላይ በተነገረው የቡራኬ ቃል በማማተብ፡ በመስቀል ይባርካል፡፡*

*ሕዝቡም፡ በእያንዳንዱ ቡራኬ መጨረሻ፡ “አሜን!” ይላሉ።*

*ይህ ጸሎትና ሥርዓት ሲያበቃ፡ በተጸለየበትና በተባረከው፡ በዚህ ዘይት፡ ካህኑ፡ ሙሽሮቹን፡ እየግንባራቸው ላይ፡ በመስቀል ምልክት፡ ይቀባቸዋል፡፡*

*ካህኑ፡ ከዚህ አያያዞ፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ በመቀባት፡ የጋብቻ ቃል ኪዳናቸውን ዐትመው ያጸኑበትን፡ ይህን የቅብዓት ሥርዓት፡ እንዲህ በሚለው ጸሎት፡ ወደእግዚአብሔር ያቀርበዋል፡-*

| | |
|---|---|
| ወኮነ ዝንቱ ቅብዐት፡ ዘይትቃወሞ፡ ለመንፈስ እኩይ።<br>ዝንቱ ቅብዐት፡ ዘተውህበ ለቅዱሳት ነፍሳት።<br>ዝንቱ ቅብዐት፡ ለተቃውሞ መንፈስ እኩይ፡ በእግዚእነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ንጉሠ ክብር።<br>እስመ ቅዱስ ውእቱ፡ አብእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፡ ሥሉስ ፍጹም። | ይህ ቅብዐት፡ ክፉ መንፈስን ይቃወም ዘንድ፡ ለተቀደሱ ነፍሳት የተሰጠ ነው።<br>ይህ ቅብዐት፡ የክብር ንጉሥ በሚኾን፡ በእግዚአብሔራችን በኢየሱስ መሲሕ፡ የክፋትን መንፈስ ለመቃወም የተሰጠ ነው።<br>የአብእም፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አንድነትና ሦስትነት ምስጢር ፍጹም ነውና። |

*ሙሽሮቹና ሕዝቡ፡ “አሜን!” ይላሉ፡፡*

## <u>አራተኛ</u>

*ካህኑ፡ ሙሽሮቹና ዕድምተኞቻቸው ተቀምጠው፡ የአክሊሉን ሥርዓት ያካኺዳል።*

**ኹለቱ ሙሽሮች፡ አክሊሉን፡ በዚህ፡ በቅዱሱ ኪዳን ጋብቻቸው አማካይነት፡ በእየራሳቸው ላይ የሚቀዳጁበት ምክንያት፡ ግልጽ ነው፤ ቀደም ብለው፡ በጥምቀታቸው ጊዜ፡በመንፈስ ቅዱስ ያገኙትን፡ ዘለዓለማዊዉን የእግዚአብሔር ልጅነትንና ክህነትን (የእርሱ አገልጋይ መኾንን) ብቻ ሳይኾን፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ የመጨረሻውን ምድራዊና ሰማያዊ ክብር የኾነውን የንጉሥነትና የንግሥትነት ማዕርግን ጭምር ለመቀበላቸው ምልክት እንዲኾናቸው ነው። ያ የቀደመው፡ በመንፈስ የኾነ እውነታ ሲኾን፡ የዛሬው ደግሞ በግዘፍ እየታየ የተፈጸመ እውነታ ነው፤ በዚህ እውነታ፡ ቤተ ሕዝቡንና ቤተ ክህነቱን፥ ቤተ ምልክናውንም፡ አጠቃልላና አዋሕዳ በያዘችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ የእግዚአብሔር ልጆች ብቻ ሳይኾኑ፡ ንጉሥና ንግሥት፥ ካህናትም ኾነው የተቀቡ መኾናቸው ተረጋግጧል።**

*በቅድሚያ፡ ካህኑ፡ በአክሊሎቹ ላይ፡ ከዚህ የሚከተለውን ጸሎት ያደርሳል፡፡*
*ካህኑ፡ “ኹነች!” ሲል፡ ሙሽሮቹና ሕዝቡም፡ በየምዕራፉ፡ “አሜን!” ይበሉ።*

ኦ እግዚአብሔር ቅዱስ፡ ዘአስተቀጸልኮሙ ለቅዱሳኒከ፡ አክሊላተ ዘኢይጸሙሂ፥ ዘአስተሳለምከ ኀቡረ ሰማያውያነ ምስለ ምድራውያን።

ይእዜኒ፡ አንተ፡ እግዚእነ፡ ባረክህከ! እሎንተ አክሊላተ፡ ዘአስተዳለውናሆሙ፡ ከመ ናንብሮሙ ላዕለ ወልድከ፥ ወገብርከ፡ እኍነ አክሊለ-ሰማዕት፡ [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ] ኪዳናዊ፣ ወላዕለ ወለትከ፥ ወአመትከ እኅትነ ዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ] ኪዳናዊት፥ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዘቅዱስ ኪዳን።

ወኮነት፡ አክሊለ ክብር፥ ወእግዚእና።

ወኮነት፡ አክሊለ በረከት፥ ወጥኢና።

ወኮነት፡ አክሊለ ፍሥሓ፥ ወይባቤ።

ወኮነት፡ አክሊለ ተድላ ወሓሤት።

ወኮነት፡ አክሊለ ፍትሕ፥ ወርትዕ።

ወኮነት፡ አክሊለ ጥበብ፥ ወልባዌ።

ወኮነት፡ አክሊለ ዕረፍት፥ ወዛኅን።

ወለእሉ ወልድከ፡ ወገብርከ፥ ወወለትከ፡ ወአመትከ፡ ዘይለብሱ፡ ሀብኮሙ፡ ማእሰረ ፍቅር፥ ወሰላም።

ወአድኃንኮሙ፡ እምኀሊና እኩይ።

ወአድኃንኮሙ፡ እምኵሉ ትምይንተ አጋንንት፤ ወእምኵሉ እኩይ፡ ክበደ ፀር።

ወሰማዕከ ጸሎቶሙ፡ ከመ ይኩን ጊሩትከ ላዕለ ክልኤሆሙ።

ወአኅደርከ ፍቅረከ፡ ውስተ አልባቢሆሙ።

የማይለወጡ አክሊሎችን፡ ለቅዱሳንህ ያቀዳጀህ፥ በአንድነትህ ሰማያውያንን፡ ከምድራውያን ጋራ ያስማማህ፡ ቅዱስ እግዚአብሔር ሆይ!

አኹንም፡ አንተ እግዚአብሔራችን፡ በኢትዮጵያ ቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ኪዳናዊ ወንድማችን በኾነው፡ ልጅህና አገልጋይህ፣ ነጋሚህም አክሊለ-ሰማዕት [አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ]፣ ኪዳናዊት እኅታችን በኾነችውም፡ ልጅህና አገልጋይህ፣ ነጋሚህም ዕሴተ-ገብርኤል [ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ] ራሶች ላይ ለመጫን ያዘጋጀናቸውን እነዚህን አክሊሎች ባረክህ!

አክሊላቸው፡ የክብርና የጌትነት አክሊልን ኹነች!

የበረከትና የደኅንነት አክሊልን ኹነች!

የደስታና የይባቤ አክሊልን ኹነች!

የተድላና የሓሤት አክሊልን ኹነች!

የእውነተኛ ዳኝነትና የትክክለኛ ፍርድ አክሊልን ኹነች!

የጥበብና የማስተዋል አክሊልን ኹነች!

የምቾትና የእርጋታ አክሊልን ኹነች!

፪ቱን አክሊላት ለሚቀዳጁት፡ ለእኒህ ልጆችህና አገልጋዮችህ፣ ነጋሚዎችህም፡ በፍቅር የሚዋሐዱበትን፡ የሰላም ማሠሪያን ሰጠሃቸው!

ከክፉ አሳብ ታደግሃቸው!

ከአጋንንት ፈተናና ከክፉ የጠላት ጥቃት ኹሉ አዳንሃቸው!

ቸርነትህ፡ በኹለቱም ላይ ይገለጥ ዘንድ፡ ጸሎታቸውን ሰማህ!

አንተን መውደድን፡ በየልቦናቸው አሳደርህ!

| | |
|---|---|
| ወነአምን ከመ ታስተዳሉ ሕይወቶሙ፡ እስከ ዕርግና። ወትረስዮሙ፡ ከመ ይትፌሥሑ፡ በርእየተ ውሉድ፥ ወአዋልድ። ወትረስዮሙ ዘይትበቍዑ፡ በውሉድ ዘተወልዱ።<br>ወትረስዮሙ፡ ጽኑአነ እስከ ፍጻሜ፡ በአሓቲ ቅድስት ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ዘቅዱስ ኪዳን፡ በመንግሥተ እግዚአብሔር ኢትዮጵያዊት፡ እንተ ትትመራሕ፥ ወትትመገብ በሥልጣነ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ወፍቁር ወልዳ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ።<br>ወታስተዳሉ ሎሙ ፍኖተ ጽድቅከ። በሥምረቱ፡ ለአቡከ ኄር፣ ወለእምከ ኄርት፣ ወመንፈስ ቅዱስ፡ ለዓለመ ዓለም፤ | የሥጋዊ ሕይወታቸውን ዕድሜ፡ እስከእርጅና እንዲቆይ እንደምታዘጋጅ!<br>ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወልደው በማየትና በመሳም፡ ደስ እንዲላቸው፣ በሚወልዱቸውም ልጆች፡ የሚጠቀሙ እንደምታደርግ፣<br>እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ በሚመርዋትና በሚያስተዳድሩዋት፡ በአንዲቷ ኢትዮጵያዊት የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ እስከመጨረሻው የጸኑ እንደምታደርጋቸው፣<br>በእውነትህ መንገድ ይኼዱ ዘንድ እንደምታዘጋጅላቸው፡ እናምናለን! ቸር በሚኾን አባትህና ቸሪት በምትኾን እናትህ፣ በመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ፤ ለዘለዓለሙ፤ |

*ሙሽሮቹና ሕዝቡ፡ "አሜን!" ይላሉ፡፡*

*ካህኑ፡ ጸሎቱን እንደፈጸመ፡ አክሊሎቹን፡ ከላይ በተነገረው የቡራኬ ቃል በማማተብ፡ በመስቀል ይባርካል፡፡*

*ሕዝቡም፡ በእያንዳንዱ ቡራኬ መጨረሻ፡ "አሜን!" ይላሉ።*

*የዚህ ክፍል ጸሎትና ሥርዓት እንዳበቃ፡ ካህኑ፡ የተጸለየባቸውንና የተባረኩትን አክሊሎች፡ በሙሽራውና በሙሽራዪቱ ዐናት ላይ፡ ፫ ጊዜያት እያመሳቀለ ካዞዋወረ በኋላ፡ በእያንዳንዳቸው ራስ ላይ አኑሮ፡ ያቀዳጃቸዋል።*

*ሠራዒው ካህን፡ ከዚህ አያያዞ፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ እነዚህን አክሊሎች መቀዳጀታቸው፡ የጋብቻቸው ቃል ኪዳን፡ ከመጨረሻው ጉልላት መድረሱን በማመልከት፡ ይህን የአክሊላት ጸሎት፡ እንዲህ እያለ ወደእግዚአብሔር ያቀርበዋል፡-*

| | |
|---|---|
| ኦ አምላክ፡ ዘኢይትመዋዕ! ናሁ አንበርከ፡ አክሊለ ጸጋ፡ ዲበ ርእሶሙ ለወልድከ ወለገብርከ፥ ወለወለትከ፥ ወለአመትከ፡ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዘቅዱስ ኪዳን፡ አክሊለ-ሰማዕት፡ [ኪዳናዊ አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ]፣ ወዕሴተ-ገብርኤል፤ [ኪዳናዊት ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ]፣<br>ወረሰይከ ሎሙ፡ ዘኢይጠፍእ አክሊለ ክብር ሉዓላዊ። ወባርክከ፡ ኵሎ ተግባሮሙ፤ እስመ አንተ፡ ዘትሁብ ኵሎ ሠናይተ። እስመ ለከ፡ ክብር፥ ወስብሓት፣ ምስለ አብከ ኄር ሰማያዊ፥ ወእምከ ኄርት ሰማያዊት፣ ወመንፈስከ ቅዱስ ማሕየዊ፤ ዘዕሩይ ምስሌከ፤ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን። | የሚያሸንፍህ የሌለ አምላክ ሆይ! በኢትዮጵያ፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ልጆችህና አገልጋዮችህ፣ ነጋሚዎችህም በኾኑት፡ በአክሊለ-ሰማዕት፣[በኪዳናዊ አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽ]፣ እና በዕሴተ-ገብርኤል [በኪዳናዊት ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ] ራሶች ላይ የጸጋ አክሊልን አኖርህ!<br>የማይጠፋ፡ ከፍ ያለ፡ የክብር አክሊልን አደረግህላቸው! ሥራቸውንም ኹሉ ባረክህ! በጎ ነገርን ኹሉ የምትሰጥ፡ አንተ ነህና።<br>ክብርና ምስጋና የአንተ ናቸው፤ ሰማያዊ ከሚኾን፡ ከቸር አባትህ፥ ከቸሪት እናትህ ጋራ፤ ከሚተካከልህ፥ ሕይወትን ከሚሰጠው፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን። |

*ሙሽሮቹና ሕዝቡ፡ "አሜን!" ይላሉ፡፡*

*ሙሽሮቹ፡ አክሊላቱን ከተቀዳጁ በኋላ፡ ካህኑ፡ እንዲህ የሚለውን ጸሎት፡ እያስሰማና በሙሽሮቹ ላይ፡ በመስቀል እያማተበ፡ ይባርካቸዋል።*

*ሙሽሮቹና ሕዝቡም፡ አግባብ ባለው ዐረፍተ ነገር ላይ፡ "አሜን!" እያሉ ይቀበሉት።*

| | |
|---|---|
| ኦ አብእም! አስተቀጸልኮሙ ክብረ እግዚእና!<br>ኦ ወልድ ዋሕድ! ባረኮሙ!<br>ኦ መንፈስ ቅዱስ! ቀደስኮሙ!<br>ኦ አምላክነ! ዘባረኮ አዳምሃ፡ ወሔዋንሃ፥ ወኖኅ፡ ምስለ ሓይከል፥ ወለኢትዮጲስ፡ ምስለ እንተላ [ወለመልከ-ጼዴቅ፡ ምስለ ሳሌም]፡ ባረክከ ዘንተ ሰብሳበ!<br>አምላክነ! ዘባረኮ፡ ለይስሓቅ፡ ምስለ ርብቃ፥ ወለዮሴፍ ምስለ አስኔት፥ ወለዮቶር፡ ምስለ ወለተ- ራጉኤል፥ ወለሙሴ፡ ምስለ ሲጳራ፡ ባርክከ፡ ዘንተ ሰብሳበ!<br>ኦ አምላክ! ዘባረክከ ዘካርያስሃ፥ ወኤልሣቤጥሃ፥ ኢያቄምሃ፥ ወሓናሃ፥ ወለኵሎሙ መፃምርሃ ቅዱሳን ኢትዮጵያውያን፥ ወመፃምርቲሃ ቅዱሳት ኢትዮጵያውያት፡ ባርክከ፡ ዘንተ ሰብሳበ፡ ዘአክሊለ-ሰማዕት፥ [ዘኪዳናዊ አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽን]፥ ወዘዕሴተ-ገብርኤል፤ [ወዘኪዳናዊት ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷ] አሜን። | የሰማዩ አባትእናት ሆይ!<br>ክብርንና ጌትነትን አቀዳጀሃቸው!<br>ወልድ ዋሕድ ሆይ! ባረክሃቸው!<br>መንፈስ ቅዱስ ሆይ! ቀደስሃቸው!<br>አዳምን እና ሔዋንን፥ ኖኅን፡ ከሓይከል ጋር፥ ኢትዮጲስንም፡ ከእንተላ ጋር [መልከጼዴቅንም፡ ከሳሌም ጋር] የባረክህ አምላክ ሆይ! አኹንም፡ ይህን ጋብቻ ባረክህ!<br>ይስሓቅን፡ ከርብቃ ጋር፥ ዮሴፍን፡ ከአስናት ጋር፥ ዮቶርን፡ ከወለተ ራጉኤል ጋር፥ ሙሴንም፡ ከሲጳራ ጋር፡ የባረክህ አምላክ ሆይ፡ ይህንም ጋብቻ ባረክህ!<br>የዘካርያስንና የኤልሣቤጥን፥ የኢያቄምንና የሓናን፥ የሌሎቹን ቅዱሳን ኢትዮጵያውያንና ቅዱሳት ኢትዮጵያውያት አንድነት የባርክህ አምላክ ሆይ! አኹንም፡ ይህን፡ የአክሊለ-ሰማዕትን፥ [የኪዳናዊ አክሊሉ መልአኩ ብርዝነሽን] እና የዕሴተ-ገብርኤልን፤ የኪዳናዊት ቤዛዊት ስንሻው ንጋቷን ጋብቻ ባረክህልን! አሜን። |

# ክፍል አምስት።

## ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብበት፡ ሥርዓተ ቅዳሴ።

*የቀለበቱና የአልባሳቱ÷ የቅብዓቱና የአክሊላቱ ሥርዓታት እንደተፈጸሙ፡ የጠቅላላው ሥርዓተ ተክሊል መደምደሚያ የኾነው፣ የቅዱስ ቍርባን ዝግጅትንና መቀበልን ያካተተው ሥርዓተ ቅዳሴ፡ ራሱ፡ ሠራዒው ካህን እና መሸሮቹ፣ መላው የቅዳሴው ሕዝበ ጉባኤም፡ በእግዝእተብሔር ድንግል ማርያምና በልጇ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ መንበር ፊት፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ተንበርክከው፣ ወይም፡ ሰግደው ባሉበት፡ "ፍትሓት ዘወልድ" የሚባለውን፡ የንስሓውን ጸሎት በማሰማት ካደረሰ በኋላ፡ "ለምስጋና ጸሎት ተነሡ!" በሚለው የረዳቱ ካህን (ዲያቆን) የዜማ ጥሪ ከመጀመሩ በፊት፡ ቀዳስያኑም፣ የቅዱሱ ቍርባን ታዳሚዎቹም፡ ኹሉም፡ ይህን ሃሌታ በኅብረት እያዜሙ፡ መንበሩን ይዞሩ!*

*ዕለቱ፡ በዓለ-ፍልሰታ ለማርያም ስለኾነ፣ መላ ቅዳሴው፡ በትንሣኤ ሥርዓት ተካኺዶ ይፈጸማል። ፍሬ-ቅዳሴውም፡ የኢትዮጵያዊው ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ይኾናል።*

| | |
|---|---|
| ይ.ሕ. ሃሌ ሉያ! ዮሴፍ÷ ወኒቆዲሞስ፡ ገነዝዎ ለኢየሱስ፡ በሰንዱናት፤ ለዘተንሥአ እሙታን፤ በመንክር ኪን። | ይ.ሕ. ሃሌ ሉያ! ዮሴፍ እና ኒቆዲሞስ፡ ድንቅ በኾነ ተመሥጦ፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ በበፍታ ገነዙት! |
| *(ቀጥለውም፡ ይህን የዐዋጅ ቃል፡ በኅብረት እያዜሙ ያስሰሙ!)* | *(ቀጥለውም፡ ይህን የዐዋጅ ቃል፡ በኅብረት እያዜሙ ያስሰሙ!)* |
| ሃሌ ሉያ! እመቦ ብእሲ፡ እምእመናን፡ ዘቦአ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ-እግዚአብሔር፤ በጊዜ ቅዳሴ፡ ወኢሰምዓ፡ መጻሕፍተ-ቅዱሳት፤ ወኢተዓገሠ፡ እስከይፌጽሙ ጸሎተ-ቅዳሴ፣ ወኢተመጠወ፡ እምቍርባን፡ ይሰደድ እምቤተ-ክርስቲያን፤ እስመ አማሰነ፡ ሕገ-እግዚአብሔር፤ ወአስተሓቀረ፡ ቍመተ፡ ቅድመ ንጉሥ ሰማያዊ፣ ንጉሠ ሥጋ፣ ወመንፈስ፤ ከመዝ መሀሩነ ሓዋርያት፡ በአብጥሊሶሙ። | ሃሌ ሉያ! በዚህ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የቅዱስ ቍርባን ሥርዓት ላይ ከተገኙ ሰዎች መካከል፤ በቅዳሴው ጊዜ፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማያዳምጥ፣ የቅዳሴውም ጸሎት፡ እስኪፈጸም የማይታገሥ፣ ከቅዱስ ቍርባኑም የማይቀበል ቢኖር፡ ከዚህ የቅዳሴ ሥርዓት ይለይ! የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና። የሥጋ እና የነፍስ፣ የመንፈስም ንጉሥ እና ንግሥት በሚገኙበት፤ በመለኮታዊው ዙፋን ፊት መቆምንም፡ አቃሏልና። ሓዋርያት፡ እንዲህ ሲሉ፡ በመልእክታቸው አስተምረውናልና። |
| *(አያይዘውም፡ ይህን በዜማ ይበሉ!)* | *(አያይዘውም፡ ይህን በዜማ ይበሉ!)* |
| አንቲ ውእቱ፣ መሶበ-ወርቅ ንጹሕ፡ እንተ ውስቴታ መና ኅቡዕ፣ ኅብስት ዘወረደ፡ እምሰማያት፣ ወሀቤ ሕይወት፡ ለኵሉ ዓለም። | ለዓለም ኹሉ፡ ሕይወትን የሚሰጥ፡ ከሰማያት የወረደ፡ኅብስት የኾነው፡ የተሠወረ መና ያለብሽ፡ ንጹሕ፡ የወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ። |

*በዚህ በቅዳሴው አገልግሎት ጊዜ፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ የሥርዓቱ ማእከል ይኾናሉ። ከአኹን በኋላ፡ ከቀደመው በበለጠ የሚተኮርባቸው፡ ሕያዋኑ የታቦት መንበር እነርሱ ናቸው። ከዚህ የተነሣ፡ "ንስግድ!" ሲባል፥ የኪዳን ጸሎት በሚደርስበት ወቅትና የምሥራቹ ቃል በሚነበብበት ሰዓት እስኪነሡ ድረስ፡ እነርሱ ተቀምጠው፡ የአገልግሎቱ ሥርዓት፡ ከፊሉ በዜማ ኾኖ የሚካኼደው፡ በእነርሱ ዙርያ ነው።*

**ይ.ካ. = ይበል ካህን፤ ት.ካ. = ትበል ካህኒት፤ ይ.ሕ. = ይበሉ ሕዝብ፤**

*ሠራዒው ካህን፡ በኅብስቱ እና በጽዋው ላይ የሚካኼደውን የጸሎት እና የቡራኬ ሥርዓት ከፈጸመ በኋላው ቀጥ ብሎ ቆሞ እና ኹለት እጆቹን በመስቀልኛ ዘርግቶ፣ ፊቱንም ወደመንበሩ ምሥራቅ መልሶ፡ ከፍና ዘለግ ባለ ድምፅ፡ አሰምቶ እንዲህ እያለ ያዚም!*

**ይ.ካ.** *(ሠራዒው)* አሐዱ፡ አብእም ቅዱስ፤ አሐዱ፡ ወልድ ቅዱስ፤ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።
**ይ.ሕ.** በአማን አብእም ቅዱስ፤ በአማን ወልድ ቅዱስ፤ በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።
**ይ.ካ.** ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ኵልክሙ አሕዛብ!
**ይ.ሕ.** ወይሴብሕዎ፡ ኵሎሙ ሕዝብ።
**ይ.ካ.** እስመ ጸንዐት ምሕረቱ ላዕሌነ!
**ይ.ሕ.** ጽድቁሰ ለእግዚአብሔር፡ ይሄሉ ለዓለም።
**ይ.ካ.** ስብሐት ለአብእም፥ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ! ይእዜኒ፣ ወዘልፈኒ፣ ወለዓለመ ዓለም፣ አሜን፤ ሃሌ፣ ሉያ።
**ይ.ሕ.** ስብሐት ለአብእም፥ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ! ይእዜኒ፣ ወዘልፈኒ፣ ወለዓለመ፣ ዓለም፣ አሜን፤ ሃሌ፣ ሉያ።
**ት.ካ.** *(በዜማ)* ንትነሣእ ለጸሎት፤
**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* እግዚኦ: ንሴብሓከ!
**ይ.ካ.** *(በዜማ)* ሰላም ለኵልነ፤
**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ምስለ መንፈስ ቅዱስ።
**ይ.ካ.** *(በዜማና በንባብ)* ነአኵቶ፡ ለገባሬ ሠናያት ላዕሌነ፡ እግዚአብሔር መሓሪ፡ አቡሁወእሙ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ። እስመ ሰወረነ፡ ወረድአነ፣ ዐቀበነ፡ ወአቅረበነ፣ ወተወከፈነ ኀቤሁ፤ ወተማኅፀነነ፣ ወአጽንዐነ፡ ወአብጽሓነ እስከ ዛቲ ሰዓት።
ንሰብሖ እንከ፡ እስመ ይዕቀበነ፡ በዛቲ ዕለት ቅድስት፤ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትነ፤ ወበኵሉ ሰላም፡ አኀዜ ኵሉ፡ እግዚአብሔር አምላክነ!

**ይ.ካ.** *(ዋናው)* አብእም፡ አንዱ ቅዱስ ነው፤ ወልድ፡ አንዱ ቅዱስ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ፡ አንዱ ቅዱስ ነው።
**ይ.ሕ.** አብእም፡ በእውነት፡ አንዱ ቅዱስ ነው፤ ወልድ፡ በእውነት፡ አንዱ ቅዱስ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ፡ በእውነት፡ አንዱ ቅዱስ ነው።
**ይ.ካ.** አሕዛብ፡ ኹላችሁም፡ እግዚአብሔርን አመስግኑት!
**ይ.ሕ.** ሕዝብ ኹሉ ያመሰግኑታል።
**ይ.ካ.** ምሕረቱ፡ በእኛ ላይ ጸንታለችና።
**ይ.ሕ.** የእግዚአብሔርስ እውነት ለዘለዓለሙ ይኖራል።
**ይ.ካ.** ለአብእም፥ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ፡ ምስጋና ኾነ! ዛሬም፣ ዘወትርም፣ ለዘለዓለሙ አሜን፤ ሃሌ፣ ሉያ።
**ይ.ሕ.** ለአብእም፥ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ፡ ምስጋና ኾነ! ዛሬም፣ ዘወትርም፣ ለዘለዓለሙ አሜን፤ ሃሌ፣ ሉያ።
**ት.ካ.** *(በዜማ)* ለጸሎት እንነሣ!
**ይ.ሕ.** እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን!
**ይ.ካ.** ሰላም ለኹላችን ኾነ!
**ይ.ሕ.** ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ።
**ይ.ካ.** *(በዜማና በንባብ)* ለእኛ፡ በጎ ነገርን ያደረገ፡ ይቅር ባይ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ይቅር ባይ፣ የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፣ የካህናችንና የንጉሣችን፡ የኢየሱስ መሲሕ አባትናእናት፡ ሰውሮናልና፤ ረድቶናልና፤ ጠብቆ አቅርቦናልና፤ ወደእርሱም ተቀብሎናልና፤ አጽንቶ ጠብቆናልና፤ እስከዚችም ሰዓት አድርሶናልና።
አኹንም፡ ክብርት በምትኾን፡ በዚች ዕለት፡ በሕይወታችን ዘመን ኹሉ፡ በፍጹም ሰላም፡ ኹሉን የያዘ አምላካችን እግዚአብሔር ስለሚጠብቀን እናመስግነው!

**ት.ካ.** *(በዜማ)* ሰብሑ!
**ይ.ካ.** *(በንባብ)* እግዚእ እግዚኦ እግዚአብሔር አኃዜ ኵሉ! አቡሁ፥ ወእሙ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፥ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ።

ነአኵተከ፡ ላዕለ ኵሉ ግብር፥ በእንተ ኵሉ ግብር፥ ወውስተ ኵሉ ግብር። እስመ ሰወርከነ፡ ወረዳእከነ፣ ዐቀብከነ፡ ወአቅረብከነ፣ ወተወከፍከነ ኀቤከ፣ ወተማኅፀንከነ፡ ወአጽናዕከነ፣ ወአብጻሕከነ እስከዛቲ ሰዓት።

**ት.ካ.** አእኵቱ! ወሰብሑ! እስመ መሓረነ እግዚአብሔር፤ ወተሣሃለ ላዕሌነ።

*(በንባብ)* ወተወክፈ ጸሎተ ወስብሓተ፡ እምነ ቅዱሳኒሁ በእንቲአነ፤ በዘይሤኒ ኵሎ ጊዜ ረሰየነ ድልዋነ፣ ከመ ንንሣእ፡ እምሱታፌ ምስጢር ቡሩክ፤ ወሰረየ ለነ፡ ኃጣውኢነ።

**ይ.ካ.** *(በንባብ)* በእንተ ዝንቱ ነአኵተከ፤ ወነኀሥሥ እምነ ኂሩትከ፤ አ መፍቀሬ ሰብእ! ሀብከነ፡ ከመ ንፈጽም፡ ዛተ ዕለተ ቅድስተ፤ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትነ፤ ወበኵሉ ሰላም፡ ምስለ ፈሪሆትከ በዘአፍቅሮትነ። ኵሎ ቅንዓተ፥ ወኵሎ መከራ፥ ወኵሎ መከራ፥ ወኵሎ ግብረ ሰይጣን፥ ወምክረ ሰብእ እኩያን፥ ወትንሣኤ ፀር፡ ዘኅቡእ፥ ወዘገሃድ፡ አርኅቅከ እግዚኦ እምኔነ! *(ይባርክ በዘመንገሌሁ)* ወእምነ ኵሉ ሕዝብከ! ወእምዝንቱ መካን ቅዱስ ዘዚአከ!

ኵሎ ሠናያተ ዘይሤኒ፥ ወዘይኄይስ፡ አዘዝከ ለነ! እስመ አንተ፤ ዘወሀብከነ ሥልጣነ፡ ከመ ንኪድ ከይሴ ወዐቃርብተ፣ ወዲበ ኵሉ ኃይለ ጸላዒ። ኢአባእከነ ውስተ መንሱት! አላ አድኅንከነ! ወባልሓከነ፡ እምኵሉ እኩይ፤ በጸጋ ወሣህል፡ ለዘፍቅረ ሰብእ፤ ዘበወልድከ ዋሕድ፡ እግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፥ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፤ ዘቦቱ ለከ፡ ስብሓት፥ ወክብር፥ ወእዘዝ፡ ይደሉ፡ ምስሌሁ፤ ወምስለ መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ፤ ዘዕሩይ ምስሌከ፤ ይእዜኒ፤ ወዘልፈኒ፤ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* እግዚኦ: ተሣሃልከነ!
**ት.ካ.** *(ንፍቂት፣ በዜማ)* ንትነሣእ ለጸሎት፤
**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* እግዚኦ: ንሴብሓከ!
**ይ.ካ.** *(ንፍቅ፣ በዜማ)* ሰላም ለኵልነ፤
**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ምስለ መንፈስ ቅዱስ።

**ት.ካ.** *(በዜማ)* አመስግኑ!
**ይ.ካ.** ኹሉን የያዝህ ፈጣሪያችን እና አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ! የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፣ የካህናችንና የንጉሣችን የኢየሱስ መሲሕ አባት-እናት! በኹሉ ሥራህ ላይ፥ ስለሥራህ ኹሉ፥ በሥራህም ውስጥ ኹሉ፡ እናመሰግንሃለን። ሰውረኸናልና፤ ረድተኸናልና፤ ጠብቀኸናልና፤ ወደአንተ አቅርበኸናል፤ ተቀብለኸናልና፤ ስለተማፀንብህ፡ አጽንተህ፡ ከዚች ሰዓት አድርሰኸናልና።

**ት.ካ.** እግዚአብሔር ስለማረን፣ በእኛም ላይ ይቅር ስላለ፣ ስለእኛ፡ ከቅዱሳንና ከቅዱሳት፡ ጸሎትን፥ ምስጋናንም ስለተቀበለ፤ ኹልጊዜ፡ ባማረ ነገር፡ ቡሩክ ከሚኾን ምስጢር፡ በአንድነት እንድንቀበል የበቃን ስላደረገን፡ አመስግኑት! አወድሱት!

**ይ.ካ.** ስለዚህ እናመሰግንሃለን፤ ከቸርነትህም እንሻለን፤ ሰውን የምትወድ ሆይ! ክብርት የምትኾን፡ ይህችን ዕለት እንድንፈጽም ሰጠኸን! የሕይወታችንን ዘመን ኹሉ፡ በፍጹም ሰላም፥ አንተን በፍቅር ከመፍራት ጋራ። ቅንዓትን ኹሉ፥ መከራውንም ኹሉ፥ የሰይጣንንም ሥራ ኹሉ፥ የክፉዎችንም ምክር፤ የጠላትን መነሣት፥ የተሠወረውንና የተገለጸውን፡ አቤቱ! ከእኛ! (በያግጣጫው ይባርክ) ከሕዝብህም ኹሉ! የአንተ ከሚኾን፡ ከዚህም ቅዱስ ቦታ አራቅህልን! በጎውን ነገር ኹሉ፥ ያማረውንና የሚሻለውን አዘዝህልን! እባቡን፥ ጊንጡንም፥ የጠላትንም ኃይል ኹሉ እንረግጥ ዘንድ፡ ሥልጣንን የሰጠኸን፡ አንተ ነህና። ወደመከራ አላገባኸንም! ከክፉ ነገር ኹሉ፡ አዳንኸን እንጂ።

አንድ ልጅህ፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን፥ ሰላማችን፣ ካህናችንና ንጉሣችን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለሰው ፍቅር ብሎ፡ ባደረገው ቸርነትና ይቅርታ። በእርሱ ያለ ምስጋና፥ ክብርና ጽንዕ፡ ከእርሱ ጋራ ለአንተ ይገባል፤ ከሚተካከልህ፥ ሕይወትን ከሚሰጥ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር፤ ዛሬም፣ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

**ይ.ሕ.** እግዚአብሔር ሆይ! ይቅር አልኸን!
**ት.ካ.** (ንፍቂት *በዜማ*) ለጸሎት እንነሣ!
**ይ.ሕ.** እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን!
**ይ.ካ.** (ንፍቅ) ሰላም ለኹላችን ኾነ!
**ይ.ሕ.** ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ።

| | |
|---|---|
| ይ.ካ. *(ንፍቅ፣ በንባብ)* ወካዕበ ንሴብሕ፡ ዘኵሎ ይእኀዝ፡ እግዚአብሔር አብእም፡ ለእግዚእ፥ ወሰላምነ ኢየሱስ መሲሕ።<br>በእንተ እለ ያበውኡ መባኣ፡ በውስተ ቅድስት አሓቲ፡ እንተ ላዕለ ኵሉ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ-እግዚአብሔር፤ መሥዋዕተ፣ አኰቴተ ተዝካር፥ ዘብዙኅ፡ ወዘኅዳጥ፥ ዘኅቡዕ፡ ወዘገሃድ፤ ወለእለሂ ይፈቅዱ የሀቡ፡ አልቦሙ ዘይሁቡ፡ ይትወከፍ ፍትወቶሙ ዘበሰማያት፡ መንግሥተ ጸጉ! ዘኵሉ ግብረ በረከት፡ ሥልጣን ቦቱ፡ እግዚአብሔር አምላክነ።<br>ት.ካ. *(ንፍቂት፣ በዜማ)* ስብሑ፤ በእንተ እለ ያበውኡ መባአ!<br>ይ.ሕ. *(በዜማ)* ተወከፍከ መባኦሙ ለአኀው! ወተወከፍከ መባኦን ለአኃት! ለነኒ ተወከፍከ መባአነ፥ ወአኰቴተነ! | ይ.ካ. *(ንፍቅ፣ በንባብ)* ዳግመኛ፡ ኹሉን የያዘ፡ የፈጣሪያችንንና የሰላማችንን፡ የኢየሱስ መሲሕን አባት-እናት፡ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን።<br>ከኹሉ በላይ በምትኾን፡ በከበረች፡ በአንዲት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መባ ስለሚያገቡ፤ መሥዋዕቱን እና የመታሰቢያ ምስጋናውን፥ ብዙውንና ጥቂቱን፥ የተሰወረውንና የተገለጸውን፥ ይሰጡ ዘንድ ሲወድዱ፡ የሚሰጡት ከሌላቸው ላይ፡ ፈቃዳቸውን ተቀብሎ፡ ለመንግሥቱ ያበቃ ዘንድ፡ ለኹሉ በረከትን፡ የሚያድልበት ሥልጣን፡ ገንዘቡ የሚኾን አምላካችን፡ እግዚአብሔር ነው።<br>ት.ካ. *(ንፍቂት)* አመስግኑ! መባ ስለሚያገቡ ሰዎች።<br>ይ.ሕ. የወንድሞችን መባ ተቀበልህ! የእኅቶችንም መባ ተቀበልህ! የእኛንም መባችንንና ምስጋናችንን ተቀበልህ! |

*ሠራዒው ካህን፡ የዕጣኑን ማዕጠንት የሚያሳርግበትን ጸሎት ያካኺዳል፡፡*
*ሙሽሮቹ፡ አኹን፡ "ንስግድ!" ከመባሉ በፊት፡ ከመቀመጫቸው ይነሣሉ።*

| | |
|---|---|
| ት.ካ. *(በዜማ)* ንትነሣእ ለጸሎት፤<br>ይ.ሕ. *(በዜማ)* እግዚኦ: ንሴብሓከ!<br>ይ.ካ. *(በዜማ)* ሰላም ለኵልነ፤<br>ይ.ሕ. *(በዜማ)* ምስለ መንፈስ ቅዱስ።<br>ይ.ካ. *(በዜማ፡ ፫ተ ጊዜ)* ንስግድ!<br>ይ.ሕ. *(በዜማ፡፫ ጊዜ)* ለአብእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፣ እንዘ ሠለስቱ፡ አሐዱ።<br>ይ.ካ. *(በዜማ)* ሰላም ለኪ!<br>ይ.ሕ. *(በዜማ)* ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ ማኅደረ መለኮት።<br>ይ.ካ. *(በዜማ)* መሓሪት ለነ!<br>ይ.ሕ. *(በዜማ)* ድንግል ማርያም፡ወላዲተ አምላክ።<br>ይ.ካ. *(በዜማ)* አንቲ ውእቱ፥<br>ይ.ሕ. *(በዜማ)* ማዕጠንት ዘወርቅ፣ እንተ ፆርኪ ፍሕመ እሳት፤ ቡሩክ ዘነሥአ እመቅደስ፤ ዘይሠሪ ኃጢአተ፥ ወይደመስስ ጌጋየ፤ ዝውእቱ፡ ዘእግዚአብሔር ቃል፣ ዘተሰብአ እምኔኪ፡ ዘአዕረገ ለአቡሁ ወእሙ፣ ርእሶ ዕጣነ፥ ወመሥዋዕተ ሥሙረ።<br>ንሰግድ ለከ መሲሕ፡ ምስለ አብከወእምከ ኄር ሰማያዊ፤ ወመንፈስከ ቅዱስ ማሕየዊ፣ እስመ መጻእከ፥ ወአስተሳለምከነ። | ት.ካ. *(በዜማ)* ለጸሎት እንነሣ!<br>ይ.ሕ. እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን!<br>ይ.ካ. ሰላም ለኹላችን ኾነ!<br>ይ.ሕ. ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ።<br>ይ.ካ. እንስገድ!<br>ይ.ሕ. ሦስት ሲኾኑ፡ አንድ ለሚኾኑ፡ ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስም።<br>ይ.ካ. ሰላም ለአንቺ ይኹን!<br>ይ.ሕ. ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡የመለኮት ማደሪያ ነሽ ።<br>ይ.ካ. በምሕረቷ የታረቀችን!<br>ይ.ሕ. አምላክን የወለደች፡ ድንግል ማርያም ናት።<br>ይ.ካ. አንቺ ነሽ፥<br>ይ.ሕ. ቡሩክ፡ ከቤተ መቅደስ የተቀበላት፡ የእሳትን ፍሕም የተሸከምሽ፡ የወርቅ ጥና። ኃጢኣትን የሚያስተሠርይ፥ በደልንም የሚያጠፋ፥ ራሱን፡ ያማረ መሥዋዕትና ዕጣን አድርጎ፡ ለአባቱ-ለእናቱ ያሳረገ። ይኸውም፡ ከአንቺ፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል፡ ሰው የኾነው፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው።<br>መሲሕ ሆይ! ቸር፥ የሰማያት ከኾኑ አባትህ-እናትህ ጋራ፥ ሕይወትን ከሚሰጥ፡ ከቅዱስ መንፈስህም ጋራ እንሰግድልሃለን፤ መጥተህ ሰላምህን አድለኸናልና። |

*እዚህ ላይ፡ የጸሎተ ዕጣኑና የማዕጠንቱ ሥርዓት፡ በሙሽሮቹ ዙርያና በአራቱ ማዕዝናት ይከናወናል።*

*ቀጥሎም፡ በቅድሚያ፡ ለሥርዓተ-ተክሊሉ፤ ከዚያም ተያይዞ፡ ለበዓለ-ፍልሰታዋ የሚገቡት፡ መዝሙራትና ምንባባት፡ ከሓዲሳት መጻሕፍት ተውጣጥተው እየቀረቡ፤ "ለምስጋና ጸሎት ተነሡ!" በሚለው፡ በዋናዋ ረዳት ካህኒት የዜማ ጥሪ፡ በቀጣይነት መስሰማት ይጀምራሉ።*

*እርሷም፡ ፊቷን ወደመንበሩ ምዕራብ መልሳ፤ የቀሩትም ቀዳስያን፡ በየተራቸው፡ በሰሜን እና በደቡብ ማዕዝናት፤ ሙሽሮቹ እና ሕዝቡ እንደተቀመጡ፡ ከአዲስ ኪዳኑ የመልእክታት መጻሕፍት፡ ከእያንዳቸው ተጠቅሰው የወጡትን፡ ከዚህ በታች ያሉትን የእግዚአብሔርን ቃላት ያነብባሉ።*

## <u>የሥርዓተ-ተክሊሉ፡ ምንባብ እና ምስባክ።</u>

<u>ምንባቦች፡-</u>

፩ኛ፡ ኤፌ. ፮፡ ፲-፲፰።

፪ኛ፡ ራእ. ፳፩፥ ፩-፰።

፫ኛ፡ የሓዋ. ፪፥ ፴፮-፵፮።

<u>ምስባክ፡-</u>

መዝ. ፹፬፡ ፲-፲፩።

ሣህል ወርትዕ ተራከባ፤
ጽድቅ ወሰላም ተሰዓማ፤
ርትዕሰ፡ እምድር ሠረፀት።

ምሕረትና ቅንነት ተገናኙ፤
እውነትና ሰላም ተሳሳሙ፤
ቅንነት፡ በምድር ላይ በቀለች።

*ይህም ምስባክ ከተዘመረ በኋላ፡ ሠራዒው ካህን፡ ለበዓሉ አግባብነት ያለውን፡ ከዚህ የሚከተለውን የምሥራች ቃል፡ ፊቱን ወደምሥራቅ አድርጎ ያነብባል። በዚህ ጊዜ፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ ስለምሥራቹ ቃል ክብር፡ እነርሱም፡ ሕዝቡም ይነሣሉ።*

<u>ብሥራት፡-</u> ማቴ. ፲፱፡ ፩-፲፪።

ት.ካ. *(በንባብ፡ እንዘ ትወጽእ ኅበ ምንባበ ቅዱሳት መጻሕፍት)*

ኵሉ ዘኢያፈቅሮ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፥ ወካህንነ፡ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወዘኢየአምን ልደቶ፡ እምማርያም እምቅድስት ድንግል በሠለስት፥ ታቦተ መንፈስ ቅዱስ፤ እስከምጽአቱ ሓዳስ፡ በከመ ይቤ ጳውሎስ፡ ውጉዘ ለይኩን!

*(ወታንብብ መንገለ ምዕራብ ዘመንበር!)*
*(እምድኅረ አንበበት፡ ትበል!)*

በረከተ አብወእም፥ ወፍተ ወልድ፥ ወሀብተ መንፈስ ቅዱስ፡ ዘወረደ ላዕለ ሓዋርያት፡ በጽርሓ ጽዮን ቅድስት፤ ከማሁ፡ ይረድ፥ ወይትመከዐብ ላዕሌየ፥ ወላዕለ ኵልክሙ።

ይ.ሕ. *(በዜማ)* ቅዱስ ሓዋርያ ጳውሎስ፡ ሠናየ መልእክት፥ ፈዋሴ ዱያን፤ ዘነሣእከ አክሊለ፤ ሰባሕከ፥ ወጸለይከ በእንቲአነ፤ እስመ አድኅነ ነፍሳተነ መሲሕ፡ በብዝኀ ሣህሉ፥ ወምሕረቱ፤ በእንተ ስሙ ቅዱስ።

ት.ካ. *(ንፍቂት፡ በንባብ፡ እንዘ ትወጽእ ኅበ ምንባበ ቅዱሳት መጻሕፍት)*

ነገር ዘመልእክተ ዮሓንስ፤ ረድኡ፥ ወሓዋርያሁ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፥ ወካህንነ፤ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፤ ጸሎቱ፥ ወበረከቱ፡ ሀለወ ምስሌነ፡ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

*(ወታንብብ መንገለ ሰሜን፡ ዘመንበር። እምድኅረ አንበበት፡ ትበል!)*

ኦ አኃውየ፥ ወአኃትየ! ኢታፍቅርዎ ለዓለም! ወኢዘሀሎ ውስተ ዓለም! ዓለሙኒ፡ ኃላፊ፤ ፍትወቱኒ ኃላፊ፤ ንብረቱኒ ኃላፊ ውእቱ።

ይ.ሕ. *(በዜማ)* ቅዱስ ሥሉስ! ዘኅቡር ህላዌከ፤ ዐቀብከ ማኅበረነ፤ በእንተ ቅዱሳን ኅሩያን፥ [ወቅዱሳት ኅሩያት] አርዳኢከ። ናዘዝከነ፡ በሣህልከ፤ በእንተ ቅዱስ ስምከ።

ት.ካ. *(ከቅዱሳት መጻሕፍት ልታነብብ ስትወጣ፡ በንባብ የምትለው፤)*

ፈጣሪያችንንና አምላካችንን፥ ሰላማችንን፤ ካህናችንንና ንጉሣችንን ኢየሱስ መሲሕን የማይወድደው፥ በሦስት ወገን፡ ድንግል፤ የመንፈስ ቅዱስም ማደሪያ ከኾነችው፡ ከቅድስት ማርያም መወለዱን የማያምን ሰው ኹሉ፡ እንግዳ እስከሚኾን ምጽአቱ ድረስ፡ ጳውሎስ እንደተናገረ የተለየ ይኹን!

*(በመንበሩ ምዕራብ አግጣጫ ታንብብ!)*
*(ካነበበች በኋላ፡ ይህን ትበል!)*

ቅድስት በምትኾን፡ በጽርሓ ጽዮን፡ በሓዋርያት ላይ የወረደው፡ የአብወእም በረከትና የወልድ ፍቅር፥ የመንፈስ ቅዱስም ሀብት፡ በእኔም፥ በእናንተ፡ በኹላችሁም ላይ ዕጥፍ ድርብ ኾኖ ይውረድ!

ይ.ሕ. አክሊልን የተቀበልህ፥ በሽተኞችን የምትፈውስ፥ መልእክትህ የበጀ፡ ቅዱስ ሓዋርያ ጳውሎስ ሆይ! መሲሕ፡ በይቅርታውና በቸርነቱ ብዛት፥ ስለቅዱስ ስሙም፡ ሰውነታችንን አድኗልና፡ ስለእኛ አመስግን! ጸልይም!

ት.ካ. *(ንፍቂት፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ልታነብብ ስትወጣ፡ በንባብ የምትለው፤)*

የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፤ የካህናችንና የንጉሣችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ሓዋርያው እና ደቀ-መዝሙሩ ከኾነው፡ ከዮሓንስ መልእክት፡ የተገኘ ቃል፡ ይህ ነው። ጸሎቱ እና በረከቱ፡ ከኹላችን ጋር ኾነ፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

*(በመንበሩ፡ የሰሜን አግጣጫ ታንብብ። ካነበበች በኋላ፡ ይህን ትበል!)*

*ወንድሞቼ እና እኅቶቼ! ሥጋዊዉን ዓለም፤ በውስጡ ያለውንም ኹሉ፡ ብቻውን አትውደዱት! ዓለሙ፡ ዐላፊ፤ ፈቃዱም፡ ዐላፊ፤ ንብረቱም፡ ዐላፊ ነውና።*

ይ.ሕ. ባሕርይህ አንድ የኾነ፡ በልዩ ሦስትነት የተገለጽህ ሆይ! አንድነታችንን ጠበቅህ፤ ስለቅዱስ ስምህ፤ ስለተመረጡት ቅዱሳን እና ቅዱሳት ደቀ-መዛሙርትህም፤ በይቅርታህ አጸናኸን።

| | |
|---|---|
| **ይ.ካ.** *(ንፍቅ፣ በንባብ፡ እንዘ ይወጽእ ኀበ ምንባበ ቅዱሳት መጻሕፍት)*<br>ነቅዐ ንጹሕ፡ ዘእምአንቅዕተ ሕግ ንጹሓን፣ ዝ፡ ውእቱ፡ ዜና ግብሮሙ ለሓዋርያት! በረከተ ጸሎቶሙ፡ ሀለወ ምስሌነ፤ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።<br>*(ወያንብብ መንገለ ደቡብ፡ ዘመንበር። እምድኅረ አንበበ፡ ይበል!)*<br>መልአ፣ ወዐብየ፣ ወተለዓለ ቃለ-እግዚአብሔር። ወበዝኀ፤ ወተወሰከ፣ ውስተ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ-እግዚአብሔር። ወበዝኁ ሕዝብ፡ እለ አምኑ በእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፥ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፣ ዘሎቱ ስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ አንተ አብወእም፡ አኃዜ ኵሉ፤ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ አንተ ወልድ ዋህድ፣ ዘአንተ ቃለ-አብወእም ሕያው፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ አንተ መንፈስ-ቅዱስ፣ ዘተአምር ኵሎ። | **ይ.ካ.** *(ንፍቅ፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ሊያነብ ሲወጣ፡ በንባብ የሚለው፣)*<br>ንጹሓን ከሚኾኑ፡ ከሕግ ምንጮች የተገኘ፡ ጥሩ ምንጭ፤ ይኸውም፡ የሓዋርያት፡ የሥራቸው ዜና ነው። ጸሎታቸው እና በረከታቸው፡ ከኹላችን ጋር ኾነ፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።<br>*(በመንበሩ፡ የሰሜን አግጣጫ ኾኖ ያንብብ። ካነበበ በኋላ፡ ይህን ይበል!)*<br>የእግዚአብሔር ቃል፡ እያደገ፣ ከፍ ከፍ እያለም፡ ፈጽሞ መላ። በቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትም በዝቶ ተጨመረ። ምስጋና የእርሱ በኾነው፡ በፈጣሪያችንና በአምላካችን፥ በሰላማችን፣ በካህናችንና በንጉሣችን፡ በኢየሱስ መሲሕ ያመኑት ሕዝብም በዙ፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ አብወእም ሆይ! አንተ፡ ኹሉን የያዝህ ነህ፤ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የአብወእም ሕያው ቃል ሆይ! አንተ፡ አንድ ልጃቸው ነህ፤ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ አንተ መንፈስ-ቅዱስም፡ ኹሉንም የምታውቅ ነህ። |

***የኪዳን ጸሎት፡ ከዚህ ይቀጥላል።***

| | |
|---|---|
| ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኃያል፣ ቅዱስ ሕያው፡ ዘኢትመውት፣ ዘተወለድከ እመድኃኒትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ አድኃንከነ እግዚኦ።<br>ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኃያል፣ ቅዱስ ሕያው፡ ዘኢትመውት፣ ዘተጠመቅከ በዮርዳኖስ፣ ወተሰቀልከ፡ ዲበ ዕፀ-መስቀል፡ አስተሳለምከነ እግዚኦ።<br>ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኃያል፣ ቅዱስ ሕያው፡ ዘኢትመውት፣ ዘተንሥእከ እሙታን፡ አመ ሣልስት ዕለት፤ ዐርግከ በስብሓት፡ ውስተ-ሰማያት፣ ወነበርከ በየማነ አቡከ ወእምከ፤ ዳግመ መጻእከ፡ በመንፈስ-ቅዱስናከ ኀቤነ፤ ወዳግመ ትመጽእ በስብሓት፤ ትኰንን ሕያዋነ፥ ወሙታነ፡ ተሣሃልከነ እግዚኦ፤<br>ስብሓት፡ ለእግዚአብሔር አብወእም፣ ስብሓት፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፤ ስብሓት፡ ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤ ይእዜኒ፣ ወዘልፈኒ፤ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን፣ ወአሜን፤ ለይኩን፣ ለይኩን፤ ቅዱስ ሥሉስ እግዚአብሔር ሕያው፡ ተሣሃልከነ። | ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኃያል፣ ቅዱስ ሕያው፡ የማትሞት፣ ከመድኃኒታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም የተወለድህ፤ አቤቱ አዳንኸን።<br>ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኃያል፣ ቅዱስ ሕያው፡ የማትሞት፣ በዮርዳኖስ የተጠመቅህ፣ በእንጨት መስቀል ላይ የተሰቀልህ፡ አቤቱ ሰላምህን ሰጠኸን።<br>ቅዱስ እግዚአብሔር፣ ቅዱስ ኃያል፣ ቅዱስ ሕያው፡ የማትሞት፣ በሦስተኛው ቀን፡ ከሙታን ተለይተህ የተነሣህ፤ በምስጋና ወደሰማያት ያረግህ፤ በአባትህ እና እናትህ ቀኝ፡ በዙፋንህ የተቀመጥህ፤ ዳግመኛ፡ በመንፈስ ቅዱስነትህ፡ ወደእኛ የመጣህ፤ በሕያዋንና በሙታን ልትፈርድም፡ እንደገና፡ የምትመጣ፡ አቤቱ ይቅር አልኸን።<br>ለእግዚአብሔር አብወእም፡ ምስጋና ኾነ! ለእግዚአብሔር-ወልድ፤ ምስጋና ኾነ! ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤ ምስጋና ኾነ! ዛሬም፣ ዘወትርም፣ ለዘለዓለሙ፤ በእውነት፣ በእውነት። ኾነ፤ አዎን! ኾነ። በቅድስት ሦስትነትህ የምትመለክ፡ አንተ፡ አንድ ሕያው እግዚአብሔር፡ ይቅር አልኸን። |

## ኪዳን፡ ዘመንፈቀ-ሌሊት።

ይ.ካ. ስብሓት ለእግዚአብሔር!
ይ.ሕ. ርቱዕ ይደሉ!
ይ.ካ. *(ያንብብ፡ ዘቀዳሚ ጸሎት!)*
ይ.ሕ. ኪያከ፡ ንሴብሕ እግዚኦ።
ት.ካ. *(ታንብብ፡ ዘካዕብ ጸሎት!)*
ይ.ሕ. ኪያከ፡ ንቄድስ እግዚኦ።
ይ.ካ. *(ያንብብ፡ ዘሣልስ ጸሎት!)*
ይ.ሕ. አሜን።

## ኪዳን፡ ዘነግህ።

ት.ካ. ጸጋ ዘእግዚአብሔር፡ ሀለወ ምስሌነ!
ይ.ሕ. ምስለ መንፈስ ቅዱስ!
ት.ካ. ሰባሕነ ለአምላክነ!
ይ.ሕ. ርቱዕ ይደሉ!
ት.ካ. አጽንዓነ፡ ኀሊና ልብነ!
ይ.ሕ. ብነ፡ ኀበ እግዚአብሔር፣ አቡነ፣ ወእምነ ዘበሰማያት፤ አቡነ፣ ወእምነ ዘበሰማያት፤ አቡነ፣ ወእምነ ዘበሰማያት፤ ኢአባእከነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት።
ት.ካ. *(ታንብብ፡ ዘቀዳሚ ጸሎት!)*
ይ.ሕ. ኪያከ፡ ንሴብሕ እግዚኦ።
ይ.ካ. *(ያንብብ፡ ዘካዕብ ጸሎት!)*
ይ.ሕ. ኪያከ፡ ንቄድስ እግዚኦ።
ት.ካ. *(ታንብብ፡ ዘሣልስ ጸሎት!)*
ይ.ሕ. አሜን።

## ኪዳን፡ ዘሠርክ።

ይ.ካ. ጸጋሁ ለእግዚአብሔር፡ ሀለወ ምስሌነ!
ይ.ሕ. ምስለ መንፈስ ቅዱስ!
ት.ካ. ነአኵቶ ለአምላክነ!
ይ.ሕ. ርቱዕ ይደሉ!
ይ.ካ. *(ያንብብ፡ ዘቀዳሚ ጸሎት!)*
ይ.ሕ. ንሴብሓከ እግዚኦ።
ት.ካ. *(ታንብብ፡ ዘካዕብ ጸሎት!)*
ይ.ሕ. ንቄድሰከ እግዚኦ።
ይ.ካ. *(ያንብብ፡ ዘሣልስ ጸሎት!)*
ይ.ሕ. አሜን።

## የመንፈቀ-ሌሊት ኪዳን።

ይ.ካ. ምስጋና፡ ለእግዚአብሔር ኹነ!
ይ.ሕ. እውነት ነው፤ ይገባል!
ይ.ካ. *(፩ኛውን ጸሎት ያንብብ!)*
ይ.ሕ. እግዚአብሔር ሆይ! አንተን፡ እናመሰግንሃለን።
ት.ካ. *(፪ኛውን ጸሎት ታንብብ!)*
ይ.ሕ. እግዚአብሔር ሆይ! አንተን፡ እናወድስሃለን።
ይ.ካ. *(፫ኛውን ጸሎት ያንብብ!)*
ይ.ሕ. አሜን።

## ኪዳን፡ ዘነግህ።

ት.ካ. የእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡ ከእኛ ጋር ነው!
ይ.ሕ. ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ!
ት.ካ. አምላካችንን አመስገንነው!
ይ.ሕ. እውነት ነው፤ ይገባል!
ት.ካ. ነፍሳችንን እና መንፈሳችንን አጸናን!
ይ.ሕ. የሰማያት፤ አባታችን እና እናታችን፣ የሰማያት፤ አባታችን እና እናታችን፣ የሰማያት፤ አባታችን እና እናታችን፡ አንተ እግዚአብሔር ስላለህልን፣ አቤቱ ወደፈተና አላገባኸንም።
ት.ካ. *(፩ኛውን ጸሎት ታንብብ!)*
ይ.ሕ. እግዚአብሔር ሆይ! አንተን፡ እናመሰግንሃለን።
ይ.ካ. *(፪ኛውን ጸሎት ያንብብ)*
ይ.ሕ. እግዚአብሔር ሆይ! አንተን፡ እናወድስሃለን።
ት.ካ. *(፫ኛውን ጸሎት ታንብብ!)*
ይ.ሕ. አሜን።

## ኪዳን፡ ዘሠርክ።

ይ.ካ. የእግዚአብሔር ጸጋው፡ ከእኛ ጋር ነው!
ይ.ሕ. ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ!
ት.ካ. ነአኵቶ አምላካችንን አመስገንነው!
ይ.ሕ. እውነት ነው፤ ይገባል!
ይ.ካ. *(፩ኛውን ጸሎት ያንብብ!)*
ይ.ሕ. እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን።
ት.ካ. *((፪ኛውን ጸሎት ታንብብ!)*
ይ.ሕ. እግዚአብሔር ሆይ! እናወድስሃለን።
ይ.ካ. *(፫ኛውን ጸሎት ያንብብ!)*
ይ.ሕ. አሜን።

*የኪዳኑ ጸሎት አንዳበቃ፡ ኹሉም፡ በኅብረት፡ ይህን፡ የምስጋና ጸሎት ያዚሙ!*

| | |
|---|---|
| **ይ.ሕ.** ኦ ሥሉስ ቅዱስ፡ አድኃንከነ፣ ኦ ሥሉስ ቅዱስ፡ አስተሳለምከነ፣ ኦ ሥሉስ ቅዱስ፡ መሓርከነ። | **ይ.ሕ.** ሥሉስ ቅዱስ ሆይ! አዳንኸን፤ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ! ሰላምህን ሰጠኸን፤ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ! ማርኸን። |

*ከዚህ ተያይዞ፡ የምሥራቹ ቃል ሥርዓተ ጸሎት ይካኼዳል።*

*ረዳቷ ካህን፡፡ በዜማ፡ "ለጸሎት ተነሡ!" ስትል፡ ሙሽሮቹ እንደተቀመጡ፡ ሕዝቡ ይነሣሉ።*

| | |
|---|---|
| **ት.ካ.** *(በዜማ)* ንትነሣእ ለጸሎት፤<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* እግዚኦ: ንሴብሓከ!<br>**ይ.ካ.** *(በዜማ)* ሰላም ለኵልነ፤<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ምስለ መንፈስ ቅዱስ።<br>**ይ.ካ.** *(በንባብ ወበዜማ)*<br>እግዚአብሔር እግዚኦ፡ ኢየሱስ መሲሕ አምላክነ፡ ዘትቤሎሙ ለአርዳኢከ ቅዱሳን፥ ወለሐዋርያቲከ ንጹሓን፡- "እስመ ብዙኃን ነቢያት፥ ወጻድቃን፡ ፈተዉ ይርአዩ፡ አንትሙ ዘትሬእዩ፤ ወኢርእዩ፤ ወፈተዉ ይስምዑ፡ አንትሙ ዘትሰምዑ፤ ወኢሰምዑ።<br>ወለክሙሰ፡ ብፁዓት አዕይንቲክሙ፡ እለ ርእያ፤ ወአእዛኒክሙ እለ ሰምዓ።"<br>ወከማሆሙ፡ ለነኒ፡ ረስይከነ ድልዋነ፡ ንስማዕ፥ ወንግበር ቃለ ብሥራትከ ቅዱስ፡ በጸሎቶሙ ለቅዱሳን።<br>**ት.ካ.** *(በዜማ)* ሰብሑ፡ በእንተ ብሥራት ቅዱስ!<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ረሰይከነ ድልዋነ፡ ለሰሚዐ ብሥራት ቅዱስ! | **ት.ካ.** *(በዜማ)* ለጸሎት እንነሣ!<br>**ይ.ሕ.** እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን!<br>**ይ.ካ.** ሰላም ለኹላችን ኾነ!<br>**ይ.ሕ.** ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ።<br>**ይ.ካ.** *(በንባብ ወበዜማ)*<br>አቤቱ አምላካችን፡ እግዚአብሔር ኢየሱስ መሲሕ ሆይ! ቅዱሳን የሚኾኑ ደቀ መዛሙርትህንና ንጹሓን ሐዋርያትን እንዲህ ያልሃቸው፡- "እናንተ የምታዩትን ያዩ ዘንድ፡ ብዙ ነቢያትና ጻድቃን ወደዱ፤ አላዩም። እናንተ ዛሬ የምትሰሙትንም ይሰሙ ዘንድ ወደዱ፤ አልሰሙም።<br>የእናንተ ያዩ ዓይኖቻችሁና የሰሙ ጆሮቻችሁ ግን፡ የተመሰገኑ ናቸው።<br>በቅዱሳን ጸሎት፡ የከበረ፡ የምሥራችህን ቃል ሰምተን፡ እንሠራ ዘንድ፡ እኛንም፡ እንደነርሱ የበቃን አደረግኸን!<br>**ት.ካ.** *(በዜማ)* አመስግኑ! ቅዱስ ስለሚኾን፡ ስለምሥራች ቃሉ።<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* የከበረ የምሥራቹን ቃል ለመስማት፡ የበቃን አደረግኸን! |

*ረዳቷ ካህኒት፡ ለበዓሉ ተስማሚ ኾኖ፡ ከዳዊት መዝሙር ተጠቅሶ የወጣውን "ምስባክ"፡ አንድ ጊዜ፡ በዜማ ታሰሰማለች፤ ያንንም ሕዝቡ ተቀብለው፡ አንድ ጊዜ መልሰው ያዚሙትና የመጨረሻውን፡ ኹሉም፡ በአንድነት ኾነው ይዘምሩታል።*

| | |
|---|---|
| **ት.ካ.** *(በዜማ፡ ምስባክ ዘሥርዓት፣ አው ወዘበዓል)*<br>**ይ.ሕ.** *(ክልኤተ ጊዜ ይበሉ ከማሁ።)*<br>**ት.ካ.** *(በዜማ)* ሃሌ ሉያ! ቁሙ! ወአጽምዑ! ብሥራት ቅዱሰ፤ ዜናሁ፡ ለእግዚእነ፥ ወሰላምነ ኢየሱስ መሲሕ። | **ት.ካ.** *(የሥርዓቱን፥ ወይም፡ የበዓሉን ምስባክ፡ በዜማ)*<br>**ይ.ሕ.** *(እንደዚሁ፡ ኹለት ጊዜ ይበሉ!)*<br>**ት.ካ.** *(በዜማ)* ሃሌ ሉያ! ፈጣሪያችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ የተናገረውን፡ ቅዱስ ምሥራቹን፡ ቆማችሁ ስሙ! |

*የምስባኩ ዜማ አብቅቶ፡ ረዳቷ ከህኒት፡ “ቁሙ!” የሚለውን መመሪያ፡ ለኹሉ ስታስሰማ፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ ስለምሥራቹ ቃል ክብር፡ እነርሱም ይነሣሉ።*

*ሠራዒው ካህን፡ ወደምሥራቹ ምንባብ መግቢያ የኾነውን የሚከተለውን ጸሎት፡ በዜማ ካስሰማ በኋላ፡ ለበዓሉ አግባብ የኾነውን የምሥራች ቃል፡ ፊቱን ወደመንበሩ አድርጎ ያነብባል።*

| | |
|---|---|
| **ይ.ካ.** *(በዜማ)* እግዚአብሔር፡ ምስለ ኵልነ። | **ይ.ካ.** እግዚአብሔር፡ ከኹላችን ጋር ነው።! |
| **ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ምስለ መንፈስ ቅዱስ። | **ይ.ሕ.** ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ። |
| **ይ.ካ.** *(በልዑል ዜማ)* ብሥራት ቅዱስ፡ ዘዜነወ ማቴዎስ፡ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር። | **ይ.ካ.** *(በታላቅ ዜማ)* ማቴዎስ የዜነወው፡ የእግዚአብሔር ልጅ ቃል፡ ቅዱስ ምሥራች፡ እነሆ! |
| **ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ስብሓት ለከ መሲሕ፡ እግዚእነ፥ ወአምላክነ፡ ኵሎ ጊዜ። | **ይ.ሕ.** ፈጣሪያችንና አምላካችን፡ መሲሕ ሆይ! ኹለጊዜ፡ ለአንተ ምስጋና ይገባል። |
| ተፈሥሑ፡ በእግዚአብሔ ዘረድአነ! ወየብቡ፡ ለአምላከ ያዕቆብ! ንሥኡ መዝሙረ! ወሀቡ ከበሮ! መዝሙር ሓዋዝ፡ ዘምስለ መሰንቆ። | በረዳን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ! የያዕቆብንም አምላክ አመስግኑ! መዝሙሩን በሉ! ከበሮውንም ምቱ! መዝሙር፡ ከበገና ጋር የተስማማ ነው። |
| **ይ.ካ.** *(በንባብ)* ነዋ፡ ብሥራተ መንግሥተ እግዚአብሔር! *(ወይሁብ መጽሓፈ ቅዱሰ፡ ለንፍቅ ካህን፤)* | **ይ.ካ.** የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ምሥራች፡ እነሆ! *(ብሎ፡ ቅዱሱን መጽሓፍ፡ ለረዳቱ ካህን ይስጠው!)* |
| ንፍቅ ካህን፡ *(ወውእቱሰ፡ የሀብ ለንት ካህኒት፡ እንዘ ይብል፡ በንባብ)* መንግሥቶ፥ ወጽድቆ፡ ዘአወፈየኒ፣ አወፈይኩኪ። | ንፍቁ ካህን፡- *(እንዲህ እያለ፡ ለዋናዋ ያስተላልፈው!)* በአደራ የተሰጠኝን፡ መንግሥቱንና እውነቱን ይኸው አስረከብሁህ! |
| **ት.ካ.** ተወክፍዋ በንስሓ፡ ለኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር! እስመ ትሄሉ ዘልፈ ማእከሌክሙ! ወማእከሌክን! | **ት.ካ.** ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በመካከላችሁ ናትና፡ በንስሓ ተቀበሏት! |
| **ይ.ካ.** ባርክ እግዚኦ! ነገረ፡ ዘእምብሥራተ-[ማቴዎስ፣ አው፣ ዘሉቃስ፡] ረድኡ፥ ወሓዋርያሁ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፥ ወካህንነ፡ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው፡ ሎቱ ስብሓት፡ ወትረ፡ እስከ ለዓለም። | **ይ.ካ.** የሕያው እግዚአብሔር ልጅ፡ የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፣ የካህናችንና የንጉሣችን፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ ሓዋርያውና ደቀ መዝሙሩ ከሚኾን፡ [ከማቴዎስ፥ ወይም ከሉቃስ] ምሥራች የተገኘውን ቃል፡ አቤቱ ባርክ! ምስጋና ዘወትር የእርሱ ነው፤ ለዘላለሙ። አሜን። |
| *(ወያንብብ መንገለ ምሥራቅ፡ ዘመንበር፤ ወእምድኅረ አንበበ ይበል በንባብ፣ እንዘ ብሥራቱ ዘማቴዎስ)* “ሰማይ ወምድር የኀልፍ፤ ወቃልየሰ ኢየኀልፍ!” ይቤ እግዚእ ለአርዳኢሁ። | *(ወደመንበሩ፡ ምሥራቅ አግጣጫ ኾኖ ያንብብ፤ ካነበበ በኋላ፡ ለማቴዎስ ምሥራች፡ ይህን፡ በንባብ ይበል!)* እግዚአብሔር ወልድ፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ “ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያልፍም።” አለ። |
| **ይ.ሕ.** *(እምድኅረ ምንባበ ብሥራት፡ በዜማ)* ነአምን አብወእም ዘበአማን፤ ወነአምን ወልደ ዘበአማን፤ ወነአምን፡ መንፈሰ ቅዱሰ ዘበአማን፤ ህልወ ሥላሴሆሙ ነአምን። | **ይ.ሕ.** *(ከምሥራቹ ንባብ በኋላ፡ በዜማ)* አብወእምን፡ በእውነት እናምናለን፤ ወልድንም፡ በእውነት እናምናለን፤ መንፈስ ቅዱስንም፡ በእውነት እናምናለን። የማይለወጥ ሦስትነታቸውን እናምናለን። |

| | |
|---|---|
| **ይ.ካ.** *(እንዘ ብሥራቱ ዘሉቃስ፣ ይበል! በንባብ)* "ይቀልል ኅልፈተ ሰማይ ወምድር፣ እምትደቅ አሓቲ ቃል፡ እምኦሪት፥ ወእምነቢያት።"<br><br>**ይ.ሕ.** *(እምድኅረ ምንባበ ብሥራት፡ በዜማ)* መኑ ይመስለከ፡ እምነ አማልክት እግዚኦ! አንተ ውእቱ፡ ዘትገብር መንክረ፤ አርአይኮሙ ለሕዝብከ ኃይለከ፤ ወአድኃንኮሙ ለሕዝብከ፡ በመዝራዕትከ። ሖርከ ውስተ ሲኦል፤ ወአዕረግከ ፄዋ እምህየ፤ ወጸጎከነ፡ ምዕረ፣ ዳግመ ግዕዛነ፤ እስመ መጻእከ ወአስተሳለምከነ። በእንተ ዝንቱ ንሴብሓከ፤ ወንጸርሕ ኀቤከ፣ እንዘ ንብል፡- "ቡሩክ አንተ እግዚኦ! ኢየሱስ መሲሕ፣ እስመ መጻእከ ወአስተሳለምከነ።" | **ይ.ካ.** *(ለሉቃስ ምሥራች፡፣ ይህን፡ በንባብ ይበል!)* 'ከኦሪት እና ከነቢያት፡ አንዲቱ ቃል ከምትወድቅ፡ የሰማይ እና የምድር ማለፍ ይቀልላል።<br><br>**ይ.ሕ.** *(ከምሥራቹ ንባብ በኋላ፡ በዜማ)* አቤቱ! ከአማልክት ወገን፡ የሚመስልህ ማነው? ተአምራትን የምታደርግ አንተ ነህ፤ ለሕዝብህ፡ ኃይልህን አሳየሃቸው፤ በክንድህም፡ ሰላምህን አስገኘህላቸው። ወደሲኦል ወርደህ፣ ከዚያ ምርኮን አወጣህ። ለአንዴ እና ለዘላለም፡ ዳግመኛ፡ ነጻነትን ሰጠኸን። መጥተህ፡ ሰላምህን አስገኘተህልናልና። ስለዚህ፡ እናመሰግንሃለን። አቤቱ! ኢየሱስ መሲሕ ሆይ! "ቡሩክ ነህ!" እያልን፡ ወዳንተ እየጮህን እንዘምራለን፤ መጥተህ፡ ሰላምህን አስገኘተህልናልና። |

<u>የበዓለ ፍልሰታ ለማርያም፡ ምንባብ እና ምስባክ።</u>

<u>ምንባቦች፡-</u>

፩ኛ፡ ዕብ. ምዕ. ፲፥ ቁ. ፲፰-፳፰።
፪ኛ፡ ራእ. ምዕ. ፲፩፥ ቁ. ፲፰-፲፱።
፫ኛ፡ የሐዋ. ምዕ. ፩፥ ቁ. ፮-፲፬።

<u>ምስባክ፡-</u>

መዝ. ፹፫፥ ቁ. ፪-፫።

ወትቀውም ንግሥት በየማንከ።
በአልባሰ-ወርቅ፡ ዑጽፍት፣ ወሁብርት፤
ስምዒ ወለትየ! ወርእዪ! ወአጽምዒ ዕዝነኪ።

ንግሥቲቱ፡ በቀኝህ ትቆማለች።
በወርቅ መጐናጸፊያ ተሸልማና አሸብርቃ፤
ልጄ ሆይ! ስሚ! እዩ! ጆሮሽንም አዘንብዪ።

*የምስባኩ ዜማ አብቅቶ፡ ዲያቆኑ፡ "ቁሙ!" የሚለውን መመሪያ፡ በዜማ፡ ለኹሉ ሲያስሰማ፡ ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ ስለምሥራቹ ቃል ክብር፡ እነርሱም ይነሣሉ።*

*ሠራዒው ካህን፡ ለሥርዓቱ፥ ወይም፡ ለበዓሉ አግባብነት ያለውን፡ የምሥራች ቃል፡ ፊቱን ወደመንበሩ ምሥራቅ አድርጎ ያነብባል።*

<u>ብሥራት፡-</u> ሉቃስ፤ ምዕ. ፩፥ ቁ. ፴፱-፶፮።

ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ ስለእግዚአብሔር ቃል አክብሮት፡ የምሥራቹ ሕያው መለኮታዊ መጽሓፍ የኾነውን፡ ራሱን፡ የአንባቢውን ካህን ግንባር ይስማሉ። ይህ ሥርዓት አረጋግጦ የሚያመለክተው እውነታ፡ ብቸኛውና የታመነው፣ ለመለኮታዊው እውነት ማደሪያና ምንጭ ኾኖ በፈጣሪ የተሠራው፡ የእግዚአብሔር መጽሓፍ፡ የፍጡር እጅ የጻፈው መጽሓፍ ሳይኾን፡ የፈጣሪ መመሪያ ቃል እንደሚያሳስበው፡ ራሱ፡ የሰብአዊው ፍጡር ሰውነት መኾኑን ነው።

+ + +

*ከዚህ ተያይዞ፡ ወደፍሬ-ቅዳሴ የመግቢያው ሥርዓተ-ጸሎት፡ እንደሚከተለው ይቀጥላል፦*

*በቅድሚያ፡ ስለዘለዓለማዊቷ፡ የሰማይ እና የምድር አገራችን ኢትዮጵያ፣ ስለእግዚአብሔር መንግሥቷ፣ በውስጧ ስላሉትም፡ ስለቤተሕዝቧ፣ ስለቤተ-ምልክናዋ እና ስለቤተ-ክህነቷ የአገልግሎት ዘርፎቿ፡ የሰላም ህልውና፡ የሚያርገው የምስጋና ጸሎት ይቀርባል።*

*ረዳቷ ካህኒት፡ በዜማ፡ "ለጸሎት እንነሣ!" ስትል፡ ሙሽሮቹ እንደተቀመጡ፡ ሕዝቡ ይነሣሉ።*

| | |
|---|---|
| ት.ካ. *(በዜማ)* ንትነሣእ ለጸሎት፤ | ት.ካ. *(በዜማ)* ለጸሎት እንነሣ! |
| ይ.ሕ. *(በዜማ)* እግዚኦ: ንሴብሓከ! | ይ.ሕ. እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን! |
| ይ.ካ. *(በዜማ)* ሰላም ለኵልነ፤ | ይ.ካ. ሰላም ለኹላችን ኾነ! |
| ይ.ሕ. *(በዜማ)* ምስለ መንፈስ ቅዱስ። | ይ.ሕ. ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ። |
| ይ.ካ. *(በዜማና በንባብ)* ወካዕበ ናአኵት፡ ዘኵሎ ይእኅዝ፡ እግዚአብሔር አብእም፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ። ንሰብሕ፥ ወነኅሥሥ እምነ ኂሩትከ፣ አ መፍቀሬ ሰብእ። ተዘከርከ እግዚኦ፡ ሰላመ ኢትዮጵያ! አሓቲ አገር ቅድስት፣ እንተ ተሐንጸት በኪዳንከ ቅዱስ፣ እምጥንተ-ዓለም፣ ወእስከ ለዓለም። | ይ.ካ. *(በንባብ)* ዳግመኛ፡ ኹሉን የያዘውን፡ የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፣ የካህናችንና የንጉሣችን፡ የኢየሱስ መሲሕን አባት-እናት፣እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። ሰው ወዳጅ ሆይ! ቸርነትህን እንሻለን፤ እንታመንብሃለንም። አቤቱ! ከዓለም መጀመሪያ አንሥተህ፡ ለዘለዓለም፡ በቅዱስ ኪዳንህ ስላነጽካት፡ ስለአንዷት ቅድስት አገር፡ ስለኢትዮጵያ፣ ስለሰላሟ፡ ስለምታስብላት እናመሰግንሃለን። |
| ት.ካ. ሰብሑ፡ በእንተ ሰላመ-ኢትዮጵያ፡ አሓቲ ሀገር ቅድስት፡ እንተ ቅዱስ ኪዳን፤ ሕንጽት በኀበ እግዚአብሔር። | ት.ካ. አመስግኑ! እግዚአብሔር፡ በቅዱስ ኪዳኑ አንጾ ለሠራት፤ አንዷት ቅድስት አገር ለኾነችው ኢትዮጵያ፡ ሰላሙን ስለሰጣት። |
| ይ.ካ. ኵሎ ሕዝበ፣ ወኵሎ መራዕየ፡ ባረኮሙ። ኵሎ ሰላመ፡ እንተ እምሰማያት፣ ፈነውከ ውስተ አልባቢነ ለኵልነ፤ ወሰላመ፣ ወሕይወተነ፡ ጸገውከነ ባቲ። ጸገውካ ሰላመ፡ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ፤ ለቤተ-ሕዝባ፣ ወለቤተ-ክህነታ፣ ወለቤተ-ምልክናሃ፣ ወለአድያማቲሃ። | ይ.ካ. በውስጧ የሚኖሩትን ሕዝቦች እና ወገኖች ኹሉ፡ በረክሃቸው። ሰማያዊት የኾነችውን ሰላምህን፡ በኹላችን ልቦና አሳደርህብን፤ በእርሷም፡ ሰላማዊ ሕይወትን ሰጠኸን። ለአገራችን ኢትዮጵያ፣ ለቤተ-ሕዝቧ፣ ለቤተ-ክህነቷ እና ለቤተ-ምልክናዋ፣ ለአካባቢዋም፡ ሰላምን ሰጠሃት። |

ወጉባኤ አግዋሪሃ፡ ዘአፍአ፤ ወውስጥ፤ አሠርገውኮሙ በኵሉ ሰላም። አ ንጉሠ-ሰላም! ሰላመከ ሀብከነ፤ እስመ ኵሎ፡ ዘወሀብከነ። አጥረይከነ እግዚአብሔር፤ ወዕሠይከነ። እስመ ዘእንቤለከ፡ አልቦ ዘነአምር። ስመከ ቅዱሰ ንሰሚ፤ ወንጼውዕ፤ እስመ አሕየወት ነፍሰነ፡ በመንፈስ ቅዱስ። ወኢይትኃየለ ሞተ-ኃጢአት ላዕሌነ፤ ለአግብርቲከ፣ ወለአዕማት፣ ወለኵሉ ሕዝብከ። በ፩ዱ ወልድከ፤ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ፤ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ። ስብሓት፣ ወእኂዝ፤ ይእዜኒ፣ ወዘልፈኒ፤ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

ይ.ሕ. *(በዜማ)* እግዚኦ: ተሣሃልከነ!

ይ.ካ. *(በዜማና በንባብ)* ወካዕበ ናአኵት፡ ዘኵሎ ይእኅዝ፡ እግዚአብሔር አብእም፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ። ንሰብሕ፥ ወነኀሥሥ እምነ ኂሩትከ፣ አ መፍቀሬ ሰብእ። ተዘከርከ እግዚኦ፡ ማኅበረነ፤ ባረኮሙ።

ት.ካ. *(በዜማ)* ሰብሑ፡ በእንተ ዛቲ፡ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፣ ወማኅበረነ በውስቴታ።

ይ.ሕ.*(በዜማ)* ማኅበረነ፡ ባረክከ፤ ዐቀብከነ በሰላም።

ት.ካ. *(በዜማ)* ንትነሣእ ለጸሎት፤

ይ.ሕ. *(በዜማ)* እግዚኦ: ንሴብሓከ!

ይ.ካ. *(በዜማ)* ሰላም ለኵልነ፤

ይ.ሕ. *(በዜማ)* ምስለ መንፈስ ቅዱስ።

ይ.ካ. *(በዜማ ወበንባብ)* እግዚአብሔር ዐቢይ ዘለዓለም፤ ዘለሐኮ ለሰብእ፡ እንበለ ሙስና። ሞተ፡ ዘቦአ ቀዳሚ፡ በቅንዓተ-ሰይጣን። አብጠልከ፡ በምጽአቱ ለሕያው ወልድከ፡ እግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ። ወመላእከ ኵላ ምድረ፣ ሰላመከ፡ እንተ እምሰማያት፣ እንተ ባቲ፡ ሠራዊተ-ሰማያት ይሴብሑከ፣ እንዘ ይብሉ፡- "ስብሓት፡ ለእግዚአብሔር በሰማያት! ወሰላም በምድር፡ ሥምረቱ ለሰብእ።

በቅርብ እና በሩቅ ያሉትንም፡ ጎረቤቶቿን ኹሉ፡ ሙሉ ሰላምን ሰጥተህ፡ አስደሰትሃቸው። የሰላም ንጉሥ ሆይ! ኹሉን ሰጥተኸናል፣ ሰላምህን ሰጠኸን። ከአንተ በቀር፡ ሌላ የምናውቀው አምላክ የለንምና፣ ቅዱስ ስምህንም ፈጽመን እንጠራለንና፡ እግዚአብሔር ሆይ! ዋጋችንን ሰጥተህ፣ ያንተ ጥሪት አደረግኸን። ነፍሳችን፡ በመንፈስ ቅዱስ ዳነች። በኃጢአት የመጣ ሞትም፡ በእኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን ልጆችህ እና አገልጋዮችህ፣ በሕዝብህም ላይ አልተበረታታም። በአንድ ልጅህ፣ በእርሱ ያለ ክብር እና ጽንዕ፡ ለአንተ ይገባል፤ከእርሱ ጋራ፤ ዛሬም፤ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

ይ.ሕ. *(በዜማ)* እግዚአብሔር ሆይ! ይቅር አልኸን!

ይ.ካ. ዳግመኛ፡ ኹሉን የያዘውን፡ የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፣ የካህናችንና የንጉሣችን የኢየሱስ መሲሕን አባት-እናት፣ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። ሰው ወዳጅ ሆይ! ቸርነትህን እንሻለን፤ እንታመንብሃለንም። አቤቱ! አንድነታችንን አስበህ ስለጠበቅህልን፣ ስለባረክህልንም፡ እናመሰግንሃለን።

ት.ካ. አመስግኑ! ስለዚች ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፣ በውስጧም ስለሰፈነው አንድነታችን።

ይ.ሕ. አንድነታችንን ባረክህ፤ በሰላምም ጠበቅኸን።

ት.ካ. *(በዜማ)* ለጸሎት እንነሣ!

ይ.ሕ. እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን!

ይ.ካ. ሰላም ለኹላችን ኾነ!

ይ.ሕ. ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ።

ይ.ካ. *(በዜማ ወበንባብ)* ለዘለዓለሙ ገናና የምትኾን እግዚአብሔር ሆይ! ሰውን፡ እንደማይጠፉ አድርገህ የፈጠርኸው። አስቀድሞ፡ በሰይጣን ቅንዓት የገባውን ሞት፡ በሕያው ልጅህ፡በፈጣሪያችንና በአምላካችን፥ በሰላማችን፣ በካህናችንና በንጉሣችን በኢየሱስ መሲሕ መምጣት አስወገድኸው። ከሰማይ የተገኘች ሰላምህን፡ በምድር ኹሉ መላህ። እርሷም፡ የሰማይ ሠራዊተ-መላእክት፡ "በሰማያት፡ ለእግዚአብሔር፡ ምስጋና ኾነ! በምድርም፡ ለሰው፡ ሰላም ይኾንለት ዘንድ ፈቃዱ ኾነ!" እያሉ፡ አንተን የሚያመሰግኑባት ናት።

| | |
|---|---|
| **ይ.ሕ.** *(ከማሁ ይበሉ!)* ስብሓት፡ ለእግዚአብሔር በሰማያት! ወሰላም በምድር፡ ሥምረቱ ለሰብእ።<br><br>**ይ.ካ.** ኦ እግዚኦ በሥምረትከ፡ መላእከ ውስተ አልባቢነ፡ ለኵልነ፤ ወአንጻሕከነ፡ እምኵሉ ደነስ፤ ወእምኵሉ ምርዓት፤ ወእምኵሉ ቂም፥ ወቅንዓት፤ ወእምኵሉ ምግባር ሕሱም፤ ወእምተዘክሮ እከይ፡ እንተ ታለብስ ሞተ። ወረሰይከነ ለኵልነ ድልዋነ፡ ከመ ንትአማኅ በበይናቲነ፡ በአምኃ ቅድሳት።<br>**ት.ካ.** *(በዜማ)* ሰብሐ፡ በእንተ ሰላም! ፍጽምት፥ ወፍቅር፤ ተአምኁ በበይናቲክሙ! በአምኃ ቅድሳት።<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* መሲሕ አምላክነ! ረሰይከነ ድልዋነ፡ ከመ ንትአማኅ በበይናቲነ፣ በአምኃ ቅድሳት። *(በዝየ፡ ይትአምኁ በኀድገተ-አበሳ፡ በበይናቲሆሙ፥ ወበበይናቲሆን፣ በመንገለ ፬ቱ ማእዝናት።)*<br>**ይ.ካ.** ወንትመጦ፡ እንበለ ኵነኔ፡ እምሀብትከ ቅድስት፡ እንተ ይእቲ እንበለ ሞት ሰማያዊት፤ በኢየሱስ መሲሕ፡ እግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ። ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ፤ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ። ስብሓት፣ ወእኂዝ፤ ይእዜኒ፣ ወዘልፈኒ፤ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን። | **ይ.ሕ.** *(እንዲሁ ይበሉ!)* "በሰማያት፡ ለእግዚአብሔር፡ ምስጋና ኾነ! በምድርም፡ ለሰው፡ ሰላም ይኾንለት ዘንድ ፈቃድህ ኾነ!"<br>**ይ.ካ.** እግዚአብሔር ሆይ! ፈቃድህን፡ በኹላችን ልቦና መላህ፤ ከኃጢኣትም ኹሉ፣ ከዋዛ-ፈዛዛም ኹሉ ፤ ከቂም እና ከቅንዓት ኹሉ፣ ከክፉ ሥራም ኹሉ፣ ሞትን ከምታለብስ፡ ክፉ ነገርንም ከማሰብ አነጻኸን። በተቀደሰች ሰላምታ፡ ይቅር በመባባል፡ እርስ-በርሳችን እጅ እንነሣሣ ዘንድ፣ ኹላችንንም የበቃን አደረግኸን።<br>**ት.ካ.** አመስግኑ! ፍጽምት እና የፍቅር ስለኾነች ሰላም። በተቀደሰች ሰላምታ፡ ይቅር በመባባል፡ እርስ-በርሳችሁ፡ እጅ ተነሣሡ!<br>**ይ.ሕ.** አምላካችን መሲሕ ሆይ! በተቀደሰች ሰላምታ፡ ይቅር በመባባል፡ እርስ-በርሳችን እጅ እንነሣሣ ዘንድ፣ የበቃን አደረግኸን። *(እዚህ ላይ፡ ኹሉም፡ ይቅር በመባባል፡ እርስ-በርሳቸው፡ በ፬ቱም ማዕዘን፡ እጅ ይነሣሡ!)*<br>**ይ.ካ.** እንግዴህ፡ በፈጣሪያችንና በአምላካችን፥ በሰላማችን፣ በካህናችንና በንጉሣችን፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ ሞት ከሌለባት፣ ሰማያዊት ከኾነችው፡ ከቅድስት የሥጋወደሙ ስጦታህ፡ ሳይፈረድብን ልንቀበል ነው። በእርሱ ያለ ክብር እና ጽንዕ፡ ለአንተ ይገባል፤ ከእርሱ ጋራ፤ ዛሬም፤ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን። |

*ይህ የሥርዓተ-ቅዳሴው የምስጋና ጸሎት፡ የፍሬ ቅዳሴው መግቢያ ኾኖ፡*
*በፍሬ ቅዳሴው ውስጥ፡ በኅብረት የሚነበቡት እና የሚዜሙት ጸሎቶች፡ እንደሚከተለው ሠፍረዋል፡-*

*ሠራዒው ካህን፡ ከዚህ የሚቀጥለውን ጸሎት፡ ከጨረሰ በኋላ፡ ከማዕጠንቱ የዕጣን መዓዛ፡ በእጆቹ እያፈነ፡ በሥጋው እና በደሙ መሥዋዕት ላይ፡ ፫ ፥ ፫ ጊዜያት ያሳርጋል።*

| | |
|---|---|
| **ይ.ካ.** አማን፡ መልአ፡ ሰማያተ፥ ወምድረ፤ ቅድሳተ፣ ስብሓቲከ፣ በእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ፡ ኢየሱስ መሲሕ። ቅዱስ ወልድከ መጽአ፤ ወእምድንግል ተወልደ፣ ከመ ፈቃድከ ይፈጽም፤ ወሕዝበ ለከ፡ ይግበር። | **ይ.ካ.** አዎን! የጌትነትህ ምስጋና፡ በፈጣሪያችንና በአምላካችን፥ በሰላማችን፣ በካህናችንና በንጉሣችን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በእውነት፡ በሰማያት እና በምድር መላ። ቅዱስ ልጅህ መጣ፤ ከድንግልም ተወለደ፤ ፈቃድህን ይፈጽም ዘንድ፤ ሕዝቡንም፡ ለአንተ ያደርግ ዘንድ። |

| | |
|---|---|
| ይ.ሕ. *ከቀዳስያኑ ጋር፡ በኅብረት፡ እንዲህ እያሉ ይዘምራሉ፡-*<br>ተዘከርከነ፡ እግዚኦ! በውስተ መንግሥትከ፤ ተዘከርከነ፡ እግዚኦ ኦሊቅ! በውስተ መንግሥትከ፤ ተዘከርከነ፡ እግዚኦ! በውስተ መንግሥትከ። በከመ ተዘከርኮ፡ ለፈያታዊ ዘየማን፤ እንዘ ሀሎከ ዲበ ዕፀ-መስቀል ቅዱስ። | ይ.ሕ. *ከቀዳስያኑ ጋር፡ በኅብረት፡ እንዲህ እያሉ ይዘምራሉ፡-*<br>አቤቱ! በመንግሥትህ አስበን! ሊቅ ሆይ! አቤቱ! በመንግሥትህ አስበን! ቅዱስ በሚኾን ዕፀ-መስቀል ላይ ሣለህ፡ በቀኝህ የተሰቀለውን ወንበዴ፡ በቸርነትህ እንዳሰብኸው፣ አቤቱ! እኛንም፡ እንደእርሱ፡ በመንግሥትህ አስበን! |

*ሠራዒው ካህን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በምሴተ-ሐሙስ፡ የመጨረሻ የፋሲካ ገበታው ላይ፡ የአዲስ ኪዳን ቍርባኑን፣ ይህም ማለት፡ የሥጋ ወደሙን ምስጢር እየገለጠ፣ አቀራረቡን እና አፈጻጸሙንም፡ ለደቀ መዛሙርቱ እያመለከተ፡ የሰጠበትን ሥርዓት፡ የሚያስታውሰውን ጸሎት፡ ከዚህ ቀጥሎ እያሰማ፤ ሥርዓቱን ይፈጽማል።*

| | |
|---|---|
| ይ.ካ. ሰፍሐ እደዊሁ ለሕማም፤ ሓሚሞ፡ ከመ ሕሙማነ ያድኅን፡ እለ ተወከሉ በላዕሌሁ። ዘተውህበ ለሕማም፣ ከመ ሞተ፡ ይሥዓር፤ ወማዕሠረ-ሰይጣን፡ ይብትክ፣ ወይኪድ፡ ሲኦለ፤ ቅዱሳነ፡ ይምራሕ፤ ሥርዓተ፡ ይትክል፤ ወትንሣኤሁ፡ ያዑቅ። | ይ.ካ. በእርሱ በመታመናቸው፡ በመከራ እየተፈተኑ ያሉ ወገኖቹን ሊያድን፡ እጆቹን፡ ለመከራ ዘረጋ። ሞትን፡ ይሽር ዘንድ፤ የሰይጣንንም ማሠሪያ፡ ይቆርጥ ዘንድ፤ ሲኦልንም፡ ይረግጥ ዘንድ፤ ቅዱሳንን/ቅዱሳትን ይመራ ዘንድ፤ ሥርዓትን፡ ይሠራ ዘንድ፤ ትንሣኤውንም ይገልጥ ዘንድ፣ ለመከራ ተሰጠ። |
| ት.ካ. አንሥ'ኡ እደዊክሙ ቀሳውስት! | ት.ካ. ቀሳውስት፡ እጆቻችሁን አንሡ! |
| ይ.ካ. በይእቲ ሌሊት፡ እንተ ባቲ፡ አመ ያገብእዎ፣ ነሥአ ኅብስተ፡ በእደዊሁ ቅዱሳት÷ ወብፁዓት፡ እለ እንበለ ነውር። | ይ.ካ. እርሱን ባስያዙባት፡ በዚያች ሌሊት፡ ነውር በሌለባቸው፡ ቅዱሳት÷ ብፁዓት በኾኑ እጆቹ፡ ኅብስቱን፡ አንሥቶ ያዘ። |
| ይ.ሕ. ነአምን፡ ከመ ዝንቱ፡ ውእቱ በአማን፡ ነአምን። | ይ.ሕ. እናምናለን፤ ይህ ቅዱስ ቍርባን፡ እንደዚያ፡ እውነት እንደኾነ እናምናለን። |
| ይ.ካ. አንቃዕደወ ሰማየ፡ ኀቤከ፣ ኀበ አቡሁ ወእሙ፣ አእኰተ፤ ባረከ፤ ወፈተተ። ወወሀቦሙ፣ ለእሊአሁ አርዳኢሁ። ወይቤሎሙ፡- "ንሥኡ! ብልዑ፣ ዝ ኅብስት፡ ሥጋየ ውእቱ! ለዘበእንቲአክሙ ይትፌተት፡ ለኅድገተ ኃጢኣት። | ይ.ካ. ወደአንተ ወደአባቱ፣ ወደአንቺም፡ ወደእናቱ፡ ወደሰማይ፡ ቀና ብሎ፡ አመሰገነ፤ ባረከ፤ ቈረሰ። "ንሡ! ብሉት! ይህ ኅብስት፡ ለኃጢኣት ማስተስረያ ሊኾን፡ ስለእናንተ የሚፈተት፡ ሥጋዬ ነው!" ብሎ፡ ለወገኖቹ፡ ለደቀ-መዛሙርቱ ሰጣቸው። |
| ይ.ሕ. አሜን፣ አሜን፣ አሜን፣ ነአምን፡ ወንትአመን፤ ንሴብሓከ፣ ኦ እግዚእነ፣ ወአምላክነ፣ ከመ ዝንቱ፡ ውእቱ በአማን፣ ነአምን። | ይ.ሕ. በእውነት፣ በእውነት፣ በእውነት እናምናለን፤ እንታመናለንም። ፈጣሪያችን እና ንጉሣችን ሆይ! እናመሰግንሃለን። ይህ ኅብስት፡ እንደዚያ ሥጋህ፡ እውነት እንደኾነ እናምናለን። |
| ይ.ካ. ወከማሁ፡ ጽዋዓኒ፡ አእኰቶ፣ ባሪኮ፣ ወቀዲሶ፣ መጠዎሙ፣ ለእሊአሁ አርዳኢሁ። ወይቤሎሙ፡- "ንሥኡ! ስትዩ!፣ ዝ ጽዋዕ፡ ደምየ ውእቱ፣ ለዘበእንቲአክሙ ይትከዐው፡ ለቤዛ ብዙኃን። | ይ.ካ. እንዲሁም፡ ጽዋዉን አመስግኖ፣ ባርኮ እና ቀድሶ፣ "ንሡ! ጠጡት! ይህ የጽዋ ወይን፡ለብዙ ሰዎች ቤዛ ሊኾን፡ ስለእናንተ የሚፈስስ ደሜ ነው!" ብሎ፡ ለወገኖቹ፡ ለደቀ-መዛሙርቱ ሰጣቸው። |
| ይ.ሕ. አሜን፣ አሜን፣ አሜን፣ ነአምን፡ ወንትአመን፤ ንሴብሓከ፣ ኦ እግዚእነ፣ ወአምላክነ፣ ከመ ዝንቱ፡ ውእቱ በአማን፣ ነአምን። | ይ.ሕ. በእውነት፣ በእውነት፣ በእውነት እናምናለን፤ እንታመናለንም። ፈጣሪያችን እና ንጉሣችን ሆይ! እናመሰግንሃለን። ይህ ወይን፡ እንደዚያ ደምህ፡ እውነት እንደኾነ እናምናለን። |

**ይ.ካ.** ሶበ ትገብርዎ ለዝንቱ፣ ተዝካረ ዚአየ ግበሩ!
**ይ.ሕ.** ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ! ወትንሣኤከ ቅድስተ፤ ነአምን ዕርገተከ፤ ወዳግመ ምጽአተከ። ንሴብሐከ፤ ወንትአምነከ፤ ነአኵተከ፤ ወንባርከከ። ኦ! እግዚእነ፤ ወአምላክነ።

**ይ.ካ.** ይእዜኒ እግዚኦ፡ ንዜከር ሞተከ፤ ወትንሣኤከ ንትአመነከ፤ ወናቀርብ ለከ፡ ዘንተ ኅብስተ፤ ወዘንተ ጽዋዐ፡ እንዘ ነአኵተከ። ወቦቱ ረሰይከ ለነ ለተድላ፤ ንቁም ቅድሜከ፣ ወለከ ንትከሀን። ነአኵተከ እግዚኦ፤ ወንሴብሐከ፤ እስመ ፈነውከ፡ ቅዱሰ መንፈሰ፤ ወኃይለ፡ ዲበ ዝንቱ ኅብስት፤ ወላዕለ ዝንቱ ጽዋዕ። ይረስዮ፡ ሥጋሁ፥ ወደሞ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ፡ ኢየሱስ መሲሕ፤ ለዓለመ ዓለም።

**ይ.ሕ.** አሜን፤ እግዚኦ አድኃንከነ፤ እግዚኦ አስተሳለምከነ፤ እግዚኦ ተሣሃልከነ።

**ት.ካ.** በኵሉ ልብ፡ ናአኵቶ፣ ለእግዚአብሔር አምላክነ፤ ኅብረተ-መንፈስ ቅዱስ ሠናየ፡ እስመ ጸገወነ።
**ይ.ሕ.** በከመ ሀሎ፡ ህልወ፣ ወይሄሉ፤ ለትውልደ-ትውልድ፤ ለዓለመ ዓለም።
**ይ.ካ.** ደሚረከ ተሀቦሙ፣ ለኵሎሙ፡ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ፤ ይኩኖሙ ለቅድሳት፤ ወለምልአተ መንፈስ ቅዱስ፤ ወለአጽንዖ ሃይማኖት፡ ዘበአማን፣ ከመ ኪያከ ይቀድሱ፤ ወይወድሱ፤ ወወልደከከ፣ ወፍቁረከ፡ ኢየሱስ መሲሕ፣ ዘምስለ መንፈስ ቅዱስ።
**ይ.ሕ.** አሜን።

**ይ.ካ.** *(ሕዝቡ፡ ከካህኑ ጋር፡ በዜማ ይጸልዩት)*
ሀብከነ ንኅበር፡ በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ። ወፈወስከነ፣ በዝንቱ ቅዱስ ቍርባን። ከመ ብከ ንሕየው፤ ዘለኵሉ ዓለም፤ ወለዓለመ ዓለም። ቡሩክ ስሙ፡ ለእግዚአብሔር፤ ወቡሩክ፡ ዘመጽአ፡ በስመ-እግዚአብሔር፤ ወተባረከ፤ ስመ-ስብሓቲሁ፤ ለይኩን፤ ለይኩን፣ ቡሩክ ለይኩን። ፈነውከ፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ።

**ይ.ካ.** ይህን ሥርዓት በምትፈጽሙበት ጊዜ፡ የእኔን መታሰቢያ አድርጉ!
**ይ.ሕ.** አቤቱ! የሞትህን፣ የቅድስት ትንሣኤህንም ዜና እንናገራለን። ዕርገትህን፣ ዳግም ምጽአትህንም፡ እናምናለን። ፈጣሪያችንና አምላካችን ሆይ! እናመሰግንሃለን፣እንታመንብሃለን፤ እናገንሃለን፤ እናወድስሃለንም።
**ይ.ካ.** እግዚአብሔር ሆይ! አኹንም፡ ሞትህን እና ትንሣኤህን እናስባለን፤ እንታመንብሃለን። እያመሰገንንህ፡ ይህን ኅብስት፣ ይህንም ጽዋ፡ እናቀርብልሃለን። በፊትህ፡ እንቆም ዘንድ፣ አንተንም እናገለግል ዘንድ፣ በሱ፡ ተድላን አደረግህልን። የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፣ የካህናችንና የንጉሣችን፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ ሥጋው እና ደሙ ያደርገው ዘንድ፡ ቅዱስ መንፈስህን፣ ኃይልህንም፡ በዚህ ኅብስት እና በዚህ ጽዋ ላይ ስለላክህ፡ ነአኵተከ እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን፤ እናገንሃለን፤ ለዘለዓለም ዓለም።

**ይ.ሕ.** አሜን፤ እግዚአብሔር ሆይ! አዳንኸን፤ እግዚአብሔር ሆይ! ሰላምህን መለስህልን፤ እግዚአብሔር ሆይ! ይቅር አልኸን።
**ት.ካ.** አምላካችን እግዚአብሔር፤ መልካሙን የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ስለሰጠን፡ በፍጹም ልብ እናመስግነው!
**ይ.ሕ.** ቀድሞ ይኖር እንደነበረ፣ አኹንም፣ ወደፊትም፡ከትውልደ-ትውልድ፤ ለዘለዓለም ይኖራል።
**ይ.ካ.** ከሱ ለሚቀበሉ ኹሉ፡ ለቅድስና እና መንፈስ ቅዱስን ለመመላት፣ እውነተኛውንም ሃይማኖት ለማጽናት፡ አንድ አድርገህ ሰጠሃቸው። አንተን ይቀድሱ እና ያወድሱ ዘንድ፤ ልጅህን፣ ወዳጅህን፡ ኢየሱስ መሲሕንም፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ።
**ይ.ሕ.** አሜን።
**ይ.ካ.** *(ሕዝቡ፡ ከካህኑ ጋር፡ በዜማ ይጸልዩት)*
በቅዱስ መንፈስህ፡ አንድ የመኾንን ጸጋ ሰጠኸን። ለዘለዓለም፡ ጤናማ እና ሕያዋን ኾነን እንኖር ዘንድ ኾነን እንኖር ዘንድ፡ በዚህ ቅዱስ ቍርባን ፈወስከን። የእግዚአብሔር ስሙ፡ ምስጉን ነው፤ በእግዚአብሔር ስም የመጣውም ምስጉን ነው፤ የጌትነት ስሙም ተመሰገነ፤ ይኹን፤ ይኹን፣ ምስጉን ይኹን። በዚህ ቍርባንህ፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ፡ በየሰውነታችን ላይ አሳደርክ።

| | |
|---|---|
| **ት.ካ.** *(በዜማ)* ንትነሣእ ለጸሎት፤<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* እግዚኦ: ንሴብሓከ!<br>**ይ.ካ.** *(በዜማ)* ሰላም ለኵልነ፤<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ምስለ መንፈስ ቅዱስ። | **ት.ካ.** ለጸሎት እንነሣ!<br>**ይ.ሕ.** እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን!<br>**ይ.ካ.** ሰላም ለኹላችን ኾነ!<br>**ይ.ሕ.** ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ። |
| **ይ.ካ.** *(ጸሎተ ፈትቶ፡- የቅዱስ ቍርባኑ መሥዋዕት ማከናወኛ ጸሎት።)* ወካዕበ ነአኵት! ዘኵሎ ይእኅዝ፡ እግዚአብሔር አብወእም፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ፡ ኢየሱስ መሲሕ፤ ከመ የሀበነ፡ በበረከት፣ ንንሣእ ዘእምቅዱስ ምስጢር፣ ጽንዓተ ለነ፡ የሀበነ። ወኢመነሂ እምውስቴትነ፡ ኢያርስሕ። አላ ለኵሎሙ፡ ተድላሆሙ ይረሲ፡ ለእለ ይትሜጠዉ፡ ንሥአተ ቅዱስ ምስጢር፣ ዘሥጋሁ ወደሙ ለመሲሕ፣ ዘኵሎ ይእኅዝ፡ እግዚአብሔር አምላክነ። | **ይ.ካ.** *(ጸሎተ ፈትቶ፡- የቅዱስ ቍርባኑ መሥዋዕት ማከናወኛ ጸሎት።)* ዳግመኛም፡ ኹሉን የያዘ የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፣ የካህናችንና የንጉሣችን፡ የኢየሱስ መሲሕን አባትእናት፡ እግዚአብሔር አብወእምን እናመሰግናለን። ከቅዱስ ምስጢረ-ቍርባኑ፡ በበረከት እንቀበል ዘንድ እንድንበቃ፡ መጽናቱን ሰጠኸን። ኹሉን የያዘው የአምላካችን የእግዚአብሔር መሲሕ ሥጋ እና ደም የኾነው፡ ይህ ምስጢረ-ቍርባን፡ ለሚቀበሉት ኹሉ፡ ተድላን የሚያደርግላቸው ስለኾነ፡ ከእኛ መካከል፡ ማንንም እንደማያጐሣቍል እናምናለን።፡ |
| **ት.ካ.** *(በዜማ)* ሰብሑ!<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* አቡነ ዘበሰማያት! ተቀደሰ ስምከ። መጽአት መንግሥትከ። ኮነ ፈቃድከ፡ በከመ በሰማይ፥ ከማሁ፡ በምድር። ሲሳየነ ዘለለዕለትነ፡ ሀብከነ ዮም። ኅደግከ ለነ፡ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፤ ከመ ንሕነኒ፡ ንኅድግ፡ ለዘአበሰ ለነ። ኢአባእከነ፡ እግዚኦ ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅንከነ፤ ወባልሓከነ፡ እምኵሉ እኩይ። እስመ ዚአከ፣ ይእቲ መንግሥት፤ ኃይል፤ ወስብሓት። ለዓለመ ዓለም። አሜን። | **ት.ካ.** *(በዜማ)* አመስግኑ!<br>**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* አባታችን ሆይ! በሰማያት የምትኖር! ስምህ ተቀደሰ። መንግሥትህ መጣች። በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ኾነ። የዕለት ምግባችንን፡ ለዛሬ ሰጠኸን። ኃጢኣታችንንና በደላችንን ይቅር አልኸን፤ እኛም፡ የበደሉንን፡ ይቅር እንል ዘንድ። አቤቱ፡ ወደፈተና አላገባኸንም፤ ከክፉው ኹሉ፡ አዳንከን፥ ታደግኸን እንጂ። ይህች መንግሥት፥ ኃይልና ምስጋናም፡ የአንተ ናቸው፤ ለዘለዓለሙ። አሜን። |
| + + + | + + + |
| *(በንባብ)* ኦ ማርያም እምነ ዘበሰማያት! ሰላም ለኪ! በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ። ድንግል በመንፈስኪ፤ ወበነፍስኪ፣ ወበሥጋኪ።<br>እመ እግዚአብሔር ጸባዖት፡ ሰላም ለኪ!<br>ቡርክት አንቲ እምአንስት፤ ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ። ተፈሥሒ፡ ፍሥሕት! ኦ ምልእተ ጸጋ! በእግዚአብሔር እምናኪ፥ ወበፍቁር ወልድኪ፡ ኢየሱስ መሢሕ፡ ገበርኪ ለነ፡ ምሕረተ። ወሰረይኪ ለነ፡ ኃጣውኢነ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን። | *(በንባብ)* እናታችን ማርያም ሆይ! በሰማያት የምትኖሪ!በመልአኩ፡ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ "ሰላም!" እንልሻለን። በመንፈስሽ እና በነፍስሽ፤ በሥጋሽም፡ ድንግል ነሽ። የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ሆይ! ሰላምታ፡ ለአንቺ ይገባል። ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ አንቺ፡ የተመሰገንሽ ነሽ። የማሕፀንሽም ፍሬ፡ የተመሰገነ ነው። የደስታ ምንጭ፥ ጸጋንም የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ! በእግዚአብሔር እናትነትሽ፥ በተወደደውም ልጅሽ፡ በኢየሱስ መሢሕ፡ ምሕረትን አደረግ ሽልን። ኃጢኣታችንንም፡ አስተሰረይሽልን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን። |

**ይ.ካ.** እግዚአብሔር አምላክነ፣ ዘኮሎ ትእኅዝ፤ ንሥአተ፡ ዘቅዱስ ምስጢር፣ ጽንዓተ ለነ ተሀበነ፤ ወኢመነሂ እምውስቴትነ፡ ኢያርስሕ። አላ ኮሎ ባርክ፡ በመሲሕ፤ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ፤ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ፤ ስብሓት፥ ወእኂዝ፤ ይእዜኒ፣ ወዘልፈኒ፤ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

**ይ.ሕ.** በከመ ምሕረትከ አምላክነ! ወአኮ በከመ አበሳነ! *(ሦስት ጊዜያት)*

**ት.ካ.** *(በዜማ)* ንትነሣእ ለጸሎት፤
**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* እግዚኦ: ንሴብሓከ!
**ይ.ካ.** *(በዜማ)* ሰላም ለኵልነ፤
**ይ.ሕ.** *(በዜማ)* ምስለ መንፈስ ቅዱስ።

**ይ.ካ.** *ሥጋ* ቅዱስ ዘበአማን፤ ዝ ውእቱ ዘእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህነነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ እምእግዝእትነ፣ ወእምነ፣ ወመድኃኒትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ-አምላክ፤ ዘይትወሀብ፡ ለሕይወት፣ ወለመድኃኒት፣ ወለስርየተ ኃጢኣት፡ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ በአሚን!
**ይ.ሕ.** አሜን።
**ይ.ካ.** ደም ክቡር ዘበአማን፤ ዝ ውእቱ ዘእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህነነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ እምእግዝእትነ፣ ወእምነ፣ ወመድኃኒትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ-አምላክ፤ ዘይትወሀብ፡ ለሕይወት፣ ወለመድኃኒት፣ ወለስርየተ ኃጢኣት፡ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ በአሚን!
**ይ.ሕ.** አሜን።
**ይ.ካ.** እስመ ዝንቱ ውእቱ፡ ቅዱስ *ሥጋሁ*፣ ወክቡር ደሙ፡ ለአማኑኤል አምላክነ፡ ዘበአማን፣ ዘነሥአ እምእግዝእትነ፣ ወእምነ፣ ወመድኃኒትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ-አምላክ!
**ይ.ሕ.** አሜን።

**ይ.ካ.** ኹሉን የያዝህ፡ አምላካችን እግዚአብሔር! ከቅዱስ ምስጢረ-ቊርባኑ፡ እንቀበል ዘንድ እንድንበቃ፡ መጽናቱን ሰጠኸን። በመሲሕ፡ ኹሉን እንደምትባርክ እንጂ፡ ከእኛ መካከል፡ ማንንም እንድማታጐሣቊል እናምናለን። በእርሱ ያለ ክብር፡ ለአንተ ይገባል፤ ከእርሱ ጋራ፤ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ፤ ዛሬም፤ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።
**ይ.ሕ.** አምላካችን ሆይ! እንደምሕረትህ እንጂ፣ እንደኃጢአታችን አይደለም! *(ሦስት ጊዜያት)*
**ት.ካ.** ለጸሎት እንነሣ!
**ይ.ሕ.** እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን!
**ይ.ካ.** ሰላም ለኹላችን ኾነ!
**ይ.ሕ.** ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ።

**ይ.ካ.** ይህ፡ ከእርሱ አምነው ለሚቀበሉ ኹሉ፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን፥ ሰላማችን፣ ካህናችንና ንጉሣችን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእግዝእተብሔር እናታችን፣ ከመድኃኒታችን እና ከአምላክ እናት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው፣ ለዘለዓለም ሕይወት እና ለመድኃኒትነት፣ ለኃጢኣት ማስተስረያም የተሰጠ፡ በእውነት ቅዱስ *ሥጋ* ነው።
**ይ.ሕ.** አሜን።
**ይ.ካ.** ይህ፡ ከእርሱ አምነው ለሚቀበሉ ኹሉ፡ ፈጣሪያችንና አምላካችን፥ ሰላማችን፣ ካህናችንና ንጉሣችን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእግዝእተብሔር እናታችን፣ ከመድኃኒታችን እና ከአምላክ እናት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው፣ ለዘለዓለም ሕይወት እና ለመድኃኒትነት፣ ለኃጢኣት ማስተስረያም የተሰጠ፡ በእውነት ክቡር ደም ነው።
**ይ.ሕ.** አሜን።
**ይ.ካ.** ይህ፡ በእውነት፡ አምላካችን አማኑኤል፡ ከእግዝእተብሔር እናታችን፣ ከመድኃኒታችን እና ከአምላክ እናት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው፣ ቅዱስ *ሥጋ* እና ክቡር ደም ነውና።
**ይ.ሕ.** አሜን።

| | |
|---|---|
| **ይ.ካ. ነአምን! ነአምን! ነአምን! ወንትአመን! እስከደኃሪት እስትንፋስ፤ ከመ ዝንቱ ውእቱ፡ ሥጋሁ፥ ወደሙ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዘነሥአ እምእግዝእትነ፣ ወእምነ፣ ወመድኃኒትነ፡ ቅድስት ድንግል በሠለስት፣ ማርያም ወላዲተ-አምላክ። ወረሰዮ አሐደ፡ ምስለ መለኮቱ፡ ዘእንበለ ቱስሕት፣ ወኢትድምርት፡ ዘእንበለ ፍልጠት፣ ወኢውላጤ፤ ወኮነ ሰማዕተ፡ በስምዕ ሠናይ፣ በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፤ ወመጠዎ በእንቲአነ፣ ወበእንተ ሕይወተ ኵልነ።** | **ይ.ካ. እናምናለን! እናምናለን! እናምናለን! እስከመጨረሻዩቱ እስትንፋስም እንታመናለን! ፈጣሪያችንና አምላካችን፥ ሰላማችን፣ ካህናችንና ንጉሣችን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በሦስት ወገን፡ ድንግል ከኾነች፣ ከእግዝእተብሔር እናታችን፣ ከመድኃኒታችን እና ከአምላክ እናት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው፣ ሥጋው እና ደሙ፡ ይህ እንደኾነ። ያለመቀላቀል እና ያለመዳበል፣ ያለመለዋወጥ እና ያለመለየት፡ ከመለኮቱ ጋራ፡ አንድ ያደረገው። በጴንጤናዊው፡ በጲላጦስ ዘመን፡ በመልካም ምስክርነት፡ ምስክር የኾነ። ስለእኛ እና ስለኹላችንም ሕይወት፡ አሳልፎ የሰጠው።** |
| **ይ.ሕ. አሜን።** | **ይ.ሕ. አሜን።** |
| **ይ.ካ. ነአምን! ነአምን! ነአምን! ወንትአመን! ከመ ኢተፈልጠ መለኮቱ፡ እምትስብእቱ፡ ኢአሓተ ሰዓተ፣ ወኢከመ ቅጽበተ-ዓይን፤ አላ፡ መጠዎ በእንቲአነ፡ ለሕይወት፣ ወለመድኃኒት፣ ወለስርየተ-ኃጢኣት፣ ለእለ ይትሜጠዉ እምኔሁ በአሚን።** | **ይ.ካ. እናምናለን! እናምናለን! እናምናለን! መለኮቱ፡ ከሰውነቱ፡ ለአንዲት ሰዓት፣ ለአንዲት የዓይን ቅጽበትም እንኳ እንዳልተለየ እንታመናለን። ስለእኛ፣ ከእርሱ፡ አምነው ለሚቀበሉም፡ ለሕይወት እና ለመድኃኒት፣ ለኃጢኣት ማስተስረያም ሊኾን፡ አሳልፎ ሰጠው እንጂ።** |
| **ይ.ሕ. አሜን።** | **ይ.ሕ. አሜን።** |
| **ይ.ካ. ነአምን! ነአምን! ነአምን! ወንትአመን! ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ፣ ወደሙ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ። ዝ ውእቱ፣ ዘሎቱ ይደሉ፣ ክብር፥ ወስብሓት፥ ወስግደት፡ ምስለ አቡሁ፡ ኄር፣ ሰማያዊ፣ ወእሙ፣ ኄርት፣ ሰማያዊት፣ ወመንፈስ ቅዱስ፡ ማኅየዊ፤ ይእዜኒ፣ ወዘልፈኒ፤ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።** | **ይ.ካ. እናምናለን! እናምናለን! እናምናለን! የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የሰላማችን፣ የካህናችንና የንጉሣችን፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ ሥጋው እና ደሙ፡ ይህ እንደኾነ እታመናለሁ። ክብር እና ምስጋና፣ ስግደትም፡ ቸር ከኾነ፡ ሰማያዊ አባቱ ጋራ፣ ቸሪት ከኾነች፡ ከሰማያዊት እናቱ ጋራ፣ ሕያው ካደረገን፡ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ። ዛሬም፣ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።** |

**ይ.ካ.** *ሠራዒው ካህን፡ ቅዱስ ቍርባን የሚቀበሉ ኪዳናውያን እና ኪዳናውያት፡ የመቅረቢያ ጸሎታቸውን፡ በየግላቸው፣ በለኆሳስ (በቀስታ) እንዲጸልዩ ያስታውቃል።*

**ይ.ሕ.** *ቅዱስ ቍርባን የሚቀበሉ፡ ከግል ጸሎታቸው ጋር እንዲጸልዩት የቀረበ ጸሎት።*

ካህኔ እና ንጉሤ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሆይ! የዓለም መድኃኒት ከኾነችው፡ ከእናትህ፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የወረስኸውን፣ አንተም፡ በመስቀል የቤዛነት መከራህ፡ ለፍጥረትህ መልሰህ ያቀዳጀኸውን ሰላም ያስገኘልኝን፡ ቅዱስ ሥጋህን እና ክቡር ደምህን ለመቀበል እየቀረብሁ ነኝና፡ እርኵሰት ከኾነች፡ ከሰውነቴ ጠፈር በታች፡ ትገባ ዘንድ፡ የሚገባኝ አይደለም። እኔ አሳዝኜሃለሁና፣ በፊትህም፡ ክፉ ሥራን ሠርቼአለሁና፤ በአርአያህ እና በአምሳልህ የፈጠርኸውን ነፍሴን፣ ሥጋዬን እና መንፈሴን፡ ሥርዓትህን እና ቃልህን በመተላለፍ፡ አሳድፌአለሁና፤ ምንም ምን በጎ ምግባር የለኝምና። ነገር ግን፡ እኔን በመፍጠርህ፣ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ምሥዋዐ መድኃኒትነት እና በአንተ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ሰላመ-መስቀል ቤዛነት፡ በተገኘው በቅዱሱ ኪዳን ምሕረትም፣ ከማናቸውም ኃጢአት እና በደል፣ መርገም እና ርኵሰት ኹሉ ስለነጻሁ፣ በዚህ መለኮታዊ ቸርነት፡ በታላቅ ደስታ ተመልቼ እያመሰገንሁህ፣ ቅዱሱን ቍርባን ልቀበል እነሆ ቀርቤአለሁ። ስለዚህ፡ አንተም፣ ቅድስት እናትህም፡ እንደተቀበላችሁኝ አምናለሁ። የቅድስናችሁ ምስጢር የኾነውን፡ ይህን ቅዱስ ሥጋ እና ክቡር ደም በተቀበልሁ ጊዜ፡ በእርሱ፡ የኃጢአቴን ስርየት፣ መለኮታዊዉን ይቅርታ እና ምሕረት፣ የዘለዓለም ሕይወትንም እንዳገኘሁ ያረጋገጥሁበት እንጂ፡ ለወቀሳ እና ለመፈራረጃ እንደማይኾንብኝ አምናለሁ። ክብር እና ምስጋና፥ ኃይል እና መንግሥት፡ ለእግዚአብሔር አብወእም፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፤ ለዓለመ-ዓለም፤ አሜን።

*ሠራዒው ካህን፡ ቅዱስ ሥጋውን፣ ራሱ ተቀብሎ፡ ለሌላው በሚያቀብልበት ጊዜ፣ ረዳቱም ካህኒት፡ ክቡር ደሙን፡ ራሷ ተቀብላ፡ ለሌላዩቱ በምታቀብልበት ጊዜ፡ እንዲህ ይበሉ! ተቀባዮቹም፡ "አሜን!" ይበሉ!"*

| | |
|---|---|
| **ይ.ካ.** ኅብስተ ሕይወት፡ ዘወረደ እምሰማያት፡ ቅዱስ ሥጋሁ፡ ለኢየሱስ መሲሕ፣ ዘነሥአ እምእግዝእትነ፡ ወእምነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ-አምላክ!<br>**ይ.ሕ.** አሜን።<br>**ይ.ካ.** ጽዋዐ ሕይወት፡ ዘወረደ እምሰማያት፡ ክቡር ደሙ፡ ለኢየሱስ መሲሕ፣ ዘነሥአ እምእግዝእትነ፡ ወእምነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ-አምላክ!<br>**ይ.ሕ.** አሜን። | **ይ.ካ.** ኢየሱስ መሲሕ፣ ከእግዝእተብሔር እናታችን እና ከአምላክ እናት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው፣ ከሰማያት የወረደ፡ የሕይወት ኅብስት የኾነው፡ ቅዱስ ሥጋው እነሆ!<br>**ይ.ሕ.** አሜን።<br>**ይ.ካ.** ኢየሱስ መሲሕ፣ ከእግዝእተብሔር እናታችን እና ከአምላክ እናት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው፣ ከሰማያት የወረደ፡ የሕይወት ጽዋ የኾነው፡ ክቡር ደሙ እነሆ!<br>**ይ.ሕ.** አሜን። |

*<u>**ቀዳስያኑ፡**</u> ቅዱሱን ቍርባን ይዘው ለማቀበል፡ ከመንበሩ፡ ወደሕዝቡ ዘወር ብለው በሚቆሙበት ግዜ፡ ረዳኢቷ ካህኒት፡ ጽዋውን፡ እንዲህ በሚል ቃል፡ ከሠራዒው ካህን ከተቀበለች በኋላ፡ ይህን መመሪያ፡ በዜማ ታስሰማለች፡-*

| | |
|---|---|
| **ት.ካ.** *(በንባብ)፡* **ጽዋዐ ሕይወት፡ እትሜጦ። ወስመ እግዚአብሔር እጼውዕ።**<br>*(ወእምዝ፡ ትብል፡ በዜማ!)*<br>**ሰብሑ! በእንቲአነ፤ ወበእንተ ኵሎሙ ደቂቀ-ኢትዮጵያ፤ እለ ይቤሉነ፡- "ግበሩ! ተዝካሮሙ በሰላም፣ ወበፍቅረ ኢየሱስ መሲሕ፡።" ግነዩ! ወዘምሩ!** | **ት.ካ.** *(በንባብ)፡***የሕይወት ጽዋን እቀበላለሁ። የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ።**<br>*(ከዚህ በኋላ፡ ይህን፡ በዜማ ትበል!)*<br>**አመስግኑ! ስለእኛ እና "መታሰቢያቸውን፡ በኢየሱስ መሲሕ ሰላም እና ፍቅር አድርጉ!" ስላሉን ስለኢትዮጵያ ልጆች ኹሉ፡ አመስግኑ! ዘምሩ!** |

*ቀዳስያኑ፡ ድርገት ወርደው፡ቅዱስ ቍርባንን የማቀበሉ ሥርዓት በሚካኼድበት ጊዜ፡ ካህናቱ እና ሕዝቡ፡ በኅብረት፡ እንዲህ እያሉ ይዘምራሉ።*

| | |
|---|---|
| **ይ.ሕ. ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ሥሉስ፣ ዘኢይትነገር።**<br>**ሀብከነ ከመ ንንሣእ፡ ለሕይወት፣ ዘንተ ሥጋ፣ ወደመ፡ ዘእንበለ ኵነኔ።**<br>**ሀብከነ ንግበር ፍሬ፡ ዘያሠምረከ፣ ከመ ናስተርኢ በስብሓቲከ፣ ወንሕየው ለከ፤ እንዘ ንገብር፡ ዘዚአከ ፈቃደ።**<br>**በተአምኖ፡ ንጸውአከ አብወእም፤ ወንጼውእ መንግሥተከ። ተቀደሰ እግዚኦ፡ ስምከ በላዕሌነ፤ እስመ ኃያል አንተ፤ እኩት፣ ወስቡሕ፤ ወለከ ስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም።** | **ይ.ሕ. የማይነገር ሦስትነት ያለህ፡ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ።**<br>**ይህን ሥጋ እና፣ ደም፡ ሕይወት ሊኾነን፡ ሳይፈረድብን፡ እንቀበለው ዘንድ ሰጠኸን። ደስ የሚያሰኝህን የንስሓ ፍሬን በማፍራት፡ በጌትነትህ እንድንገለጽ፡ የአንተንም ፈቃድ እየፈጸምን እንኖርልህ ዘንድ ሰጠኸን።**<br>**በአንተ፡ በአብወእም ታምነን፡ አንተንም፣ መግሥትህንም እንጠራለን። እግዚአብሔር ሆይ! ስምህ፡ በእኛ ላይ ተመሰገነ። ምስጉን፣ የምትኾን፡ ኃያል፡ አንተ ነህና፡ "ለአንተ፡ ክብር ይገባሃል!" እያልን እናመሰግንሃለን፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።** |

*ይ.ሕ. ቅዱስ ቍርባንን የተቀበሉ ኹሉ፡ እያንዳንዳቸው፡ በየግላቸው ይጸልዩት ዘንድ፡ ይኸ የምስጋና ቃል ቀርቦላቸዋል፡-*

የእግዚአብሔር አባታችን እና የእግዝእተብሔር እናታችን፡ ልጅ የኾንኸው፡ አንተ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሆይ! ኃጢአቴንና በደሌን ለማስተስረይ፣ መድኃኒት እና የዘለዓለም ሕይወትን ለመውረስ ይኾነኝ ዘንድ፡ ዓለምን ካዳነችው፡ ከእናትህ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣኸውን፣ ለእኔም፡ ፍጹሚን ሰላምህን ልታጐናጽፈኝ እና ልታቀዳጀኝ፡ በመስቀል ላይ የቆረስኸውን፡ ቅዱስ ሥጋህን እና ያፈሰስኸውን፡ ክቡር ደምህን፡ እነሆ ተቀበልሁ።

ሰውን የምትወድድ፡ እግዚአብሔር ወልድ ዋህድ ሆይ! የሚገባህን ምስጋና፡ እኔም፡ እንደሚገባኝ አቀርብልህ ዘንድ፡ ለዚህ ኹሉ ፍቅርህ እና የቸርነት ጸጋህ፡ የሚበቃ ምስጋናህን፡ በልቡናዬ እና በአንደበቴ ምላ። ቀድሞውንም፡ አንተ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተፀንሰህ እና ተወልደህ፡ ሰው የኾንኸው፣ በዚያም ሰውነት የተገለጽኸው፡ ለዘለዓለሙ ታድነኝ ዘንድ ነውና። ስለቅዱስ ስምህም፡ ለዘለዓለሙ አዳንኸኝ።

ፈጣሪዬ እና አምላኬ፣ ካህኔ እና ንጉሤ፣ ሰላሜ እና ወንድሜ፡ ኢየሱስ መሲሕ ሆይ! በአገልጋዮችህ በካህኑ እና በካህኒቱ እጅ፡ ቅዱስ ሥጋህን እና ክቡር ደምህን፡ አንድ አድርገህ ለሰጠኸኝ፡ ለአንተ፡ ፍጹም ምስጋና ይገባሃል። አዎን! እኔን፡ ጠፍቼ፡ እቅበዘበዝ የነበርሁትን ኃጢአተኛ፡ ጥፋቴን ኹሉ፡ ይቅር ብለህ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" ከኾኑት ኪዳናውያት እና ኪዳናውያን ጋራ፡ አንድ እኾን ዘንድ፣ በበጎችህም መካከል፡ እንደአንዱ ተቆጥሬ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትህ፡ አንዱ ዜጋህ እኾን ዘንድ ስለተቀበልኸኝ፡ አመሰግንሃለሁ፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

ይ.ዲ. ነአኵቶ ለእግዚአብሔር፤ ቅድሳቶ ነሢአነ፣ ከመ ለሕይወተ ነፍስ፣ ይኩነነ ፈውሰ፤ ዘተመጦነ፡ ንሰብሖ፥ ወንትመሓፀን፣ እንዘ ንሴብሖ፡ ለእግዚአብሔር አምላክነ።

ይ.ካ. ናሌዕለከ፡ አምላክነ፥ ወንጉሥነ፤ ወንባርክ፡ ለስምከ ለዓለም፤ ወለዓለመ ዓለም።

ይ.ሕ. አቡነ፥ ወእምነ፡ ዘበሰማያት፡ ኢ.አባእከነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

ይ.ዲ. ተመጦነ እምሥጋሁ ቅዱስ፣ ወእምደሙ ክቡር፡ ለመሲሕ።

ይ.ካ. ኵሎ አሚረ፡ ንባርከከ፤ ወንሴብሖ፡ ለስምከ ለዓለም፤ ወለዓለመ ዓለም።

ይ.ሕ. አቡነ፥ ወእምነ፡ ዘበሰማያት፡ ኢ.አባእከነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

ይ.ዲ. ወናእኵቶ፣ ይደልወነ፡ ከመ ንሳተፍ፡ ምስጢረ፡ ክብርተ፥ ወቅድስተ።

ይ.ካ. ስብሓተ-እግዚአብሔር፡ ይነግር አፉየ፣ ወኵሉ ዘሥጋ፡ ይባርክ፡ ለስሙ ቅዱስ፤ ለዓለም፤ ወለዓለመ ዓለም።

ይ.ሕ. አቡነ፥ ወእምነ፡ ዘበሰማያት፡ ኢ.አባእከነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

ይ.ካ. ወካዕበ፡ ናአኵት ዘኵሎ ይእኅዝ፡ እግዚአብሔር፡ አብወእም፡ ለእግዚእ፣ ወሰላምነ፡ ኢየሱስ መሲሕ። ነአኵተከ፡ እስመ ከፈልከነ ንንሣእ፡ ዘእምቅዱስ ምስጢርከ፤ ኢኮነ ለርስሓት፥ ወኢለኵነኔ፤ አላ ለሓድሶ ነፍስ፣ ወሥጋ፣ ወመንፈስ። በአሓዱ ወልድከ፣ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ፤ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ፤ ስብሓት፥ ወእኂዝ፣ ይእዜኒ፣ ወዘልፈኒ፤ ወለዓለመ ዓለም።

ይ.ሕ. አሜን።

ይ.ዲ. ለነፍሳችን፡ ሕይወትን፣ ለሰውነታችንም ፈውስን የሚሰጠንን፡ ቅዱስ ቊርባንን፡ እነሆ ተቀበልን። ስለዚህ፡ አምላካችን እግዚአብሔር፡ በዚህ ጸጋው እንደሚያጸናን በመተማመን እናመሰግነዋለን።

ይ.ካ. አምላካችን እና ንጉሣችን ሆይ! ገናና የኾነ፡ ቅዱስ ስምህን፡ ከፍ አድርገን እየጠራን፡ ለዘለዓለም፡ ስናመሰግንህ እንኖራለን።

ይ.ሕ. የሰማያት አባታችን እና እናታችን ሆይ! አቤቱ! ወደፈተና አላገባኸንም።

ይ.ዲ. እነሆ! ከመሲሕ፡ ከቅዱስ ሥጋው፣ ከክቡር ደሙም ተቀበልን።

ይ.ካ. ዘወትር እናመሰግንሃለን፤ ቅዱስ ስምህንም፡ ለዘለዓለም ስንጠራ እንኖራለን።

ይ.ሕ. የሰማያት አባታችን እና እናታችን ሆይ! አቤቱ! ወደፈተና አላገባኸንም።

ይ.ዲ. የክብርት፥ ቅድስት ምስጢረ ቊርባኑን ማዕድ ለመሳተፍ ስላበቃን፡ ልናመሰግነው ይገባናል።

ይ.ካ. አንደበቴ፡ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል፤ የሥጋ ፍጥረትም ኹሉ፡ ቅዱስ ስሙን፡ ለዘለዓለሙ ያመሰግናል።

ይ.ሕ. የሰማያት አባታችን እና እናታችን ሆይ! አቤቱ! ወደፈተና አላገባኸንም።

ይ.ካ. ዳግመኛ፡ ኹሉን የያዝህ፡ የፈጣሪያችን እና የሰላማችን፡ የኢየሱስ መሲሕ፡ አባት-እናት፡ እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን። እነሆ! ቅዱስ ምስጢርህ ከኾነው፡ ሥጋህ እና ደምህ፡ እንቀበል ዘንድ አድለኸናልና። እሱም፡ ነፍሳችንን እና ሥጋችንን፣ መንፈሳችንንም ለማደስ ኾነልን እንጂ፣ ለፍዳ፥ ወይም ለፍርድ አልኾነብንም። በአንዱ ልጅህ፣ በእርሱ ያለ ክብር፣ ጽንዕ፡ ለአንተ ይገባል፤ ከእርሱ ጋራ፤ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ፤ ዛሬም፣ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ።

ይ.ሕ. አሜን።

# <u>ክፍል ስድስት፤</u>

## <u>የሥርዓተ ተክሊሉ ማብቂያ ጸሎት።</u>

*አዲሶቹ ባልና ሚስት፡ በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነትና መሪነት፡ ጥልቅ ፍላጎታቸው ለተፈጸመባት፡ ለዚች ቀን ያበቃቸውን ቸሩ ፈጣሪያቸውን፡ ከነቅድስት እናቱ እንደቆሙ በማመስገን፡ <u>የኢትዮጵያ ልጆች፡ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን፡ የምስጋና ጸሎት</u> እና <u>ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የሰላምታ ጸሎት፡</u> በሠራዒው ካህን መሪነት፡ ከዕድምተኞቻቸው ጋር ዐብረው ይጸልያሉ።*

| <u>ጸሎተ ስባሔ ለእግዚአብሔር፡ ዘደቂቀ ኢትዮጵያ።</u> | <u>የኢትዮጵያ ልጆች፡ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የምስጋና ጸሎት።</u> |
|---|---|
| አ አቡነ፥ ወእምነ፥ ወእኅትነ፥ ወእኁነ፥ ወመንፈስነ-ቢጽ እግዚአብሔር! ነአኵተከ እግዚኦ፥ ወንሴብሓከ፤ ንባርከከ እግዚኦ፥ ወንትአምነከ፤ ንገኒ ለከ እግዚኦ፥ ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ፤ ንሰግድ ለከ፤ አ ዘለከ! ይሰግድ ኵሉ ብርክ፤ ወለከ ይትቀነይ፡ ኵሉ ልሳን።<br>አንተ ውእቱ፡ አምላከ አማልክት፤ ወእግዚአ አጋእዝት፤ ወንጉሠ ነገሥት። አምላክ አንተ፡ ለኵሉ ዘሥጋ፤ ወለኵላ ዘነፍስ፤ ወለኵሉ ዘመንፈስ።<br>ወንጼውዐከ፣ በእንተ ዘተወከፍከ ዝንቱ ጸሎትነ፡ በቤዝዎቱ ለወልድከ፡ ዘመሀረነ ለሊሁ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ እንዘ ይብል፡- "አንትሙሰ፡ ሶበ ትጼልዩ፡ ከመዝ በሉ፡- 'አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ! ትምጻእ መንግሥትከ! ወይኩን ፈቃድከ፡ በከመ በሰማይ፡ ከማሁ በምድር! ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፡ ሀበነ ዮም! ሕድግ ለነ፡ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፣ ከመ ንሕነኒ ንሕድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ! ኢታብአነ እግዚኦ፡ ውስተ መንሱት! አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ፡ እምኵሉ እኩይ! እስመ ዚአከ፡ ይእቲ መንግሥት፥ ኃይል፥ ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም።'" | አባታችንና እናታችን፥ እኅታችንና ወንድማችን፥ ባልንጀራ-መንፈሳችንም፡ እግዚአብሔር ሆይ! አቤቱ እንቀድስሃለን፤ እናመሰግንሃለንም፤ አቤቱ እናወድስሃለን፤ እንታመንብሃለን፤ አቤቱ እናገንሃለንም፤ ለቅዱስ ስምህ እንታዘዛለን፣ እንሰግድልሃለን፤ ጉልበት ኹሉ፡ ለአንተ ይሰግዳል፤ አንደበትም ኹሉ፡ ወደአንተ ይጮሃል።<br>አንተ፡ የአማልክት አምላክ ነህ፤ የገዢዎች ገዢ ነህ፤ የንጉሦችም ንጉሥ ነህ። አንተ፡ የሥጋዊው ኹሉ፥ የነፍሳዊው ኹሉ፥ የመንፈሳዊውም ኹሉ ወገን ፈጣሪ ነህ።<br>ልጅህ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ "እናንተ ስትጸልዩ፡ 'የሰማዩ አባታችን ሆይ! ስምህ ይቀደስ! መንግሥትህ ትምጣ! ፈቃድህ በሰማይ እንደኾነ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ይኹን! የየዕለቱን ምግባችንን፡ ስጠን ለዛሬ! ኃጢአታችንንና በደላችንን፡ ይቅር በለን! እኛም የበደሉንን፡ ይቅር እንደምንል! አቤቱ ወደፈተና አታግባን! ከክፉው ኹሉ፡ አድነን እንጂ! መንግሥት፡ የአንተ ናትና፥ ኃይልና ምስጋናም፤ ለዘለዓለሙ።' በሉ!" |

ወበእንተ ዘአብዛኀከ ለነ፡ ኂሩትከ፤ ወዘገበርከ ለነ፡ ምሕረትከ፤ ወዘፈጸምከ ለነ፡ ፍቅርከ፤ ወዘወሀብከነ ጸጋከ፡ ለከዊነ ሥጋነ፥ ወነፍስነ፥ ወመንፈስነ።

ወረደ ለነ፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፡ በምክንያተ ምሥዋዐ መድኃኒትነ፡ ዘእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፥ ወቤዛ መስቀለ-ሰላምነ፡ ዘእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ።

በእንተዝ ኮነ ይእዜ፡ ዘትሄሉ አንተ በምድር፣ አኮ በሰማይ ባሕቲቱ።

ወዓዲ፡ ተቀደሰ ስምከ በምድር።

ወመጽአት መንግሥትከ።

ፈቃድከ፡ ዘኮነ በሰማይ፡ ከማሁ፡ ኮነ በምድርኒ።

አስተዳለውከ በሥነ ፍጥረት፡ ምግበ ሥጋነ፡ ዘይበቍዕ ለመፍቅደ ኵሉ ሀልዎትነ፤ ወአኮ ሲሳይ ዘለለዕለትነ ባሕቲቱ።

ወመጦከነ በኵሉ ጊዜ፡ ሥጋሁ ቅዱስ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፣ ዘነሥአ እምእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፤ ዘኮነ ለነ፡ ምግበ ነፍስ፥ ወመድኃኒት፤ ዘይረስየነ ሕያዋነ ዘለዓለም። ወበውእቱስ፡ ደምሰስከ፥ ወኃደግከ ለነ፡ ኵሎ ኃጢአተነ፥ ወአበሳነ ግሙራ፥ ወዘኢማእዜ። ወከማሁ አባሕከነ፡ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ።

ወዐልዓልከነ፡ በልደትነ፡ እምጥምቀት፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ ወበእሳት፤ በዘውእቱ በጻሕነ፡ ከመ ንኩን ውሉድከ፥ ወአዋልድከ።

ብሎ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትህልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምህልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን።

ስለዚህ፡ አኹን፡ እኛም፡ ስምህን እየጠራን፡ እናመሰግንሃለን።

በመዳናችን ምሥዋዕ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና በሰላማችን የመስቀል ቤዛ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን።

ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ በምድርም፡ የምትኖር ኾንህ።

ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ።

መንግሥትህም መጣችልን።

በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ኾነ።

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ፡ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህ።

ለዘለዓለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንንም፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን። እርሱም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፤ ከእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም የነሣው ነው። በእርሱም፡ ኃጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደመሰስህ። ፈጽመህም ይቅር አልኸን። እኛም፡ የበደሉንን ኹሉ፡ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።

የአንተ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ለመኾን በበቃንበት፣ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት፡ ባቀዳጀኸን፡ የጥምቀት ልደታችን አከበርኸን።

ወበጸጋከ፡ ዘንስሓ።

ወአውጻእከነ፡ እመንሱት ዘዘኢአሁ።

ወአድኃንከነ፡ እምኵሉ እኩይ።

ወሞእከዎ፡ ለዲያብሎስ፡ አቡሃ ለሓሰት።

ወአሰሰልከ፡ ለሞት።

ወበእንተ ዝንቱ፡ አሠለጥከነ፡ ንሄሉ፡ በሕይወተ ቀዳሚት ትንሣኤከ ዘመንፈስ ቅድስት፥ ወበዓለመ ሰንበትከ ዘለዓለማዊት።

ኦ እግዚኦ! ንሴብሓከ ወትረ፡ በእንተ ኂሩትከ፥ ወምሕረትከ፥ ወፍቅርከ፥ ወጸጋከ፡ ዘአወፈይከነ፡ በዘኢይትከሃል ይትነገር መጠኖሙ። ወዓዲ፡ በእንተ ዘትሁበነ፡ ኵሎ ዘንፈቅድ፤ እንዘ አኮ ዘንሰአለከ።

ንጸንሕ፡ በከመ አሰፈውከነ፡ ለምጽአተ ዛቲ መዋዕል፡ እንተ ባቲ ትኼንን መንግሥትከ አማናዊት፡ ዘስማ፡ "ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ-እግዚአብሔር"፤ ዘትትመራሕ፡ በንግሥትነ፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ዘተብህለት፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"፥

ወበንጉሥነ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፥ ዘተብህለ፡ "ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!"፤ ወንሄሉ ንሕነ፡ ይእዜ፡ በውስቴታ፤ ወንትለአካ፤ ከመ ትትረአይ፥ ወትሰፍን በገሃድ፥ በዝንቱ ዓለም፡ እምድኅረ ትሜርዎሙ፡ ለእከይ፥ ወለኃጢአት፥ ወለሞት።

እስመ ለከ፡ ኃይል፥ ወስብሓት፥ ወመንግሥት። ይእዜኒ፥ ወዘልፈኒ፥ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

የንስሓንም ጸጋ አደልኸን።

ከማናቸውም ፈተና አወጣኸን።

ከክፉው ኹሉ አዳንኸን።

የሓሰቱን አባት ዲያብሎስንም፡ ድል አደረግህ።

ሞትንም አስወገድህ።

ልዩ በኾነችው፡ በመጀመሪያዋ የመንፈስ ትንሣኤ ሕይወት እና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ዓለም ለመኖር አበቃኸን።

እግዚአብሔር ሆይ! መጠኑ፡ ሊነገር ስለማይቻለው ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም፡ የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን።

"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ ክፋትን፥ ኃጢአትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን።

እርሷም፡ "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!" በተባለችው፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ንግሥትነት እና "የይሁዳው ነገድ አንበሳ፡ ድል ነሣ!" በተባለው፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ንጉሥነት የምትመራው፥ እኛም፡ ዛሬ የምንኖርባት፤ የምናገለግላትም፡ የእውነት መንግሥትህ ናት።

ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም፡ የአንተ ናቸው፤ ዛሬም፤ ዘወትርም፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## ጸሎተ ሱላሜ፡
## ለድንግል ማርያም፡
## ዘደቂቀ ኢትዮጵያ።

ኦ እግዝእተብሔር ማርያም እምነ፥ ወመድኃኒትነ!

ንብለኪ፡ "ሰላም ለኪ!" በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ።

ድንግል በመንፈስኪ፣ ወበነፍስኪ፣ ወበሥጋኪ። ይደልወኪ ዝ ሱላሜ፣ እስመ አንቲ፡ እሙ ለእግዚአብሔር ጸባዖት፡ በእንተ ዛቲ ንጽሓ ባሕርይኪ።

አንቲ ይእቲ፡ ሔዋን ቅድስት፤ ወቡርክት፡ እምኵሎን አንስት፡ በእንተ ዘአሥረፀ ማሕፀንኪ፡ ፍሬሁ፡ ዘዕፀ ሕይወት፣ በዘውእቱ ኮነ፡ አዳምሁ ቅዱሰ።

ተፈሥሒ! ኦ ንግሥትነ፡ በሰማይ፥ ወበምድር!

እስመ ዘተወደስኪ ጥንት፡ በአፈ ነቢያት፡ እንዘ ይብሉኪ፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ፡ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር!"፥

ወንሕነኒ በዘሀልዎትነ፡ እንዘ ንብለኪ፡ "እምነ ጽዮን!"

ንሴብሓኪ ወትረ፡ እንዘ ንብል፡ "ብፅዕት አንቲ፡ ኦ ምልእተ ጸጋ!"

እስመ ዐተበ እግዚአብሔር፡ ኪዳኖ ዘምሕረት፡ ለዓለመ ዓለም፡ በዘአጥረየኪ አንቲ፡ ለምክንያተ መድኃኒትነ።

ነአምን፡ ከመ ኢተግሕሠ ከመ እምኔነ፡ ማሕፀንተኪ፡ በአምጣነ እንተ ኢተግሕሠ፡ እምፍቁር ወልድኪ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፤ እስመ አንቲ ይእቲ፡ እምነ ዘምሕፅና፤ ወንሕነ፡ ውሉድኪ፥ ወአዋልድኪ፡ ዘምሕፅና፡ በቃለ አማሕፅኖ ዘወልድኪ፡እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ አምላክነ፥ ወሰላምነ።

ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ልዑል፡ በእንተ ዛቲ ኂሩቱ፡ ዘተገብረት ለነ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

\+ + +

## የኢትዮጵያ ልጆች፡
## ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት
## የሰላምታ ጸሎት።

እናታችንና መድኃኒታችን፡ እግዝእተብሔር ማርያም ሆይ!

በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ "ሰላም!" እንልሻለን።

በመንፈስሽ እና በነፍስሽ፣ በሥጋሽም፡ ድንግል ነሽ። በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ነሽና፡ ይህ ሰላምታ፡ ለአንቺ ይገባል።

ማሕፀንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፣ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ።

ቀድሞ በነቢያት፡ "ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ወደእግዚአብሔር ታደርሳለች!" የተባልሽ፥ እኛም፡ "እናታችን ጽዮን!" ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ!

እግዚአብሔር፡ አንቺን፡ የመዳናችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳነ ምሕረቱን፡ ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡ "ጸጋን የተመላሽ ሆይ! ብፅዕት ነሽ!" እያልን፡ ዘወትር እናመሰግንሻለን። በአምላካችንና በሰላማችን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ አንቺ፡ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፥ እኛም፡ ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ፡ ከእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም እንደማይለየን እናምናለን።

በዚህ ኹሉ፡ ለተደረገልን ቸርነት፡ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

\+ + +

*ፍሬ-ቅዳሴው አብቅቶ፡ "አሜን!" እንደተባለ፡ ኹሉም ተቀምጠው፡ የተረፈ-መሥዋዕቱ ተሳትፎ ተካኺዶ ሲፈጸም፡ የሥርዓታቱ ተካፋዮች ኹሉ ቆመው፡ የተክሊሉ እና የቅዳሴው ማጠቃለያ የኾኑትን፡ ከዚህ የሚከተሉትን፡ የቅዱሱ ኪዳን እና የሰንደቅ-ዓላማ፣ እንዲሁም፡ የ"አባታችን ሆይ" እና የ"እናታችን ሆይ!" የምስጋና መዝሙሮችን፡ ዐብረው በኅብረት ያሰሰሙ።*

## <u>የኢትዮጵያ ልጆች፡ የቅዱሱ ኪዳን መዝሙር</u>

፩. ሃሌ ሉያ ለአብ፡ ለሰማይ አባታችን፤
ስብሐት ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ካህን ንጉሣችን፤
ለመንፈስ ቅዱስም፡ ጸጋ ሕይወታችን፤
አቅርበናልና፡ በዝርጉ እጃችን፤
ጌታ ሆይ ተቀበል፡ ይኸው ምስጋናችን፤ ይኸው ምስጋናችን፡፡

፪. ሰላም ለማርያም፡ ጽዮን እናታችን፤
ኪዳነ ምሕረት፡ ድንግል ንግሥታችን፤
ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ቤተ መንግሥታችን፤
ርስትሽ ነንና፡ በሕዝብነታችን፤
ይሰማ በአርያም፡ ይኸ መዝሙራችን፤ ይኸ መዝሙራችን፡፡

፫. ለሰውነታችን፡ ለመንፈስ ምግባችን፤
ለሕመም መድኃኒት፡ ለደዌ ፈውሳችን፤
ከክፋት፥ ከኃጢአት፥ ከሞት መዳኛችን፤
በመከራ ጊዜ፡ ተስፋ መጽናኛችን፤
በእምነትና ምግባር፡ የትእግሥት ፍሬአችን፤ የትእግሥት ፍሬአችን፡፡

፬. ለግል፥ ለቤተሰብ፥ ለኅብረት ኑሮአችን፤
ለአንድነት፥ ለፍቅር፥ ለሰላም ግባችን፤
ለሰብአዊ መብት፥ ለፍትሕ ዋስትናችን፤
አጥቂ እንዳይጎዳን፡ አለኝታ ጋሻችን፤
ለድል-አድራጊነት፡ መሣሪያ ኃይላችን፤መሣሪያ ኃይላችን።

፭. ለዚህ ፊደላችን፡ ለግእዝ ቋንቋችን፤
ለእውቀት፥ ለጥበብ፥ ለሥልጣኔአችን፤
ለልማት፥ ለዕድገት፡ መሠረት ሕንፃችን፤
በተፈጥሮ ውበት፡ ገነት አገራችን፤
የምንኖርበት፡ ቅዱሱ ክብራችን፤ ቅዱሱ ክብራችን፡፡

፮. ለኖኅ ልጆች ውኅደት፡ የዘር ሓረጋችን፤
ለኢትዮጵያዊነት፡ መጠሪያ ስማችን፤
ለማንነታችን፡ ልዩ ማስረጃችን፤
በቀስተ ደመና፡ ነጻነት ልብሳችን፤
የማርያም መቀነት፡ ሰንደቅ ዓላማችን፤ ሰንደቅ ዓላማችን፡፡

፯. አንበሳው ክርስቶስ፡ ምልክት አርማችን፤
ካምላክ ያገኘነው፡ ሕገ መንግሥታችን፤
ማንም የማይነጥቀን፡ የሰማይ ወርቃችን፤
የምንጠብቀው፡ ያደራ ውርሳችን፤
ቅዱሱ ኪዳን ነው፡ ሕያዉ ቅርሳችን፥ ሕያዉ ቅርሳችን፡፡

## የኢትዮጵያ ልጆች፡ የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር።

*(ሙሽሮቹ፡ የኢትዮጵያን፡ የቅዱሱን ኪዳን ሰንደቅ ዓላማ፡*
*በመካከላቸው፡ አድርገው እና ከፊት ለፊታቸው ይዘው፡ ከኹሉም ጋር ዐብረው ይዘምሩት፡፡)*

ኢትዮጵያ ሆይ! (ድንግል ማርያም) ደስ ይበልሽ፤
በአምላክሽ ኃይል፣ በንጉሥሽ (በኢየሱስ መሲሕ)።
ተባብረዋልና ልጆችሽ (የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች)፤ አይነካም ከቶ ነጻነትሽ።
ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ (ቅዱሳንሽ)። አትፈሪም ከጠላቶችሽ።
የድል ሰንደቅ ዓላማችን፥ ይኑርልን ለክብራችን፡፡

### ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የምስጋና ጸሎት *(በመዝሙር)*

አባታችን ሆይ! የምትኖር በሰማይ፤
መንግሥትህ በስምህ፡ ሰፈነች በእኛ ላይ፥ ሰፈነች በእኛ ላይ፡፡
በሰማይ የጸናች፡ ሕያው ፈቃድህ፤
ተፈጸመች በምድር፡ በሥግው ቃልህ፥ በሥግው ቃልህ፡፡
ፍቅርህ ለምግባችን፡ ፍጥረትን የሰጠች፤
በደልን ደምስሳ፡ ዕርቅን መሠረተች፤ ዕርቅን መሠረተች፡፡
ጌታ ሆይ! አዳንከን፡ ከሞት ከፈተና፤
በልጅህ ቤዛነት፡ በትንሣኤው ፋና፥ በትንሣኤው ፋና፡፡
ኃይልና ምስጋና፡ ጸንተው ለመንግሥትህ፤
አበቃኸን እኛን፡ ለቅዱስ ኪዳንህ፥ ለቅዱስ ኪዳንህ፡፡

### ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ የሰላምታ ጸሎት *(በመዝሙር)*

እናታችን ሆይ! ማርያም ድንግል፥ ማርያም ድንግል፤
ሰላም እያልንሽ ነው፡ በገብርኤል ቃል፥ በመልአኩ ቃል፡፡
በሥጋ አካልሽ፡ በነፍስሽም አካል፥ ደግሞም በኅሊና፤
ባሕርይሽ ኾነ፡ ፍጹም ድንግልና፥ ፍጹም ድንግልና፡፡
ላሸናፊው አምላክ፡ ለእግዚአብሔር እናት፥ ለጌታ እናት፤
ማቅረብ ይገባናል፡ ሰላምታን በምነት፥ ሰላምታን በውነት፡፡
ከሴቶች መካከል፡ ባለሽ ቅድስና፥ ባለሽ ቅድስና፤
ማኅፀንሽ አፈራ፡ የሕይወትን መና፥ የሕይወትን መና፡፡
ደስ ይበልሽ አንቺ፡ የግዜር ባለጸጋ፥ ያምላክ ባለጸጋ፤
ልጆችሽ ተቤዠን፡ በመስቀሉ ዋጋ፤ በመስቀሉ ዋጋ።

## <u>ክፍል ሰባት።</u>

## <u>የሥርዓተ ተክሊሉ መዝጊያና ማሰናብቻ ቡራኬ</u>

*ሙሽራውና ሙሽሪቱ፣ ዕድምተኞቻቸውም ኹሉ እንደተቀመጡ፡ ሠራዒው ካህን፡ ሙሽሮቹን፡ "እንኳን ለዚህ አበቃችሁ!" ቤተሰቦቻቸውን እና ዘመዶቻቸውን፣ ወዳጆቻቸውንም፡ "እንኳን ደስ አላችሁ!" በማለት፡ መልካም ስሜቱን ይገልጽላቸዋል።*

*ለሙሽሮቹ፣ ለጉባኤውም፡ አጭር የማበረታቻና የምክር ቃልን ካበረከታቸው በኋላ፡ ከዚህ የሚከተለውን፡ የማሰናበቻ ሥርዓተ-ጸሎት እና ቡራኬ በማካኼድ፡ ጠቅላላው የተክሊሉ ሥርዓት የተፈጸመ መኾኑን፡ በረዳቱ ካህኒት፡ መመሪያ፡ የጥሪ ቃል፡ በይፋ ያሳውቃል፡-*

| | |
|---|---|
| **ት.ካ.** አድንኑ አርእስቲክሙ/አርእስቲክን፡ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ! በእደ-ገብሩ ካህን፡ ከመ ይባርክሙ/ይባርክን! | **ት.ካ.** አገልጋዩ በሚኾን፡ በካህኑ እጅ፡ ይባርካችሁ ዘንድ፡ በፈጣሪያችን፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ እየራሳችሁን፡ ዝቅ ዝቅ አድርጉ! |
| **ይ.ሕ.** በእደ-ገብሩ ካህን፡ አሜን ይባርከነ! | **ይ.ሕ.** በአገልጋዩ፡ በካህኑ እጅ፡ በእውነት ይባርከናል። |
| **ይ.ካ.** *(እንዘ ይቀውም፡ በአንጻረ-ሕዝብ፣ ወሰፍሐ እደዊሁ፡ በትእምርተ-መስቀል፣ ወይባርክ፡ በ፫ቱ መንገለ ገጻት፡ ፫ተ ጊዜ፡ ላዕለ ሕዝብ፡ በመስቀልናሁ፡ ዘለሊሁ፤ ወይብል፡ ዝንተ ቃለ-ቡራኬ፣ ፫ተ ጊዜ፡-)* | **ይ.ካ.** *(ፊት-ለፊቱን፡ ወደጉባኤው መልሶ፡ በራሱ መስቀልነት፡ እጆቹን፡ በሦስት አግጣጫ እያመሳቀለ እና ይህን የቡራኬ ቃል፡ ፫ ጊዚያት፡ መላልሶ እያስሰማ፡ ሕዝቡን ያባርካል።)* |
| ኦ እግዚኦ! አድኅንከ ሕዝበከ! ወባረከ ርስተከ! ረዓይኮሙ፣ ወአልዓልኮሙ፡ እስከለዓለም።<br>ወዐቀብካ፡ ለኢትዮጵያ፡ መንግሥተ-እግዚአብሔር ቅድስት፡ እንተ መሠረትካ፣ ወአጥረይካ፣ ወቤዘውካ፡ በሥጋሁ ቅዱስ፣ ወበደሙ ክቡር፡ ለዋሕድ ወልድከ፡ እግዚእነ፥ አምላክነ፥ ወሰላምነ፣ ወካህንነ፣ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ።ወጸዋዕካ፡ ትኩን ማኅደረ፡ ለቤተ-ሕዝባ፣ ወለቤተ-ምልክናሃ፣ ወለቤተ-ክህነታ።<br>እለ መጻእክሙ/መጻእክን፣ ወእለ ተጋባእክሙ/ ተጋባእክን፣ ወለእለ ጸለይክሙ/ጸለይክን፣ እለ በላእክሙ/በላእክን፡ ሥጋሁ ቅዱሰ፣ ወእለ ሰተይክሙ/ ሰተይክን፡ ደሞ ክቡረ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፡ኢየሱስ መሲሕ ውስተ ዛቲ ቤተ መቅደስ፡ ኮነ ለክሙ፥ ወለክን፡ ጸጋ ወበረከት፣ ፍቅር፥ ወሰላም፣ ፍሥሓ፥ ወሓሤት፡ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን። | እግዚአብሔር ሆይ! ሕዝብህን አዳንህ! ርስትህንም ባረክህ! እስከለዓለምም ጠበቅሃቸው! ከፍ ከፍም አደረግሃቸው! ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትህንም ጠበቅሃት! እርሷም፡ አንተ፡ በአንዱ ልጃችሁ፡ በፈጣሪያችንና በአምላካችን፥ በሰላማችን፣ በካህናችንና በንጉሣችን፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ የመሠረትሃት፣ ባለቤቷ የኾንሃት፣ በቅዱስ ሥጋው እና በክቡር ደሙም፡ የተቤዠሃት ናት። አጠቃላይ፡ የነፍስ አገልግሎት ዘርፏ የኾነው፡ ቤተ-ሕዝቧ እና የሥጋዊው አገልግሎት ዘርፏ የኾነው፡ ቤተ-ምልክናዋ፣ የመንፈሳዊው አገልግሎት ዘርፏ የኾነው፡ ቤተ-ክህነትዋም፡ በውስጧ ደርጅተው እንዲሠሩ፡ ማደሪያቸው ትኾን ዘንድ የጠራሃት ናት።።<br>ወደዚች ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ቤተ-መቅደስ መጥታችሁ፣ ተሰብስባችሁ፡ የጸለያችሁ፣ የፈጣሪያችንንና የአምላካችንን፡ የኢየሱስ መሲሕን ቅዱስ ሥጋ የበላችሁ እና ክቡር ደሙን የጠጣችሁ ኹሉ፡ ጸጋ እና በረከት፣ ፍቅር እና ሰላም፣ ተድላ እና ደስታ ኾነላችሁ! ለዘለዓለሙ፤ አሜን። |

ረድኤት ወበረከት: ዘነቢያት ወሓዋርያት፥ ዘጻድቃን ወሰማዕታት፥ ዘቅዱሳን ዕደው ወዘቅዱሳት አንስት፥ ዘትጉሃን መላእክት ወዘሊቃነ መላእክት፤

ኃይል ወሞገስ: ዘትስብእቱ ወልደቱ፥ ዘግዝረቱ ወበአተ መቅደሱ፥ ዘስደቱ ወተልእኮቱ፥ ዘጥምቀቱ ወተመክሮቱ፥ ዘትምህርቱ ወተአምራቱ፥ ዘሕማማተ መስቀሉ ወሞቱ፥ ዘመቃብሩ ወትንሣኤሁ፥ ዘዕርገቱ ወምጽአቱ፥ ወዘዘለዓለም መንግሥቱ: ለፈጣሪነ ወአምላክነ ወለእግዚእነ ወለሰላምነ፥ ወለካህነ ሊቀ ካህናቲነ፥ ወለንጉሥ ንጉሠ ነገሥትነ ኢየሱስ መሲሕ፤

ኪዳን ዘምሕረት ወፍቅር: ለእግዝእትነ ወለእምነ፥ ወለመድኃኒትነ፥ ወለንግሥትነ፥ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥

ጸጋ ዘእግዚአብሔር አብ፥ ኂሩት ዘእግዚአብሔር ወልድ፥ ሱታፌ ዘእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ: የሀሉ ምስለ አንትሙ ክልኤክሙ፥ ወምስለ ሰብአ ቤትክሙ፥ ወፍቁራኒሆሙ፥ ወምስለ ኵልነ: ለዓለመ ዓለም።

ይ.ካ. *(ወእምዝ ይበል: ሰፊሖ እዴሁ: ላዕለ ሕዝቡ:-)* እግዚአብሔር ሀለወ: ምስለ ኵልነ!

ይ.ሕ. ምስለ መንፈስ ቅዱስ። አሜን: እግዚአብሔር ባረከነ: ለአግብርቲሁ ኪዳናውያን፥ ወለአዕማቲሁ ኪዳናውያት በሰላም። ስርየተ ኮነነ፤ ዘተመጦነ ሥጋከ፥ ወደመከ። አብሓከነ: በመንፈስ ቅዱስ: ንኪድ ኵሎ ኃይሎ: ለጸላኢ። በረከተ እዴክ ቅድስት: እንተ ምልእተ-ምሕረት፤ ኪያሃ ረከብነት ኵልነ። እምኵሉ: ምግባረ እኩይ: አግኅሥከነ። ወውስተ ኵሉ: ምግባረ ሠናይ ደመርከነ።

ቡሩክ: ዘወሀበነ: ሥጋሁ ቅዱሰ፤ ወደሞ ክቡረ። ጸጋ ነሣዕነ፤ ወሕይወተ ረከብነ: በኃይለ መስቀሉ: ለኢየሱስ መሲሕ። ኪያከ እግዚኦ: ነአኵት፤ ነሂአነ ጸጋ: ዘእመንፈስ ቅዱስ።

ት.ካ. እትዉ በሰላም።

የነቢያት የሓዋርያት የጻድቃን የሰማዕታት የቅዱሳን ዕደው የቅዱሳት አንስት፥ የትጉሃን መላእክት፥ የሊቃነ መላእክት: ረድኤትና በረከት፥

የፈጣሪያችንና የአምላካችን፥ የእግዚአብሔራችንና የሰላማችን፥ የካህን ሊቀ ካህናታችን፥ የንጉሥ ንጉሠ ነገሥታችን: የኢየሱስ መሲሕ: የትስብእቱና የልደቱ፥ የግዝረቱና የበአተ መቅደሱ፥ የስደቱና የአገልግሎቱ፥ የጥምቀቱና የፈተናው፥ የትምህርቱና የተአምራቱ፥ የመስቀሉና የሞቱ፥ የመቃብሩና የትንሣኤው፥ የዕርገቱና የምጽአቱ፥ የዘለዓለም መንግሥቱም ኃይልና ሞገስ፥

አምላክን የወለደች: የእግዝእተብሔራችንና የመድኃኒታችን፤ የእናታችንና የንግሥታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የቃል ኪዳን ምሕረትና ፍቅር፥

የእግዚአብሔር አብወእም ጸጋ፥ የእግዚአብሔር ወልድ ቸርነት፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድነት: ከእናንተ ከኹለታችሁ፥ ይህን ተክሊላዊ የጋብቻ በዓላችሁን ለማክበር ከተገኙላችሁ: ቤተሰቦቻችሁና ወዳጆቻችሁም፥ ከኹላችንም ጋር ይኹን! ለዘለዓለሙ።

ይ.ካ. *(ከዚህ በኋላ: እጆቹን: በሕዝቡ ላይ ዘርግቶ: ይህን ይበል:-)* እግዚአብሔር: ከኹላችን ጋር አለ።

ይ.ሕ. ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ። በእውነት: እግዚአብሔር: እኛን: ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቹን እና ነጋሚዎቹን፤ ካህናቶቹንም [አገልጋዮቹንም] በሰላም ባረከን። የተቀበልነው ሥጋህ እና ደምህ: ለስርየት ኾነን። የጠላትን ኃይል ኹሉ: በመንፈስ ቅዱስ: እንረግጥ ዘንድ አሠለጠንኸን። ምሕረትን የተመላች: ቅድስቲቱን የእጅህን በረከት: ኹላችን: አገኘናት። ከክፉው ግብር ኹሉ: አራቅኸን። በበጎው ምግባር ውስጥም ኹሉ: ተሳታፊዎች አደረግኸን።

ቅዱስ ሥጋውን፤ ክቡር ደሙንም የሰጠን ፈጣሪያችን: ቸር ነው። በኢየሱስ መሲሕ:በመስቀሉ ኃይል: ጸጋን: ተቀበልን፤ ሕይወትንም: ተረከብን። እግዚአብሔር ሆይ! የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ: እንዲህ ተቀብለናልና: እናመሰግንሃለን።

ት.ካ. በሰላም: ወደየቤታችሁ ግቡ!

*ሙሽሮቹና ዕድምተኞቻቸው ኹሉ "አሜን" ይላሉ።*

እዚህ ላይ፡ በሌሎች የኦርቶዶክስ ሃይማኖተኞች ዘንድ፡ በሚደረገው ልማድ ዓይነት፡ ካህኑ፡ መስቀል ይዞ፥ ወይም፡ ቀኝ እጁን እያሳለመ፡ ሕዝቡን፡ አይባርክም። በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ እንዲህ ያለው የባዕዳን ወግ አይሠራም፤ አይፈቀድምም።

ይኸውም፡ ከምሥራቹ (ከወንጌሉ) ቃል ምንባብ በኋላ፡ የሰው እጅ የጻፈውን መጽሓፍ-ቅዱስ ከመሳለም ይልቅ፣ የእግዚአብሔር እጅ ሠርቶት እና አዘጋጅቶት፡ ሕያው ቃሉን የጻፈበትን፡ የአንባቢውን ካህን፡ ሕያው የሰውነት ግንባር መሳሙ፡ የበለጠ አግባብነት እንዳለው ታውቆ፣ በዚሁ መሠረት እየተፈጸመ እንደኾነ ይታወሳል። እንደዚያ ኹሉ፣ አኹንም፡ በኦርቶዶክሳውያኑ ሃይማኖተኞች ዘንድ፡ መስቀል በማሳለሙ እና በመሳለሙ ረገድ፡ በሚደረገው፡ ልማድ ፈንታ፡ በተግባር ላይ የሚውለው ኢትዮጵያዊው ሥርዓት ይኾናል።

ይኼም ሥርዓት፡ መጽሓፍ ቅዱሱን የመሳለሙ ባዕድ ልማድ፡ ኢትዮጵያዊዉን መልክ እና መንፈስ እንዲከተል በማድረግ፡ የታየውን ፍሬያማ ውጤት፡ እዚህም ላይ ማጽናት፡ እንደሚገባ፡ የሚያሳስበው ነው። እርሱም፡ ቀደም ብሎ የሠፈረው፡ እንዲህ የሚለው ማብራሪያ ያስረዳል፦ "ሙሽራውና ሙሽሪቷ፡ ስለእግዚአብሔር ቃል አክብሮት፡ የምሥራቹ ሕያው መለኮታዊ መጽሓፍ የኾነውን፡ ራሱን፡ የአንባቢውን ካህን ግንባር የመሳማቸው ሥርዓት ነው። ይህ ኢትዮጵያዊ ሥርዓት አረጋግጦ የሚያመለክተው እውነታ፡ ለመለኮታዊው እውነት ማደሪያና ምንጭ ኾኖ በፈጣሪ የተሠራው፣ ብቸኛውና የታመነው፣ የእግዚአብሔር መጽሓፍ፡ የፍጡር እጅ የጻፈው መጽሓፍ ሳይኾን፡ የፈጣሪ መመሪያ ቃል እንደሚያሳስበው፡ ራሱ፡ የሰብአዊው ፍጡር ሰውነት መኾኑን ነው።"

ከዚህ የተነሣ፡ አኹን፡ ሠራዒው ካህን፡ የሰው እጅ የሠራውን መስቀል ይዞ ሳይኾን፥ ወይም፡ ቀኝ እጁን ብቻ እያሳለመ ሳይኾን፡ እጆቹን ወደጎኖቹ አመሳቅሎ እና ዘርግቶ፡ ራሱ፡ የእግዚአብሔር ሕያው መቅደስ የመኾኑ ጸጋ ያስገኘለትን **ሕያው መስቀልነቱን በማቅረብ፤** ሙሽሮቹና ዕድምተኞቻቸው፡ ወደመንበሩ ፊት-ለፊት እየመጡ፡ ደረቱን እንዲስሙ፡ ራሱን ያቀርብላቸዋል። እነርሱም፡ እያንዳንዳቸው፡ አንዳችም፡ የስግደትን መልክ እና ይዘት ፈጽመው ሳያሳዩ፡ **የሕያው መስቀልነቱ ማእከል የኾነውን ደረቱን ብቻ** እያሳለማቸው ያሰናብታቸዋል።

ከዚህ በኋላ፡ መልስ ኾኖ፡ ለበዓሉ አግባብነት ያላቸው፡ **"ንሴብሖ ለእግዚአብሔር!"** እና **"በቃና ዘገሊላ!"** የሚሉት፣ እነርሱንም የመሰሉት ወረቦች እየተዘመሩ፣ በሽብሸባ እና በይባቤ፡ አክሊላቸውን እንደተቀዳጁ ያሉት ሙሽሮች፡ በዕድምተኞቻቸው ታጅበው ወደውጭ ያመራሉ።

በዚህ ስንብት፡ በቤተ መቅደስ የሚካኼደው የበዓሉ ሥነ ሥርዓት ፍጻሜ ይኾናል።

\+ \+ \+

# የሠርጉ በዓል አከባበር መርሐ ግብር፡ ከዚህ ይቀጥላል።

## ኹለተኛ፡

<u>የበዓለ-ከብካቡ ዕለት</u>፡- እሑድ፡ ዕለተ-ሰንበት ዝልፍት፣ ነሓሴ ፳፩ ቀን፥ ፳፻፱ ዓ. ም.

<u>ጊዜው</u>፡- ከዋዜማው ዕለተ-ሰንበት፣ ነሓሴ ፳ ቀን፥ ፳፻፱ ዓ. ም. ከጧቱ ፫ ሰዓት፡ እስከ ማግሥቱ፣ እሑድ፡ ዕለተ-ሰንበት ዝልፍት፣ ነሓሴ ፳፩ ቀን፥፳፻፱ ዓ. ም. ከንጋቱ ፲፪፤ እስከ ምሽቱ ፲፪ ሰዓት ድረስ።

<u>የመርሐ-ግብሩ ዝርዝር፡-</u>

፩. ሙሽሮቹ፡ በዋዜማው፡ ነሓሴ ፳ ቀን፥ ፳፻፱ ዓ. ም. በሰንበት፡ ከጧቱ <u>በ፫ ሰዓት</u>፣ በደንገጡሮቻቸውና በሚዜዎቻቸው፣ በሠርገኞቹም ታጅበው፡ ወደዟይ ደሴት ለመጓዝ፡ ከመኖሪያ ቤታቸው ይነሣሉ።

፪. ምሳ፡ በዙዋይ ከተማ ቤተ-ነግድ ተበልቶ፣ ከጥቂት ዕረፍት በኋላ፡ ከብካባዊው ጉዞ፡ በተዘጋጀው ጀልባ፡ ወደደብረ-ጽዮን ደሴት ይቀጥላል።

እዚያ ሲደርሱ፡ የደሴቲቱ ነዋሪዎች በኾኑት ወላጆችና ቤተሰቦች፥ ዘመዶችና ወዳጆች፡ ለሙሽሮቹና ለዐጃቢዎቻቸው ሠርገኞች: ተገቢው አቀባበል ይደረግላቸዋል። የራት መስተንግዶው እና ዐዳር፡ በዚያው፡ በደሴቲቱ ላይ ይኾናል።

፫. ሙሽሮቹ እና ዐጃቢዎቻቸው ሠርገኞች፡ ከንጋቱ፡ በ፲፪ ሰዓት፡ በደብረ ጽዮን፡ ቅድስት ማርያም ሰበካ ቤተ-ክርስቲያን ተገኝተው በማስቀደስ፡ ቅዱስ ቍርባንን ይቀበላሉ።

፬. ይህች ሰበካ ቤተ-ክርስቲያን፡ በተለይ፡ ሙሽራው፡ ተወልዶ በሕፃንነት ያደገባት፣ ተምሮም፡ እስከዲቁና ክህነት ያገለገለባት በመኾኗ፣ ዛሬ፡ ከዘለዓለማዊት የሕይወት ጓደኛው ሙሽሪት ጋር፡ ኹለቱንም፡ ለዚህ፡ ኹለንተናዊ ወግ-ማዕርግ ለኾነው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ጋብቻ ጸጋና በረከት ስላበቃቻቸው፣ እርሷን፡ እናታቸውን፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን ተሳልመውና እግሮቿን ስመው፡ ፍቅራቸውንም ይገልጹላታል። አዎን! ለዚችው፡ ለሰማይዋ እናታቸው፡ ፍጹሙን የሓሤት ደስታቸውን፡ በእውነተኛው፡ የመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው በማበርከት፡ የተለየ ምስጋናቸውን ያቀርቡላታል።

፰. በቤተ-ክርስቲያን የሚደረገው የስብሓተ-እግዚአብሔሩ [የምስጋናው እና የሓሜቱ] ሥርዓተ-ጸሎት እንዳበቃ፣ ሙሽሮቹ፡ በዚያች ሰበካ ቤተ-ክርስቲያን ላሉ ካህናትና የኔብጤዎች ወንድሞችና እኅቶች ባዘጋጁት፣ በሠርጉ የምስጋና ድግስ ላይ፡ ተጋባዦቻቸውን ለማስተናገድ፡ ወደዚያ ያመራሉ። በዚያም፡ ሙሽሮቹ፡ በአካለ-ሥጋ ተገኝተው፥ እነዚያን የተጠሩ እንግዶቻቸውን ይጋብዛሉ።

ሙሽሮቹ፡ ይህን ሲያደርጉ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸውና እንደታወቀው፣ እንደኾነውም፡ እኒያ፡ በቃና ዘገሊላ የሠርግ በዓል ላይ የታደሙት፣ ያንንም በዓል የባረኩትና የቀደሱት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከዚህ በቀደመው ሥርዓተ-ተክሊልና ሥርዓተ-ቅዳሴ ላይ በመንፈስ-ቅዱስ ተገኝተው፡ ሥርዓታቱን እንደባረኩላቸውና እንደቀደሱላቸው ዅሉ፡ አኹንም፡ እኒሁ፡ የፈጠሯቸውና የዘለዓለም ወላጆቻቸው የኾኑት እናት እና ልጅ፣ በዚህ የሠርግ ግብዣ ላይ ተገኝተው፡ ይህን የምስጋና ገበታ እንደሚባርኩላቸውና እንደሚቀድሱላቸው አምነው ነው።

፱. በዚያ የሚካኼደው፡ ይህ ቃና ዘገሊላዊው የማዕድ ሥርዓት እንዳበቃ፡ ሙሽሮቹ፡ በዕድምተኞቻቸው እንደታጀቡ፡ የእርሷን፡ የዘለዓለማዊት እናታቸውን፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን እና የዘለዓለማዊ አባታቸውን፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ብቻ ሳይኾን፡ በዚያ የተገኙትን የባለአደራዎቹን ወላጆቻቸውን ጉልበት ጭምር በመሳለም፣ በእነርሱም ተስመው በመመረቅ ይሰናበታሉ።

፲. በዚያ ያሉትን፡ የቤተ-ክርስቲያኗን ቅዱሳትና የታሪክ ቅርሶች፣ መዘክሮችም በመጐብኘት፣ የሥነ-ፍጥረት ውበቶችንና ድንቆችንም፡ እየተዘዋወሩ ይመለከታሉ።

እንዲህ፣ ሓይቁን እና ደሴቲቱን አካትቶ በሚያሳየው ከፍታ ላይ ኾነው፡ የሓይቁን እና የደሴቲቱን መሓልና ዙርያ፣ አካባቢም በመቃኘት፡ የተወሰነ፡ የሠርግ መዝናኛ ጊዜን አሳልፈው ሲያበቁ፡ የመልስ ጉዞው፡ በመጡበት መልክና ይዘት፡ ወደዐዲስ-አበባ ይደረጋል። እርሱም፡ ከእራት ግብዣ በኋላ፣ ሠርገኞቹ፡ ሙሽሮቹን፡ ከመኖሪያ ቤታቸው በማድረስ ይከናወንና፡ ዅለተኛው የጊዜው መርሓ ግብር፡ በዚሁ ይፈጸማል።

\+ + +

## ሦስተኛ፤

**የሠርጉ ድግስ ዕለት፡-** ዕለተ-ሰንበት፤ መስከረም ፲፫ ቀን፥ ፳፻፲ ዓ. ም.
**ጊዜው፡-** ከንጋቱ ፲፪ እስከማታው ፪ ሰዓት።
**የመርሐ-ግብሩ ዝርዝር፡-**

፩. እስከጥዋቱ ፪ ሰዓት ድረስ፤ ሙሽሮቹ፡ በያሉበት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ፈጣሪያቸውና አምላካቸው፡ የምስጋና ጸሎትን ያቀርባሉ።

፪. ጥዋት በ፫ ሰዓት፤ ሙሽራው፤ ሚዜዎቹ እና ዐጃቢዎቹ፡ በሓኪም ዘርፉ ቤት* ይገኛሉ። በዚያ፡ የቊርስ ግብዣ ይደረጋል።

፫. ጥዋት በ፬፡፲፭ ሰዓት፤ የሠርገኛው ጉዞ፡ ወደሙሽሪት ቤት ይጀመራል።

፬. በረፋዱ ፭ እስከቀትሩ ፯ ሰዓት፤ በሙሽሪቷ የደመቀው ሠርገኛ፡ ሙሽሮቹን ዐጅቦ፡ አካባቢውን፡ በከብካባዊው ደስታና በወርኃዊው መዝናናት እያደነቀ በመመልከት፡ ጉዞውን፡ ወደሳሬም ቤተ-ነግድ* ያመራል።

፭. ከቀኑ ፭፡ ፴፭ እስከቀትሩ ፯ ሰዓት፡ የሙሽሮቹ ወላጆች፡ በሳሬም ቤተ-ነግድ ተገኝተው፡ የሠርጉን ታዳሚዎችና ሙሽሮቹን ከነሠርገኞቻቸው ይቀበላሉ። ከዚህ በኋላ፡ ለሠርጉ ድግስ የተሰናዳው የምሳ ገበታ ግብዣ፡ እስከ፲ ሰዓት ድረስ ይካኼዳል።

በዚያም ግብዣ ላይ፡ የምግቡን እና የመጠጡን፤ የዘፈኑን እና የእስክስታውን፤ ሌላውንም፡ በመልክ-ጼዴቅ ቃል-ኪዳን የሚፈጸመውን፡ የዳቦ መቊረሱንና የስም-ማውጣቱን፤ የጒልበት መሳሙንና የምርቃት አሰጣጡን አቀራረብ በሚመለከት፡ የሚካኼደው የሠርጉ ኅብረተሰብአዊ ሥርዓት፡ የሙሽሮቹን ወላጆች ፍላጎትና ደስታ ያሚላ፤ ኢትዮጵያዊው ባህል ይታይበታል።

ይህም ሲኾን፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸውና እንደታወቀው፤ እንደኾነውም፡ እኒያ፡ በቃና ዘገሊላ የሠርግ በዓል ላይ የታደሙት፤ ያንንም በዓል የባረኩትና የቀደሱት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በእኒህ ሙሽሮች ልጆቻቸው ሥርዓታተ-ተክሊል እና ቅዳሴ ላይ በመንፈስ-ቅዱስ ተገኝተው፡ ሥርዓታቱን እንደባረኩላቸውና እንደቀደሱላቸው ኹሉ፡ አኹንም፡ እኒሁ፡ የፈጠሯቸውና የዘለዓለም ወላጆቻቸው የኾኑት እናት እና ልጅ፤ በዚህም የሠርግ ግብዣ ላይ ተገኝተው፡ ይህን የምስጋና ገበታ እንደሚባርኩትና እንደሚቀድሱት ይታመናል።

፮. ከቀትር በኋላ፡ ከ፲ እስከምሽቱ ፲፪ ሰዓት፤ በሠርገኞቻቸው የታጀቡት ሙሽሮች፡ በቅዱሳትና በሥነ ፍጥረት የውበት መካናት ዘንድ የሚያደርጉትን ጒብኝት፤ በተመረጡ ቦታዎችም፡ የተዘጋጀላቸውን የመታሰቢያ ብርሃናዊ ሥዕል* የመነሣት ሥርዓት እየተዘዋወሩ በመፈጸም፡ የተቀደሰውን የሠርግ በዓላቸውን ሓሤት ያሚላሉ።

፯. ከምሽቱ ፲፪ እስከማታው ፪ ሰዓት፤ በሠርገኛው የመልስ ጒዞ ላይ፡ ተስማሚ በኾነ፡ የተዘጋጀ ሥፍራ፡ የራት ግብዣ የሚካኼድ ኾኖ፡ ግብዣው ሲያበቃ፡ ሙሽሮቹ፡ እዚያው፡ ሠርገኛውን ያሰናብቱና፡ ዐጃቢዎቻቸው፡ ሙሽሮቹን፡ ወደሳሬም ቤተ-ነግድ፡ በክብር በማድረስ፡ መርሓ ግብሩ ተጠቃልሎ ይፈጸማል።

+ + +

አዘጋጅ፡-

ኤርምያስ ከበደ ዓባይነሽ፤ ንቡረ-እድ፡ ዘአኵስም ጽዮን።

የኢትዮጵያ እግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ።

ከዚህ ልዩ ዕትም እና ከዘመኑ ቀን መቍጠሪያ ጋር፡ በዚሁ ደራሲ ተዘጋጅተው የታተሙትን፥ እየተሠራጩ ያሉትንም፡

ምናሴ፤ የመከራዬ ደስታ፣ ዓለምን ረታ!

ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!

ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!

Ethiopia: The Classic Case፥

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡ አንደኛ መጽሓፍ፣

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡ ኹለተኛ መጽሓፍ፣

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት፡ ሦስተኛ መጽሓፍ፣

ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ! ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት፥

አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ! ኢትዮጵያዊው፡ በጦብያ ፍለጋ! ፩ኛ መጽሓፍ"፥

አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ! ኢትዮጵያዊው፡ በእውነት ፍለጋ! ፪ኛ መጽሓፍ

አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ! ኢትዮጵያዊው፡ በዕውቀት ፍለጋ! ፫ኛ መጽሓፍ፣

ከሚለው ዕትምና በመጨረሻም፡ በኢትዮጵያኛና በእንግሊዝኛ የተሰናዱትን፡

የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ ትምህርት፡ ለኢትዮጵያ ሕፃናት፥ አንደኛ መጽሓፍ፥ እና ኹለተኛ መጽሓፍ፥ የተባሉትን፥ ወደፊትም፡ እየታተሙ የሚወጡትን፡ ሌሎች መጻሕፍት ለማግኘት፡ ከዚህ በታች በተመለከቱት፡ አድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች፡ መጠየቅ ነው።


**<u>ወኪል አከፋፋይ፡-</u> <u>ዋሽራ መጻሕፍት ቤት። ስልክ ቁጥር፡-</u>**

ዐ፱-፲፩-፷፫ ፶፪- ፳፭ (0911-63 52 25) እና ዐ፱-፲-፺፪-፵፱-፸፩ (0910-92-4971)።

አሳታሚ እና አከፋፋይ

Publisher & Distributor

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

**Ethiopia: The Kingdom of God.**

መልእክት ሣጥን ቍጥር፡ ፰፻፲፪። P. O. Box 812.

<u>ስልክ ቍጥር</u>፡- ዐ፲፩-፬-፲፮-፲፰-፹፭ እና ዐ፲፩-፫-፳-00-፹፭፤

<u>Tel.:-</u> (011-4-16-18-85 & 011-3-20-00-85)፤

<u>የኪስ ስልክ ቍጥር</u>፡- ዐ፱-፵፬-፩፻፪-፫-፷፰ እና ዐ፱-፲፩-፷፰-፵፬-፶፪፤

<u>Cellphone:-</u> (09-44-102-3-68 & 09-11-68-44-52)፤

አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ። Addis Abeba, ETHIOPIA

ወይም or

**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~ USA.**

**Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971**

Cellphone: 310-948-1024, 202-262-0230 & 202-262- 0713

Email: info@ethkogserv.org Web Site: www.ethkogs.org

Facebook: ethiopiathekingdomofgod